# ሰበር ኢትዮጵያ

ሚያዝያ 2006 - ልዩ እትም




## ፕሪምየር ሊግ

### በፕሪምየር ሊጉ 1ኛ ዙር ዙርያ ልዩ ጥንቅር



**ጥቂት ታክቲካዊ ነጥቦች በፕሪምየር ሊጉ ዙሪያ**
አዲስ ወርቁ

**አዲሱ የክለቦች ምዝገባ አሠራር በኢትዮጵያ**
ሳሙኤል የሺዋስ

**ማሊያ፣ ብራንድ እና ክለቦቻችን**
አብርሃም ገብረማርያም



ሶከር ኢትዮጵያ

Soccer Ethiopia, PO Box
25192/1000, Addis Ababa, Ethiopia
Tel: +251 -913-041-925
+251 -910-847-505
Email: info@soccerethiopia.com
Website: www.soccerethiopia.com
Facebook: Soccer Ethiopia
Twitter: @soccerethiopia

**የሶከር - ኢትዮጵያ ቡድን**

**ፀሐፊዎች**

አብርሐም ገብረማሪያም
ኦምና ታደሰ
አዲስ ወርቁ
ሳሙኤል የሺዋስ

**ለሶከር ኢትዮጵያ ፅሁፎችን ለመፃፍ ይፈልጋሉ?**

የኢትዮጵያ እግር ኳስን ከልብ የሚወዱ፣ በቋሚነት የሚከታተሉ፣ በእግር ኳሳችን ዙሪያ የተለያዩ ፅሁፎችን የሚፅፉ እንዲሁም ፅሁፎችዎ በሶከር ኢትዮጵያ እንዲወጡ የሚፈልጉ ከሆነ ከታች በተመለከተው የኢሜይል አድራሻ ይፃፉልን። ከህትመታችን ጋር የሚሄዱ ፅሁፎችን፣ ምስሎችን፣ ቪድዮዎችን ተቀብለን በቀጣይ እትሞች እናካትታለን።

ኢሜይል፡ info@soccerethiopia.net

ይጎብኙ፡ www.soccerethiopia.net

አብገ 21 ኮምዩኒኬሽን እና ማስታወቂያ
ABG 21 COMMUNICATION & ADVERT

# ሶከር ኢትዮጵያ እነሆ በኦንላይን መፅሄትም መጥታለች!



የእግርኳስ አድማስ ብዙ ነው:: አሰልጣኞች ከሚተገብሩት ፍልስፍና ጀምሮ እስከ ቡድኖች አጨዋወት፣ የደጋፊዎች የአደጋገፍ ስልት፣ የሀገራት የእግርኳስ ባህል እና ህዝቦች እግርኳስን የሚረዱበት መንገድ እጅግ በርካታ ነው:: የሜዳ ላይ እግርኳስን ምሉእ የሚያደርገው ሚዲያም እንዲሁ ዘርፈ ብዙ እና በርካታ አድማሶች አሉት:: ከትልቁ የኬብል ሚድያ እስከ ትንሹ የፌስቡክ ገፅ ድረስ እግርኳስ የሚዘገብበት፣ የሚወራበት እና ሀሳብ የሚንሸራሸርበት መንገድ ብዙ ነው:: ከእነዚህ የእግርኳስ እና የተከታታዩ አገናኝ ድልድዮች መሃከል በኢንተርኔት ላይ ጥገኛ የሆኑ ሚድያዎች አሁን አሁን ከቴክኖሎጂ መምጠቅ እና ከአጠቃቀም ቀላልነት ጋር ተዳምረው ወደ ተመራጭ ሚድያነት እየተሸጋገሩ ነው:: የእግርኳስ ድረገፆች፣ ኦንላይን ሜጋዚኖች፣ የማህበራዊ ድረገፆች እና ሌሎች ከኢንተርኔት ጋር የተያያዙ ሚድያዎች ቁጥር መበራከት የእግርኳስ እና ግሎባላይዜሽን አብሮ መሄድ ማሳያዎችም ናቸው::

የሚድያ እድገት ገና ጨቅላ በሆነባት ኢትዮጵያ ድረገጽ ተኮር የሆኑ ሚድያዎች በህብረተሰቡ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ እና እነዚህ ሚድያዎች ያለው ግንዛቤ አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ በሃገራችን ያለው እድገት እምብዛም ነው:: ከቁጥሮች አንፃር ካየነው በአሁኑ ሰአት ሶከር ኢትዮጵያን ጨምሮ በሃገራችን በእግርኳስ ላይ የሚያተኩሩ ድረገፆች ብዛት 3 ብቻ ሲሆኑ ከሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ጋር እግርኳስን በጣምራ የሚዘግቡ ድረገፆች ብዛት ከአንድ እጅ ጣቶች አይበልጡም:: በኦንላይን ሜጋዚን ደረጃ እስካሁን የተመዘገበ የለም:: በማህበራዊ ድረገፆች አማካኝነት የሚፈጠሩ ገፆች ቁጥር በንፅፅር የተሻለ ነው:: የክለቦች ፣ የተጫዋቾች እና የዜና ጎፆች እና ግሩፖች በተለይም በፌስቡክ በብዛት ይገኛሉ::

በሃገራችን ይህ አይነቱ ክፍተት የመጣበት ምክንያት የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ በሃገራችን ገና እየተዘወተረ በመምጣቱ ይሁን ሌላ ጥናት ቢያስፈልገውም ለኢንተርኔት ተኮር ሚድያዎች አለመስፋፋት ዋናው መንስኤ በኢትዮጵያ ያለው የኢንተርኔት ተጠቃሚ ቁጥር አነስተኛ መሆን ነው:: የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ ኢንተርኔት የሚጠቀመው ህብረተሰብ ከአጠቃላዩ ህዝብ 1 በመቶ ብቻ ነው:: ይህን ቁጥር ከግምት ብናስገባ እና በኢንተርኔት የሚገኙ የመረጃ አይነቶች እና አላማቸው ብዛት ብናሰላ የእግርኳስ መረጃዎችን ለመፈለግ ወደ ኢንተርኔት ካፌ የሚገባው ሰው ውስን ይሆናል::

የሆነው ሆኖ ሶከር ኢትዮጵያ ዳገቱን ለመውጣት ጥረቷን ከጀመረች ሰነባብታለች:: የኢንተርኔት ሚድያው እንደ ኤሌክትሮኒክስ ሚድያዎች በበርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ባይሆንም በኢትዮጵያ እግርኳስ ውስጥ መወጣት የሚገባትን ያህል ድርሻ ለማበርከት ጥረቷን ትቀጥላለች:: ዛሬ እየተመለከታችሁት ያለው የኦንላይን ሜጋዚንም የዚህ ጥረታችን አካል ነው:: ይህ ዝግጅት የመጀመርያ እንደመሆኑ በጥልቀቱ እና በመረጃዎቹ ላይ ክፍተት ሊኖር እንደሚችል ሶከር ኢትዮጵያ ታምናለች:: ነገር ግን ይህ ከ0 - 1 የምንልበት አጋጣሚ በመሆኗ በእግርኳሳችን ላይ የራሳችንን አሻራ እና በጎ ተፅእኖ ለማሳረፍ እንደመንደርደርያ እንደምትቆጥሩልን ተስፋ እናደርጋለን::

መፅሄቷ የመጀመርያ እትም እንደመሆኗ እና አመዛኙን የመፅሄት ክፍል በፕሪሚየር ሊጉ ግማሽ የውድድር ዘመን ላይ በማተኮሯ ይህን እትም ‹‹ልዩ እትም›› ብለን ሰይመነዋል:: መፅሄቷ በውስጧ የፕሪሚየር ሊጉ የመጀመርያ ዙር መጠናቀቅን አስመልክቶ በርካታ ፅሁፎችን ይዛለች:: ትንታኔዎች፣ ቁጥራዊ መረጃዎች፣ ታሪኮች፣ አስተያየቶች እና ሌሎች በርካታ ቁምነገሮች ተካተውበታል:: መፅሄቷን አንብበው ማወቅ ሊኖርባቸው የሚገባችሁን ቁምነገሮች ካገኛችሁ ዘንዳ አስተያየታችሁን፣ ጥቆማችሁን እና ማንኛውንም ምክንያታዊ ትችት በሙሉ ልብ ለመቀበል ሶከር ኢትዮጵያ ትጠብቃችኋለች:: ካለእናንተ አንባቢዎች ድጋፍ እና ማበረታቻ አንዲትም እርምጃ ፈቀቅ ማለት አንችልምና::

**መልካም ንባብ**

በዚህ መፅሄት ላይ የወጡ ፅሁፎች የሶከር ኢትዮጵያ ናቸው። እባክዎትን ፅሁፎቹን በሚጠቀሙበት ጊዜ ምንጭ መጥቀስዎን አይዘንጉ።



ገፅ 4

የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ዋና ትዕይንቶች ዳሰሳ

**23** HALL OF FAME | **የአሸዋ ሜዳ እንቁዎች**

የአሸናፊ ግርማ እና ዮርዳኖስ አባይ የእግር ኳስ ተጫዋችነት ህይወት

## ብሔራዊ ቡድን

**13** አዲሱ የብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ሊመለከቷቸው የሚገቡ 10 አዳዲስ ተጫዋቾች

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አዳዲስ ፊቶችን ባለማሳየቱ ሁልጊዜም ይታማል፡፡ በአንድ አጋጣሚ የተመረጠ ተጫዋች አቋሙ እና የአካል ብቃቱ ወርዶ እንኳን ከምርጫ አይዘለሉም፡፡ ከአንፃራዊ ስኬት እና የቻን ውድቀት በኋላ አዲስ የሚቀጠሩት አሰልጣኝ አደን ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ አዳዲስ ፊቶችን ሶከር ኢትዮጵያ በአጭሩ ታስተዋውቃለች፡፡

## ተጨማሪ ገፆች

**26** የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታዎች

በግማሽ የውድድር ዓመቱ የተደረጉት የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታዎች ቀን፣ ውጤት፣ ግብ አስቆጣሪዎች....

**27** የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የደረጃ ሠንጠረዥ

## አጫጭር መረጃዎች

**14** ዝውውር እና የተጫዋቾች መጥፋት

የኢትዮጵያ እግርኳስ ወደኋላ ከቀረባቸው ነገሮች አንዱ የዝውውር ሊስተሙ ነው፡፡ ክለቦች ተጫዋቾች እና አሰልጣኞችን የሚያዘዋውሩት በዘፈቀደ ሲሆን የፌዴሬሽኑ ስራ እና ሀላፊነትም የተዘዋወሩ ተጫዋቾችን መመዝገብ ብቻ ይመስላል፡፡ በኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ ተጫዋቾችን ለማዘዋወር ክለቦች ከወኪሎች ጋር መደራደር የማይታሰብ ነው፡፡

**14** የወላይታ ድቻ መምጣት ለአዲስ አበባ ቡድኖች ጠቅሟል

ገቢዎቹ ደፋ ባይሆኑም፣ የተረጋገጠ የፋይናንስ ጥናት ባይኖርም በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አንደኛው ዙር የአዲስ አበባ ክለቦች ከስታዲየም የሚያገኙት ገቢ ከሌሎች አመታት የበለጠ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡

## ሶከር-ቢዝ

**15** ማልያ፣ ብራንድ እና ክለቦቻችን

በኢትዮጵያ እግርኳስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ቢዝነስ፣ ገንዘብ፣ ብራንድ… የሚሉ ቃል ያሉ አይመስልም፡፡ በ2006 ግማሽ የውድድር ዘመንም ይህን አለማየታችን አያስገርምም፡፡ ሶከር ኢትዮጵያ በዚህኛው እትሟ በማልያ ብራንድ ላይ ትኩረት አድርጋ ክለቦቻችን ወዴት እያመሩ ነው ስትል ትጠይቃለች፡፡

## ታክቲክ

**17** ጥቂት ታክቲካዊ ነጥቦች በፕሪሚየር ሊጉ ዙርያ

አዲስ ወርቁ ለማህበራዊ ድረገፅ ተከታታዮች አዲስ አይደለም፡፡ በፌስቡክ እና ትዊተር በሚያቀርባቸው ጥልቅ ታክቲካዊ ትንተናዎች በርካታ አድናቂዎች አፍርቷል፡፡ ሶከር ኢትዮጵያ የፕሪሚየር ሊጉን አንደኛ ዙር መጠናቀቅ ተከትሎ ከአዲስ ጋር በታክቲክ ጉዳዮች ላይ አጭር ቆይታ አድርጋለች፡፡

## አስተዳደር

**20** አዲሱ የክለቦች ምዝገባ አሠራር በኢትዮጵያ

ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ማህበር ፊፋ እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም በጀርመኗ ሙኒክ ከተማ በጠራዉ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በየሀገራቱ ዉስጥ የሚደረገዉ የእግር ኳስ እንቅስቃሴ የተሻለ ፕሮፌሽናል መልክ እንዲኖረዉ ያግዛል በሚል ያዘጋጀዉን የክለቦች ምዝገባ አሠራር (Club Licensing) ለመጀመርያ ጊዜ ያስተዋዉቃል፡፡ በስብሰባዉ የተገኙ የ209ኙ አባል ፌደሬሽን ተወካዮችም በጉዳዩ ዙሪያ ከተወያዩ በኋላ የፊፋን ሐሳብ በመቀበል በየአህጉራቱ የሚገኙ ኮንፌዴሬሽኖች ይህን አሰራር ተቀብለዉ እንዲተገብሩ ዉሳኔ በማሳለፍ ጉባኤዉን አጠናቀቁ፡፡ የአዉሮፓ እግር ኳስ ማህበር (UEFA) አዲሱን አሰራር በመተግበር የመጀመሪያዉ ሲሆን በሌሎች ኮንፌዴሬሽኖችም ይህ የክለቦች ምዝገባ አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡

**10** የሶከር ኢትዮጵያ የውድድር ዓመቱ ምርጥ ቡድን

ሶከር ኢትዮጵያ እስከ ውድድር ዓመቱ አጋማሽ ድረስ ለክለቦቻቸው ጥሩ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ተጫዋቾችን በመምረጥ የውድድር ዓመቱ ምርጥ 11 ተጫዋቾች፣ ተጠባባቂዎች እና አሠልጣኙን ተመርጣለች፡፡

# የ2006 የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ምርጥ እና ደካማ እንቅስቃሴዎች

በ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አንደኛው ዙር ከተደጋጋሚ መቆራረጥ በኃላ በቅርቡ በርካታ ክስተቶችን አስተናግዶ ተጠናቋል። ውድድሩ እየተቆራረጠ መካሄዱ ለትውስታ የማይበቃ እና የፈዘዘ ውድድር ቢያደርገውም በ1ኛው ዙር የተደረጉት 91 ጨዋታዎች ለግምገማ በቂ ናቸው ብለን እናምናለን። ሶከር ኢትዮጵያም የውድድር ዓመቱን የመጀመሪያ ግማሽ እንቅስቃሴዎች ወደኋላ በመመልከት በምርጥ እና ደካማ መልካቸው ገምግማ እንዲህ ዳሳዋለች።

## ምርጥ ተጫዋቾች - ኡመድ ኡክሪ

በ2006 ዓ.ም. የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ኡመድ ኡክሪ ውጤታማ እንቅስቃሴ ያደረገ ተጫዋች ለማግኘት ይከብዳል፡፡ የቅዱስ ጊዮርጊሱ አጥቂ ለክለቡ የሚያሳየውን እንቅስቃሴ ለብሔራዊ ቡድኑ መድገም ባለመቻሉ በብዙዎች ቢታማም ዘንድሮ በሊጉ እያሳየ የሚገኘው አቋም ግን አስደናቂ ነው፡፡ እስካሁን በውደድር ዓመቱ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ባደረጋቸው 13 የሊግ ጨዋታዎች 10 ግቦችን እንዲሁም በጥሎ ማለፍ ዋንጫ 1 ግብ በማስቆጠር አስደናቂ የማግባት ሪከርድ ከመያዙም በላይ የግብ አጋጣሚዎችን ለቡድን ጓደኞቹ በመፍጠር በኩል ያስመዘገበው ውጤት ሁለገብ ተጫዋች መሆኑን ያመላክታል፡፡ በተፈጥሮ ግራኝ የሆነው ኡመድ ምንም እንኳን አሁንም ለግራ እግሩ አድልቶ ቢጫወትም ቀኝ



እግሩን በተሻለ ሁኔታ በመጠቀም ያሳየው መሻሻል ለዘንድሮው ምርጥ አቋሙ አንድ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በሊጉ 7ተኛ ሳምንት መከላከያ ላይ ከረጅም ርቀት በቀኝ እግሩ አክርሮ በመምታት ያስቆጠራቸው ሁለት ግቦች ለዚህ ግልፅ ማሳያ ናቸው፡፡ በ2014ቱ የዓለም ዋንጫ ቅድመ ማጣሪያ በአዲስ አበባ ስታዲየም ሱማልያ ጋር ከተደረገው ጨዋታ በኋላ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ግብ ያላስቆጠረው ኡመድ አሁን የያዘውን አቋም በኢትዮጵያ ማሊያ ለመድገም ከቻለ ለሳልሃዲን ሰይድ እና ጌታነህ ከበደ ጥሩ ተፎካካሪ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

### ሊጠቀሱ የሚገባቸው

#### ፍሬው ሰለሞን

ትንሹ ልጅ አጨዋወቱ፣ ሚናው እና የሰውነት እንቅስቃሴው ሁሉ የቀድሞውን የአርሰናል የመስመር አማካይ ሮቤር ፒሬዝን ያስታውሰናል፡፡ ሁለቱ ተጫዋቾች በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ተጫዋቾች ቢሆኑም ፍሬው የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ‹‹ ዳክዬ ›› ነው፡፡ አጨዋወቱ የማይገመት እና ፈጣን ሲሆን ተጫዋቾችን አታሎ ለማለፍ አይቸገርም፡፡ አምና በገብረመድህን ኃይሌ መሪነት መከላከያ ምርጥ የውድድር ዘመን ሲያሳልፍ ጉልህ አስተዋፅኦ ቢያበረክትም የአስር ቁጥሩ የአጥቂ አማካይ የዘንድሮ አስደናቂ ብቃት ከሌሎች አመታት የተለየ ነው፡፡

ፍሬው ዘንድሮ ድንቅ የውድድር ዘመን እንዲያሳልፍ የገብረመድህን ኃይሌ አጨዋወት ጠቅሞታል፡፡ ቀጥተኛ 4-4-2 አሰላለፍ ለሚመርጡት ገብረመድህን ፍሬው ከግራ መስመር እየተነሳ ወደ ውስጥ ሰብሮ እንዲገባ እና ወደ የትኛውም የማጥቃት ወረዳ በነፃነት እንዲንቀሳቀስ ነፃነት ተሰጥቶታል፡፡ እርሱም ቢሆን የተሰጠውን ነፃነት በሚገባ ሊጠቀምበት ችሏል፡፡ ቡድኑ በአማካይ ስፍራ የቁጥር ብልጫ ሲወሰድበት ወደ አማካይ ክፍል በመጠጋት ተጨማሪ አማካይ በመሆን ክፍተቱን ይሸፍናል፡፡ ቡድኑ በተጋጣሚ ተከላካዮች ክፍተት ማግኘት በሚሳነው ሰአት ኳስ ወደ ግራ በመውሰድ የተጋጣሚ ተከላካዮች እንዲለጠጡ በማድረግ ለማናዬ ፋንቱ ክፍተት ይፈጥራል፡፡ ኢትዮጵያ ልትጠቀምባቸው ከሚገቡ ድንቅ የአጥቂ አማካዮች አንዱ የሆነው ፍሬው አዲስ የሚሾሙት የብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝ በቅድሚያ ሊመለከቷቸው ከሚገባቸው ምርጥ አማካዮች አንዱ ነው፡፡

#### ኤልያስ ማሞ

በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከፍተኛ መሻሻል ያሳየ 10 ቁጥር ነው፡፡ በሊጉ ምንያህል ተሾመ፣ ታደለ መንገሻ እና ወንድሜነህ ዘሪሁንን የመሳሰሉ ጥሩ አቋም ያሳዩ 10 ቁጥሮች ቢኖሩም ኤልያስ ማሞ ዘንድሮ የተለየ ብቃቱን ይዞ ቀርቧል፡፡ ፈጣን እና ድንቅ ኳስ አቀባይ የሆነው የቀድሞ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋችን ብዙዎች የሙሉአለም ረጋሳ ኮፒ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ የታሰበውን ያህል እድገት ባያሳይ የዘንድሮ አቋሙ የምንጠብቅበት ደረጃ የመድረስ አቅም እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡

#### ዳዊት እስጢፋኖስ

የኢትዮጵያ ቡናው 10 ቁጥር የዘንድሮ አቋም ልዩ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ቡና 4ኛ የውድድር ዘመኑን የያዘው ዳዊት የቡድኑ አምበል መሆኑን ተከትሎ በድንቅ አቋሙ ላይ እርጋታንና ብስለትን አክሎበታል፡፡ በዚህም ቡና በእጅጉ ተጠቅሟል፡፡ አደገኞቹ በተከታታይ ላስመዘገቡት ውጤትና የደረጃ መሻሻል ዋናውን ድርሻ የሚወስደው ዳዊት ነው፡፡ ወሳኝ ግቦችን ያስቆጥራል፣ ለአጥቂዎች ያለቀላቸውን ኳሶች ቀርባል፣ በክህሎት የበለፀገ በመሆኑ በጠባብ ቦታዎች እንኳን ተጫዋቾችን ለማለፍ አይቸገርም፣ በጥልቀት ወደ ኋላ እየተመለሰ ክፍተት ለመድፈን ይጥራል፣ አምበል በመሆኑም ሀላፊነት የሚሰማው ‹‹የቡድን ተጫዋች›› ሆኗል፡፡ በቅርቡ ቢጎዳም ሲመለስ አቋሙን ጠብቆ መዝለቅ ከቻለ በኢትዮጵያ ቡና የውድድር አመቱ ጉዞ ላይ የራሱን አሻራ ያሳርፋል፡፡

## ደካማ ተጫዋቾች - ግሩም ተስፋዬ

ለመጀመርያ ጊዜ ስታዲየም ገብቶ ጨዋታ የሚመለከት ሰው በመጀመርያ እይታው ግሩም ተስፋዬን ከተመለከተ የሊጉ ተጫዋቾችን ደረጃ እጅጉን አውርዶ መመልከቱ የማይቀር ነው፡፡ በፕሪምየር ሊጉ እጅግ በርካታ የማይመጥኑ ተጫዋቾች ቢታዩም የመድን የመጀመርያ ተመራጭ የሆነው ቀውላላው የፊት አጥቂን የሚያህል ይገኛል ብሎ መገመት አዳጋች ነው፡፡ ግሩም ጥሩ የአጥቂ ቁመና ቢኖረውም ከኳስ ጋር እና ያለኳስ የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ የመጀመርያ የኳስ ንክኪው እና የጨዋታ ውጪ አጠባበቁ እጅግ ደካማ ነው፡፡ በሊጉ የተመዘገቡ የቁጥር መረጃዎች ቢኖሩ ኖሮ ምናልባትም ዘንድሮ ለበርካታ ጊዜያት ከጨዋታ ውጪ ተብሎ ባንዲራ የተነሳበት ተጫዋች ይሆን ነበር፡፡

### ሊጠቀሱ የሚገባቸው

#### ሚካኤል ጆርጅ

በክረምቱ የዝውውር መስኮት ደደቢት ጌታነህ ከበደን የተኩልኛል በማለት ካስፈረማቸው 2 አጥቂዎች ውስጥ አንዱ የሆነው 'ጆርጆ' በውድድር አመቱ አምና ለሲዳማ ቡና ያሳየውን እንቅስቃሴ መድገም አልቻለም፡፡ አጥቂው ዘንድሮ ለደደቢት 1 ግብ ብቻ ያስቆጠረ ሲሆን ባደረጋቸው ጨዋታዎች ላይ ባሳየው ደካማ አቋም ምክኒያትም ወደ ተቀያሪ ወንበር ወርዶ የዳዊት ፍቃዱ እና የቀድሞ የሲዳማ ቡና ጓደኛው አሸናፊ አደም ተጠባባቂ ለመሆን ተገዷል፡፡ በውድድር ዓመቱ አጋማሽ ደደቢት ጋናዊውን አጥቂ ሳሙኤል አቶ ጋንሳህን ከቱኒዚያው ክለብ KST ያስፈረመበት ዋንኛው ምክኒያትም ለዳዊት ፍቃዱ ከነሚካኤል ጆርጅ የተሻለ የአጥቂ መስመር አጣማሪ

እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡

## ምርጥ አሰልጣኝ


### ማርት ኖይ

ሆላንዳዊው የቅዱስ ጊዮርጊስ አሠልጣኝ ያለምንም ተቀኛቃኝ የፕሪምየር ሊጉ ምርጥ አሠልጣኝ እንደሆኑ በውድድር ዓመቱ ያስመዘገቡት ውጤት በግልፅ ያሳያል፡፡ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ አዲስ የሆኑት የቀድሞ ሞዛምቢክ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ በሊጉ ጅማሬ ላይ ቅዱስ ጊዮርጊስ በወላይታ ዲቻ እስከተሸነፈበት ጊዜ ድረስ ያደረጋቸውን 10 ተከታታይ ጨዋታዎች በማሸነፍ በኢትዮጵያ እግር ኳስ አዲስ ታሪክ እንዲያስመዘግብ ረድተውታል፡፡ አሠልጣኙ በዋነኛነት በሚተገብሩት የ4-2-3-1 አሰላለፍ ምንያህል ተሾመ በ10 ቁጥር ሚና ብቸኛ አጥቂ ከሆነው ኡመድ ኡክሪ ጀርባ እንዲጫወት ያደረጉበት ሂደት ውጤት አስገኝቶላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጫዋቾችን ከለመዱት ቦታ ውጪ በተለያየ ሚና እንዲሰለፉ የሚያደርጉበት ልምዳቸው ፍሬያማ አድርጓቸዋል፤ ቅዱስ ጊዮርጊስም በአሠልጣኙ የአጨዋወት ዘይቤ አንዳንድ ጨዋታዎች ላይ ሙሉ የጨዋታ ብልጫ ወስዶ በሰፊ ጎል ልዩነት ሲያሸንፍ አይተነዋል፡፡ እዚህ ላይ የጀርመናዊው አሠልጣኝ ማይክል ክሩገር መሰናበትን ተከትሎ ቡድኑን በዋናነት ሲመሩ የቆዩት እና አሁን በምክትል አሠልጣኝነት በክለቡ የሚገኙት የፋሲል ተካልኝ እና ዘሪሁን ሸንገታ አስተዋፅኦ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ ኖይ የታንዛኒያ ብሔራዊ ቡድንን በመረከብ ከጊዮርጊስ መልቀቃቸው ለክለቡ የሚያስቆጭ ነው፡፡ በውጤት ደረጃ ቀጣዩ የብሄራዊ ቡድናችን አሠልጣኝ ማርት ኖይ በጊዮርጊስ ያመጡትን ያህል ለውጥ ማምጣት ከቻሉ ጠንካራ ብሔራዊ ቡድን ይኖረናል፡፡

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### ፀጋዬ ኪዳነማርያም

የአምናው የውድድር ዘመን የንግድ ባንክ ምስቅልቅል ጉዞ ያስታወሰ የክለቡ የዘንድሮ የውድድር ዘመን ተሻሽሎ መቅረብ ምስጢር አሰልጣኝ ፀጋዬ ኪዳነማርያም እንደሆኑ ይረዳል፡፡ ላለፉት 10 አመታት በትራንስ ኢትዮጵያ፣ ሀረር ቢራ እና ኢትዮጵያ ቡና በገነቡት መልካም እግርኳስ የሚጫወት ቡድን ትልቅ ከበሬታን ቢያተርፉም የቀድሞው ድንቅ አጥቂ በብዙዎች ዘንድ ለትልቅ ስራ መታጨት የጀመሩት አሁን አሁን ነው፡፡



ካለፈው አስከፊ የውድድር ዘመን በኋላ አሰልጣኝ ውበቱ አባተን ያሰናበቱት ንግድ ባንኮች ከኢትዮጵያ ቡና ጋር ውዝግብ ውስጥ የከረሙት እና በሃንጋሪ የአሰልጣኝነት ትምህርት ተከታትለው የተመለሱት ፀጋዬ ኪዳነማርያምን የክለቡ አሰልጣኝ አድርጎ ሲሾም የዝውውር ሂደቱን ጉዳዬ ብሎ የተከታተለው አልነበረም፡፡ ፀጋዬ ሃምራዊዎቹን ሲረከቡ አምና ወሳኝ ተጫዋች የነበሩት ፍፁም ተፈሪ (ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ)፣ ኤፍሬም የወንድወሰን (ወደ ዳሸን ቢራ)፣ ምንያህል ወንድሙ እና ቢንያም አሰፋ (ወደ ኢትዮጵያ ቡና) አሰናብቶ እና በአዳዲስ ተጫዋቾች ተሞልቶ ለመላመድ ጊዜ የሚፈልግ ቡድን ነበር፡፡ በውድድር ዘመኑ የመክፈቻ ጨዋታ በአዲስ መጪው ወላይታ ዲቻ አዲስ አበባ ስታዲየም ላይ 4-0 ሲረመረሙ አሰልጣኝ ፀጋዬ በቡድኑ ውስጥ ሊያስተካክሏቸው የሚገቡ በርካታ የቤት ስራዎች እንዳሉ አመላከተ፡፡ ይህ ሽንፈት የአሰልጣኝ ፀጋዬ በንግድ ባንክ ቆይታቸው የመጀመርያ ሽንፈታቸው ሆኖ ከተመዘገበ ከ5 ወራት በኃላ ንግድ ባንክ የተደራጀ፣ በቀላሉ ግቡ የማይደፈር እና ውጤታማ መሆን ችሏል፡፡ ለዚህ በአጭር ጊዜ ለታየው አስገራሚ መሻሻል የመጀመርያ ተመስጋኝ ሊሆኑ የሚገባቸው አሰልጣኝ ፀጋዬ ኪዳነማርያም ናቸው፡፡

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### መሳይ ተፈሪ

የቀድሞው የአርባምንጭ ጨርቃጨርቅ ግብ አዳኝ የሊጉ ወጣቱ አሰልጣኝ ነው፡፡ ከወጣትነቱ እና ከወላይታ ዲቻ የመጀመርያ የውድድር ዘመን ተሳትፎ አንፃር የአንደኛው ዙር ውጤቱ በግርምት አፍ የሚያስይዝ ነው፡፡ ለትልልቅ ክለቦች የሚከብደውን ሊግ ተቋቁመው በመጀመሪያው ዙር ባደረጓቸው 13 ጨዋታዎች አንድ ሽንፈት ብቻ ከማስተናገዳቸውም በላይ የተቆጠረባቸው የግብ ብዛት (7) ለአዲስ መጪ ክለብ ጥሩ የሚባል ቁጥር ነው፡፡በጥሎ ማለፉ ዋንጫም ቢሆን በመከላከያ 1-0 ሲሸነፉ በዳሶ ሆራ ያስቆጠራት ጎል በግልፅ ከጨዋታ ውጪ የነበረ ሲሆን በዚህ ምክኒያትም በመስመር ዳኛው ላይ የክስ ሪዞርቭ እስከማስያዝ ደርሰው ነበር፡፡ በተለይ የካቲት 27 ቀን ቅዱስ ጊዮርጊስን 2-1 ባሸነፉበት የሁለተኛ ሳምንት ተስተካካይ ጨዋታ በማርት ኖይ ላይ አስገራሚ የታክቲክ ብልጫ በመውሰድ ትልቁን ቡድን ያንበረከከበት መንገድ ይህ ወጣት አሠልጣኝ ወደፊት ብሩህ ጊዜ እንደሚጠብቀው ያሳያል፡፡ የእስካሁኑ የዲቻ ጉዞ ለመሳይ ተፈሪ ከበቂም በላይ ነው፡፡

## ደካማ አሰልጣኝ

### አስራት ሐይሌ

መድን በደረጃ ሰንጠረዡ ግርጌ ላይ ለመቀመጡ አስራት ኃይሌ ብቸኛው ተወቃሽ መሆን አይገባቸውም፡፡ በስብስባቸው ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ተጫዋቾች የመድንን መለያ ለመልበስ የማይመጥኑ ናቸው፡፡ ምክንያቶቹ እንዳሉ ሆነው ግን የአሰልጣኝ አስራት የቀድሞ ተፅእኖ አሁን የለም፡፡ በቀድሞ ቡድኖቻቸው ላይ የምናየውን የአሸናፊነት ስነ-ልቦና፣ የአካል ብቃት የበላይነት፣ ጥብቅ መከላከል እና ኮስታራ አቀራረብ በዘንድሮው መድን ላይ አልተመለከትንም፡፡ እጅጉን የላላ የተከላካይ ክፍል፣ ግብ የማያስቆጥር የአጥቂ መስመርና በቀላሉ የሚበለጥ የአማካይ የዘንድሮው የመድን መለያ ነው፡፡ ቡድኑ ሲመራ እና በእንቅስቃሴ ሲበለጥ የአሰልጣኝ አስራት መፍትሄ የመፈለግ ተነሳሽነት እጅጉን የወረደ ነው፡፡ በሁለተኛው ዙር ማንሰራራት ካልቻሉ የአሰልጣኙ የስራ ህይወት ማክተምያ ልንመለከት እንችላለን፡፡

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### መኮንን ገብረዮሐንስ

ዳሸን ቢራን ወደ ሊጉ ያሳደጉት አሰልጣኝ መኮንን የሊጉን ሪከርድ ጭምር ሰባብረው ከግማሽ ደርዘን በላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ተጫዋቾችን ቢያስፈርሙም ቡድኑን ማዋሃድ ተስኗቸው ቡድኑን በወራጅ ቀጠናው እንዲዳክር አድርገውታል፡፡ ከሁሉም በላይ እስከስንብታቸው ድረስ ዳሸን ቢራ አንድም ግብ አለማስቆጠሩ የአሰልጣኙን ደካማ የውድድር ዘመን በሚገባ ያሳየናል፡፡

### ዮርዳን ስቶይኮቭ

ቡልጋርያዊው ታክቲሺያን ባለፈት 3 የውድድር ዘመናት መብራት ኃይል ካለው የተጫዋች ስብስብ አንፃር መልካም ቡድን ቢገነቡም ዘንድሮ ምናልባትም በመብራት ኃይል ግማሽ ምዕተ አመት ታሪክ ጎልቶ የሚጠቀስ ደካማ የውድድር ዘመን አጋማሽ አሳልፈዋል፡፡ የዮርዳን ስብስብ የውጤት ረሃብ፣ የጨዋታ ፍላጎት እና ተነሳሽነት የማይታይበት፣ ለቡድኑ የማይመጥኑ ተጫዋቾች የበዙበት እና ደካማ የቡድን ውህደት የታየበት ቡድን ነው፡፡ ምናልባትም ቡድኑ ወሳኝ ተጫዋቾቹን ባንድ ጊዜ መልቀቁ ተፅዕኖ ፈጥሮበት ይሆናል፡፡

## ምርጥ ፈራሚ

### በኃይሉ አሠፋ

የአምናውን የውድድር ዘመን ከደደቢት ጋር በሊግ ሻምፒዮንነት ያጠናቀቀው በኃይሉ አሠፋ ቀስ በቀስ ወደ ወሳኝ ተጫዋችነት መለወጥ ጀምሯል፡፡ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በ2006 በተደረጉ ጨዋታዎች በአብዛኛው በቋሚነት

የጀመረው ብልሁ የመስመር አማካይ በአሰልጣኝ ማርት ኖይ የጨዋታ ሲስተም ውስጥ ጠቃሚ ተጫዋች ነው፡፡ አሰልጣኝ ማርት ኖይ በአብዛኛው በሚጠቀሙባቸው የ4-2-3-1 እና 4-3-3 ሲስተም ውስጥ በሚፈልጉት ቀጥተኛነት እና ስፋት በኃይሉ ትክክለኛው ተጫዋች ሆኖላቸዋል፡፡

### ሊጠቀሱ የሚገባቸው

**ሳምሶን ጥላሁን**

‹ባርያው› በአጭር ጊዜ የሻምፒዮኖቹ አስኳል ሆኗል፡፡ ደቃቃው አማካይ ሜዳ የማካለል ብቃት፣ ኳስ የመቀበል ዝግጁነት፣ የቴክኒክ ብቃት፣ ቁልፍ ኳሶችን የማሻገር ብቃት እና ከርቀት ወደ ግብ የሚሞክራቸው አደገኛ ኳሶች የተመለከቱ ሁሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለምን ለተቀናቃኙ አሳልፎ እነደሰጠው ይጠይቃሉ፡፡ የደደቢት ደጋፊዎች የአዲስ ህንፃን መልቀቅ እንዲረሱ ያደረጋቸው ሳምሶን ወጣት እንደመሆኑ የመጪው ጊዜ ባለቤት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡

## ደካማ ዝውውር

**ሚካኤል ጆርጅ**

ረጅም እና መልከ መልካሙ የቀድሞ የሙገር ሲሚንቶ እና ሲዳማ ቡና አጥቂ ደደቢትን የተቀላቀለው አምና እስከ ብሄራዊ ቡድን ምርጫ ድረስ ባደረሰው የሲዳማ ድንቅ አቋሙ መነሻነት ነበር፡፡ ሲዳማ ቡና ካለው የተጫዋች ስብስብ እና አጣማሪዎቹ አንፃር ለደደቢት ጥሩ ስብስብ ተጨማሪ ኃይል ይሆናል ተብሎ ቢጠበቅም ሚካኤል የተጠበቀውን ሳይሆን ቀርቶ የተጠባባቂ ወንበር አሟቂ ሆኗል፡፡
አጥቂው በጥሎ ማለፉ፣ በፕሪምየር ሊግ እና በቻምፒዮንስ ሊግ ውድድሮች ያስቆጠረው ግብ 1 ብቻ ሲሆን ከጌታነህ ከበደ ‹‹ 9 ›› ቁጥር ስኬት ጥላ መላቀቅ ተስኖታል፡፡ ለሚካኤል በደደቢት ስኬታማ አለመሆን ምክንያቶችን ማስቀመጥ እንችላለን፡፡
1ኛ. አሰልጣኝ ንጉሴ ደስታ አምና 21 ግቦች ያስቆጠረላቸው ዳዊት ፍቃዱን በብቸኝነት መጠቀምን መርጠዋል፡፡ 4-2-3-1 አሰላለፍን የሚመርጡት አሰልጣኝ ንጉሴ በሊጉ ላለፉት 7 የውድድር ዘመናት ግብ የማስቆጠር ጥሩ ሪከርድ ያለው ዳዊት ፍቃዱን ወደ መስመር አውጥተው ሚካኤልን በብቸኛ አጥቂነት ማሰለፍ አደጋው የበዛ ነው፡፡ ፍጥነት፣ የቴክኒክ ችሎታ እና ቅልጥፍና ያሌታደለው ሚካኤል እየቀረ ለመጣው 4-4-2 ይበልጥ ጠቃሚ ተጫዋች ነው፡፡
2ኛ. በትልቅ ደረጃ የመጫወት ልምዱ የለውም፡፡ በደረጃ ሰንጠረዡ ወገብ ላይ ለሚዋልለው ሙገር ሲሚንቶ በመጫወት ረጅሙን የእግር ኳስ ህይወቱን ያሳለፈው ሚካኤል በትልቅ እና በየአመቱ ለዋንጫ በሚፎካከር ቡድን ውስጥ ቦታ ማግኘት እና ራሱን ማሳየት ጊዜ ይወስድበታል፡፡ በደደቢት ታሪካዊ ተጫዋች ለመሆን የበቃው ጌታነህ ከበደ እንኳን የመጀመርያ የደደቢት የውድድር ዘመኑ በፈተና የተሞላ እንደነበር ማስታወስ ይኖርብናል፡፡

### ሊጠቀሱ የሚገባቸው

**እንዳለ ከበደ**

ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስፖርት ፋስቲቫል የተገኘው ባለ አስደናቂ ክህሎት አማካይ በሲዳማ ቡና ‹‹የጠፋ በግ›› ሆኗል፡፡ የድሪብሊንግ ብቃቱ፣ ጥንካሬውና ከመስመር ወደ ውስጥ ሰብሮ የመግባት ብቃቱ ለብሄራዊ ቡድን የሚያሳጩ ነበሩ፡፡ በክረምቱ የተጫዋቾች ዝውውር መስኮት አርባምንጭ ከነማን ለቆ በ600 ሺህ ብር ሂሳብ ወደ ይርጋለም ያመራው እንዳለ በዘንድሮው ደካማ የሲዳማ ቡና የውድድር ዘመን ውስጥ ራሱን ማግኘት ተስኖታል፡፡




**አስራት መገርሳ**

አስራት መገርሳ ከሊጉ 5 ኮከብ ተጫዋቾች አንዱ ነው፡፡ የፕሪምየር ሊጉን ያለፉት 5 አመታት ምርጥ ቡድን እንስራ ብንል እንኳን የማይቀር ተጫዋች ነው፡፡ ረጅሙ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን የመሃል ሜዳ ምሰሶ መብራት ኃይልን ለቆ በእስራኤል የጥቂት ወራት ቆይታ አድርጎ ዳሽን ቢራ ከፈረመ ወዲህ ያን ያህል በቡድኑ ላይ የተጋነነ ለውጥ መፍጠር ተስኖት ቆይቷል፡፡ ባለ 800 ሺህ ብር ፈራሚው ሊጠቀስለት የሚችል ነገር ቢኖር በዳሽን ቢራ የፕሪምየር ሊግ ታሪክ የመጀመርያውን ታሪካዊ ግብ ያስቆጠረ ተጫዋች መሆኑ ብቻ ነው፡፡

## ምርጥ ወጣት ተጫዋች

**ሳልሃዲን ባርጌቾ**

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ውስጥ ለወደፊቱ ትልቅ ተስፋ ከተጣለባቸው ተጫዋቾች አንዱ የ19 ዓመቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተከላካይ ሳልሃዲን ባርጌቾ ነው፡፡ አምና በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የውድድር ዓመቱ ለኢትዮጵያ መድን በተከላካይነት እና በተከላካይ-አማካይነት በመጫወት ካሳየው አስደናቂ አቋም በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስን የተቀላቀለው ‘ሳላ’ በአፍሪካ ኮንፌዴሬሽኖች ዋንጫ ለአዲሱ ክለቡ በመሀል እና በመስመር ተከላካይነት ተሰልፎ ተጫውቷል፡፡ በኬኒያ በተደረገው 37ተኛው የሴካፋ ውድድር ለተሳተፈው ብሔራዊ ቡድን ከኢትዮጵያ ቡናው ቶክ ጀምስ ጋር ጠንካራ የተከላካይ ጥምረት ከመፍጠራቸው በተጨማሪ በአለም ዋንጫ ማጣሪያ ቡድኑ ከሜዳው ውጪ ከመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ እና ናይጄሪያ ጋር ባደረጋቸው ጨዋታዎች በቋሚ አሠላለፍ ውስጥ ተካቷል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ አፍሪካው የአፍሪካ ሐገራት ሻምፒዮና ከኮንጎ እና ጋና ጋር በተደረጉት ጨዋታዎች በመሰለፍ በግሉ ጥሩ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ ሳልሃዲን በ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግም ቢሆን በቅዱስ ጊዮርጊስ የመሀል ተከላካይ ክፍል ውስጥ ቦታውን አስከብሯል፡፡ ዘንድሮ ክለቡ ካደረጋቸው የሊግ ግጥሚያዎች ውስጥ በአብዛኛዎቹ ላይ ከቢያድግልኝ ኤሊያስ አልያም ከዩጋንዳዊው አይዛክ ኢሲንዴ ጋር በመጣመር ጥሩ ለመጫወት ችሏል፡፡ በውድድር ዓመቱ በተለያዩ ውድድሮች ያሳየው ምርጥ አቋም ምክኒያት አውሮፓ ውስጥ በሚገኙ ክለቦች ጭምር እየታደነ ይገኛል፡፡

### ሊጠቀሱ የሚገባቸው

**ሳምሶን ጥላሁን**

ሳምሶን ኢትዮጵያ አለኝ ብላ ልትተማመንበት የሚገባ ምርጥ ታዳጊ ነው፡፡ ገና ወጣት ቢሆንም በደደቢት የመሃል ሜዳ ክፍል ጉልህ ሚና የሚወጣ ተጫዋች ሆኗል፡፡ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ደደቢትን የተቀላቀለው ዘንድሮ ቢሆንም ደቃቃው 8 ቁጥር ከቡድኑ ጋር በሚገባ ተዋህዷል፡፡ ሳምሶን ይህን ድንቅ ብቃት ይዞ የሚቀጥል ከሆነ ብሩህ ጊዜ ወደፊት እንደሚጠብቀው አያጠራጥርም፡፡

## አዲስ ታለንት

**ተመስገን ዱባ**

በፕሪምየር ሊጉ የመጀመሪያ የውድድር ዓመቱን እያሳለፈ የሚገኘው የአርባምንጭ ከነማ ኮከብ የዘንድሮ ክስተት ነው፡፡ ከቀኝ መስመር የሚነሳው ፈጣን አማካይ የእንዳለ ከበደን መልቀቅ በፍጥነት አስረስቷል፡፡ በዋንኛነት በክንፍ በኩል በሚላኩ ኳሶች ግቦችን ለማስቆጠር ጥረት ለሚያደርጉት አርባምንጮች ተመስገን ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ አጥቂው ገብረሚካኤል ያዕቆብ የተለመደውን ግልጋሎት እየሰጠ በማይገኝበት በዘንድሮ የውድድር ዘመን ተመስገን የግብ አጋጣሚዎችን ለቡድን ጓደኞቹ ከመፍጠር በተጨማሪ ወደፊት በመሄድ ወሳኝ ግቦችን ለማስቆጠር ችሏል፡፡ ይህ ተጫዋች እያሳየ እንዳለው አቋም በአርባምንጭ ከነማ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አይመስልም፡፡

### ሊጠቀሱ የሚገባቸው

**ብሩክ ቃልቦሬ፣ ዘካሪያስ ታደሰ፣ አሸናፊ ሽብሩ**

ከብሔራዊ ሊግ ያደገው ወላይታ ዲቻ ዘንድሮ አስገራሚ አቋም እያሳየ ይገኛል፡፡ ለቡድኑ የዘንድሮ ውጤት ባዬ ገዛኸኝ፣ ተስፋዬ መላኩ፣ ሳምሶን ኮሌቻን የመሳሰሉ ተጫዋቾች

የየግላቸውን አስተዋፅኦ የተወጡ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱት ልጆች ግን ልዩ ብቃትን አሳይተዋል፡፡ ብሩክ ቃልቦሬ በኬንያው የሴካፋ ዋንጫ ተሳታፊ ለመሆን የቻለ ሲሆን በኢትዮጵያ ማሊያ ባደረገው የመጀመሪያ ጨዋታም ደቡብ ሱዳን ላይ በምርጥ አጨራረስ ግብ አስቆጥሯል፡፡ ተጫዋቾቹ ወደፊት በመሄድ የዲቻን የአጥቂ ክፍል ከማገዛቸውም በላይ የሊጉ ጠንካራ የተከላካይ ክፍልን በመደገፍ ቡድኑ ባለመሸነፍ ጉዞው እንዲቀጥል ረድተውታል፡፡ ተጫዋቾቹ ከወዲሁ የብዙ ክለቦችን ትኩረት የሳቡ ቢሆንም አንዳንዶች በሌሎች ክለቦች ውጤታማ ላይሆኑ ይችላሉ እያሉ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ለዚህ ሀሳባቸው እንደምክኒያት የሚያነሱትም ልጆቹ በጋራ እንደቡድን ሲጫወቱ ጥሩ አቋም ቢያሳዩም የሚለያዩ ከሆነ በግላቸው ይህን ብቃት መድገም ይቸግራቸዋል በማለት ነው፡፡ ቀጣይ የእግር ኳስ ህይወታቸውን ወደፊት የምናየው ቢሆንም በውድድር ዓመቱ ያሳዩት ብቃት ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡

## ምርጥ አንጋፋ ተጫዋቾች

### ሙሉአለም ረጋሣ

ሙሉአለም አሁንም ታላቅ አማካይ እንደሆነ ለማረጋገጥ የዘንድሮውን የመድን ጨዋታዎች መመልከት ይበቃል፡፡
ሙሉአለም ተጠባባቂ ሆኖ በሚጀምርባቸው ጨዋታዎች የኳስ ቁጥጥር ብልጫ የሚወሰድበት የአስራት ኃይሌው መድን በሁለተኛው ግማሽ ሙሉአለምን ቀይሮ ሲያስገባ ሌላ መልክ ይኖረዋል፡፡ እድሜው እየገፋ ሲሄድ በአካል ብቃቱ ረገድ እየደከመ ቢመጣም ቦታውን ጠብቆ በመጫወት፣ እንዳስፈላጊነቱ ረጅም እና አጭር ኳሶችን በማቀበል እና የቡድኑን ፍጥነት በመቆጣጠር ረገድ አሁንም የሊጉ ምርጥ አማካይ ነው ማለት ይቻላል፡፡


ሙሉአለም ረጋሣ
ከፕሪምየር ሊግ ዋንጫ ድል በኋላ

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### አንዱአለም ንጉሴ

‹‹አቤጋ›› አበቃለት ሲባል በድጋሚ ተወልዷል፡፡ ዘንድሮ 3 ግቦች ብቻ ቢያስቆጥርም በተደጋጋሚ መጎዳቱ እና ያስቆጠራቸው ግቦች ለሀዋሳ ከነማ አስፈላጊነታቸውን ስናስብ በእርግጥም አንዱአለም ንጉሴ እድሜ ማለት ‹‹ቁጥር›› ብቻ እንደሆነ ማስረጃ ይሆነናል፡፡

## ክስተት ቡድን

### ወላይታ ዲቻ

አምና የብሄራዊ ሊግን ዋንጫ በማንሳት ወደ ፕሪምየር ሊግ ያደገው ወላይታ ዲቻ ዘንድሮ ባደረጋቸው 13 ጨዋታዎች 18 ነጥቦችን በመሰብሰብ በደረጃው ሠንጠረዥ 5ኛ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ዲቻ በመጀመሪያ ሳምንት የሊግ ጨዋታ ባልተጠበቀ ሁኔታ ንግድ ባንክን 4-0 ከረታ በኋላ ያደረጋቸውን 7 ቀጣይ ጨዋታዎች በሙሉ በአቻ ውጤት ያጠናቀቀ ሲሆን ከነዚህ ጨዋታዎች ውስጥ 3ቱን የክለቡ ዋና ሜዳ የሆነው የቦዲቲ ስታዲየም እድሳት ስራ ባለመጠናቀቁ ምክኒያት በሐዋሳ ስታዲየም ለማድረግ ተገዷል፡፡ የቦዲቲ ስታዲየም ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ዲቻ በ11ኛው ሳምንት በውድድር ዓመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በሜዳው ባደረገው ጨዋታም ከ50,000 በላይ በሚሆኑ ደጋፊዎቹ ታግዞ መከላከያን 1-0 ለማሸነፍ ችሏል፡፡ ከ15 ቀን በኋላም በሁለተኛው ሳምንት ተስተካካይ ጨዋታ ቅዱስ ጊዮርጊስን አዲስ አበባ ላይ 2-1 በማሸነፍ የዘንድሮው ቅዱስ ጊዮርጊስን የሊግ እና የሲቲ ካፕ ያለመሸነፍ ጉዞ መግታት ችሏል፡፡ ዲቻ ባለፉት ሁለት የውድድር ዘመናት በብሄራዊ እና ፕሪምየር ሊግ ባደረጋቸው ጨዋታዎች አልተሸነፈም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለፉት ሶስት አመታት በሁሉም ውድድሮች በሜዳቸው የተሸነፉት አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ የቦዲቲ ስታዲየም እድሳት እና ደረጃውን የማሻሻል ስራ መጠናቀቅ ክለቡ በቀጣይ ለሚያደርጋቸው ጨዋታዎች ብርታት የሚሰጠው ነው፡፡ እንደ ዲቻ ሁሉ ዘንድሮ ፕሪምየር ሊጉን የተቀላቀለው ዳሽን ቢራ ብዙ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ታዋቂ ተጫዋቾችን ቢያስፈርምም ውጤት ሊቀናው አልቻለም፡፡ በአንፃሩ በአካባቢው ያሉ ተሰጥኦ ያላቸውን ልጆች ከብሔራዊ ሊግ በአማካይ 150,000 ብር በማውጣት ከገዛቸው ተጫዋቾች ጋር በማዋሀድ የቀረበው ወላይታ ዲቻ በሊጉ የተሻለ ነገር ማሳየት ችሏል፡፡ ይህም በአካባቢው ያለውን እምቅ የእግር ኳስ አቅም የሚያሳይ ነው፡፡ ዲቻ ምናልባትም ወደፊት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቀዳሚ ጥያቄ የሆነው የተተኪዎች ችግርን የሚቀርፍ መልስ ሊሰጠን ይችላል፡፡

## ትልቁ ውድቀት

### ዳሽን ቢራ

አምና በብሄራዊ ሊግ ውደድር ፍፃሜ በወላይታ ዲቻ በመሸነፍ ሁለተኛ ሆነው ያጠናቀቁት ዳሽኖች ክረምቱን በዝውውር መስኮቱ ለ14 ተጫዋቾች ግገር 12 ሚሊዮን ብር በማውጣት ከግብ ጠባቂ እስከ አጥቂ ድረስ በርካታ ተጫዋቾችን በማስፈረም እና ቡድን በመገንባት ስራ ተጠምደው አሳልፈዋል፡፡ ከቀድሞው መብራት ሐይል እና ውሀ ስፖርት ናይጄሪያዊ ግብ ጠባቂ ፌቮር ኢማኑኤል፣ የብሄራዊ ቡድኑ ተከላካይ አይናለም ሐይሉ፣ አማካዩ አስራት መገርሳ፣ አጥቂ መስመር ላይ እስከሚሰለፈው የናታን ከበደ ድረስ የዘለቀው የዝውውር መረባቸው ግን ውጤትን ሊያመጣላቸው አልቻለም፡፡ በአሠልጣኝ መኮንን ገብረዮሐንስ እየተመራ የውድድር ዓመቱን የጀመረው ዳሽን ቢራ ውጤት በማጣቱ ኋላ ላይ የቀድሞው የኢትዮጵያ ቡና ተጫዋች ካሊድ መሐመድ ቡድኑን ቢረከብም ይህ ነው የሚባል ለውጥ ሊያስመዘግብ አልቻለም፡፡ በፕሪምየር ሊጉ ያስቆጠሩት የመጀመሪያ ጎል ከ9 ጨዋታዎች በኋላ የተገኘ መሆኑ የውድድር ዓመቱ ለዳሽን ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በሂደት ቡድኑ እየተዋሃደ እንደሆነ ፍንጭ የሚሰጡ ምልክቶች ቢታዩም እንዳለው ስብስብ ግን ላለመውረድ ከመጫወት ይልቅ የዋንጫ ፉክክሩ ዋንኛ ተዋናይ መሆን ይጠበቅበት ነበር፡፡ ዳሽን እንዳለው የገንዘብ አቅም ወደፊት ምርጥ ክለብ መገንባት የሚችል ቢሆንም በመጀመሪያ ግን የክለቡን አመራር በእግር ኳሱ ሰፊ እውቀት እና ልምድ ላላቸው ሰዎች መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ድንቅ የቡድን አቋም

### ቅዱስ ጊዮርጊስ 2-0 መብራት ኃይል

የፈረሰኞቹ ደጋፊዎች በክለባቸው ውጤታማነት ሁልጊዜም ቢደሰቱም ከመብራት ኃይል ጋር በተደረገው ጨዋታ ያህል የተደሰቱበትን ወቅት ለማስታወስ በርካታ አመታትን ወደኋላ መጓዝ ይጠበቅብናል፡፡ በጨዋታው ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመጀመርያው ደቂቃ ጀምሮ በውብ ጨዋታ በርካታ የግብ እድሎችን የፈጠረ ሲሆን የቡድኑ ፈጣን የማጥቃት ጨዋታ በርካቶችን ከመቀመጫ ቁጭ ብድግ ያደረገ ነበር፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ አዳነ ግርማ እና ኡመድ ኡክሪ ባስቆጠሩት ሁለት ግቦች ያሸንፍ እንጂ በርካታ ሙከራዎችን የግቡ ቋሚ እና አግዳሚ ሲመልሱባቸው ግብ ጠባቂው ቢንያም ተፈራ ለማመን የሚከብዱ ኳሶችን ግብ ከመሆን ታድጓቸዋል፡፡ ይህ ጨዋታ የማርት ኑይን አዲስ የስራ ዘመን ጅማሮ ተስፋዎች ያሳየ ሲሆን በርካታ የእግር ኳስ አፍቃሪያን ጨዋታውን በስታዲየም በመገኘት አለመመልከታቸው ቅር ያሰኛል፡፡

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### ቅዱስ ጊዮርጊስ 1-2 ወላይታ ዲቻ

ሁለቱ ቡድኖች እስከሚገናኙበት ጊዜ በውድድር ዓመቱ አንድም ጨዋታ አልተሸነፉም ነበር፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያደረጋቸውን ጨዋታዎች በሙሉ በአሸናፊነት ተወጥቶ የነበረ ሲሆን ዲቻ ግን ብዙ ጨዋታዎቹን በአቻ ውጤት አጠናቋል፡፡ ጊዮርጊስ ዘንድሮ እንዳሳየው ጥንካሬ ጨዋታውን እንደሚያሸንፍ ቅድመ ግምት ቢሰጠውም ዲቻ በመከላከሉ ረገድ ጥሩ በመሆኑ

ቢያንስ የጊዮርጊስን የማሸነፍ ጉዞ ሊገታው ይችላል የሚል አስተያየት በብዙዎች ሲሰጥ ነበር፡፡ በጨዋታው የመጀመሪያ አጋማሽ ኡመድ ኡክሪ ላይ በተሰራው ጥፋት ምክኒያት የተገኘውን የቅጣት ምት አበባው ቡጣቆ ሲመታ ኳሱ የዲቻ የተከላካይ ግንብን በመግጨት አቅጣጫ ቀይራ ከመረብ ላይ አረፈች፡፡ በቅዱስ ጊዮርጊስ 1-0 መሪነትንም የመጀመሪያው ግማሽ ተጠናቀቀ፡፡ ከእረፍት መልስ አበባው ቡጣቆ የዲቻው አጥቂ ባዬ ገዛኸኝን በሳጥኑ ውስጥ በመጥለፉ የተገኘውን ፍፁም ቅጣት ምት አሸናፊ ሽብሩ በአግባቡ በመጠቀም ዲቻን አቻ አደረገ፡፡ በጨዋታው መጠናቀቂያ አካባቢ ጊዮርጊሶች አሸናፊ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ግብ ለማግኘት ተጭነው ቢጫወቱም የኋላ መስመራቸውን ለመልሶ ማጥቃት አጋልጠዋል፡፡ ዲቻዎችም በዚሁ የአጨዋወት ዘዴ ያገኙትን አጋጣሚ የንግድ ባንኩ የግራ ተከላካይ መሐሪ መና ታናሽ ወንድም የሆነው እሸቱ መና በግሩም አጨራረስ ወደ ግብ በመቀየር ሙሉ 3 ነጥብ ይዘው እንዲወጡ አስችሏል፡፡ በጨዋታው የዲቻው አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ የተገበረው አጨዋወት ውጤታማ ያደረገው ሲሆን ተጫዋቾቹም ያሳዩት ታክቲካል ዲሲፕሊን ድንቅ ነበር፡፡

### ኢትዮጵያ ቡና 3-1 መከላከያ

ቡና ዘንድሮ ካደረጋቸው ጨዋታዎች ይበልጥ በዚህ ጨዋታ ድንቅ እንቅስቃሴ ለማድረግ ችሏል፡፡ ቡናዎች በ4-3-3 አሰላለፍ ፋሲካ አስፋው፣ ዳዊት እስጢፋኖስ እና መስዑድ መሐመድን በመሐል ሜዳ በማጣመር የተጫወቱ ሲሆን አስቻለው ግርማ፣ ዳዊት እስጢፋኖስ እና ኤፍሬም አሻሞ ባስቆጠሯቸው ግቦች ሲመሩ የቆዩ ቢሆንም የቀድሞው የቡና አጥቂ መድሃኔ ታደሰ ለመከላከያ የማስተዛዘኛውን ግብ አግብቶ ጨዋታው 3-1 ተጠናቋል፡፡ በጨዋታው የኢትዮጵያ ቡና የመሐል ሜዳ እንቅስቃሴ ግሩም የነበረ ሲሆን ዳዊት እና መስዑድ ያደርጓቸው የነበሩት የአንድ-ሁለት ቅብብሎች ለመከላከያ ተጫዋቾች ፈታኝ ነበሩ፡፡ የመሐል ተከላካዩ ቶክ ጀምስ ማናዬ ፋንቱን በቀላሉ የተቆጣጠረበት መንገድ፣ የፊት አጥቂው ቢንያም አሠፋ ሲያደርጋቸው የነበሩት እንቅስቃሴዎች ሁሉ በዕለቱ የተሳኩ ነበሩ፡፡ ቡድኑ በዚህ ጨዋታ ያደረገውን እንቅስቃሴ ሳይዋዥቅ በቀጣይነትም ማስቀጠል ከቻለ ጥሩ ተፎካካሪ ይሆናል፡፡

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

ደደቢት 4-2 መብራት ሐይል
ደደቢት 4-0 ወላይታ ዲቻ

## ምርጥ የግል አቋም


### ኡመድ ኡክሪ - ቅዱስ ጊዮርጊስ 3-0 መከላከያ

ኡመድ በጨዋታው የቀድሞ ክለቡ ላይ ምህረት አልባ ሆኗል፡፡ በተደጋጋሚ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ የግብ ክልል በመድረስ ሲያስጨንቁ ያመሹት መከላከያዎችን በግሉ ድንቅ ብቃት አሸንፏቸው ወጥቷል፡፡ በጨዋታውም ሁለት ድንቅ ግቦች አስቆጥሯል፡፡ ኡመድ ያሳየው አቋም ምናልባትም በእግር ኳስ ህይወቱ ካሳየን እጅግ ድንቅ አቋሞች አንዱ ሳይሆን አይቀርም፡፡

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### ሳምሶን ጥላሁን - ደደቢት 1-0 ሙገር ሲሚንቶ

ጨዋታው ተመጣጣኝ እና አሰልቺ ነበር፡፡ እንደውም ሙገር ሲሚንቶዎች የተሻለ የግብ ማግባት አጋጣሚዎችን ፈጥረዋል፡፡ የጨዋታው 2/3ኛ ክፍለ ጊዜ ያለግብ የዘለቀው ጨዋታ በቅፀበት የተለወጠው ሳምሶን ጥላሁን በድንቅ ሁኔታ ባስቆጠራት ግብ ነው፡፡ ሳምሶን ግቧን ከማስቆጠሩ በተጨማሪ በደደቢት በኩል ሊጠቀስ የሚችል ድንቅ አገልግሎት አበርክቷል፡፡




### ዳዊት እስጢፋኖስ - ቡና 1-1 ንግድ ባንክ

በሊጉ ሶስተኛ ሳምንት በተደረገው ጨዋታ ንግድ ባንኮች ቡናን ተጭነው ተጫውተዋል፡፡ በመጀመሪያው ግማሽ በርካታ የግብ አጋጣሚዎች መፍጠር ቢችሉም አንድም ግብ ማስቆጠር አልቻሉም፤ ለዚህም ናይጄሪያዊው አጥቂ ፊሊፕ ዳውዚ አብዛኛዎቹን ዕድሎች ባለመጠቀም ዋነኛ ተወቃሽ ነው፡፡ ዳዊት በዚህ ጨዋታ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው መሐል ሜዳውን በማደራጀትና ጥሩ ኳሶችን ለቡድን ጓደኞቹ በመስጠት ላይ የነበረ ቢሆንም ቡና በመጨረሻው 1/3 ላይ የነበረው እንቅስቃሴ ውጤታማ አልነበረም፡፡ በሁለተኛው አጋማሽ የቀድሞው የቅዱስ ጊዮርጊስ አማካይ ኤልያስ ማሞ ከርቀት አክርሮ በመምታት ለንግድ ባንክ ግሩም ግብ አስቆጠረ፡፡ በግቧ መቆጠር የተደናገጡት ቡናዎች አቻ የሚያደርጋቸውን ግብ ለማግኘት ጥረት ቢያደርጉም በአግባቡ የተደራጀውን የባንክ ተከላካይ ክፍል ሰንጥቀው ለመግባት አልቻሉም፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ዳዊት በቀኝ መስመር ላይ ኳሱን ከተቀበለ በኋላ ወደ መሐል በመግባትና በድንቅ ሁኔታ ሁለት ተጫዋቾችን በማለፍ ምናልባትም ዘንድሮ የዓመቱ ምርጥ ግብ ለመባል ተወዳዳሪ የሆነች ጎል ማስቆጠር የቻለው፡፡ ይህ ጎል ቡና አቻ እንዲሆን ከማስቻሉ በላይ ሌሎች ተጫዋቾች እንዲነቃቁ እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲፈጠርባቸው አድርጓል፤ ምንም እንኳን ጨዋታው በዚያው አቻ ውጤት ቢጠናቀቅም፡፡

### ታደለ መንገሻ - መብራት ኃይል 2-4 ደደቢት

የደደቢቱ አማካይ በእግርኳስ ህይወቱ ለመጀመርያ ጊዜ ሀትሪክ የሰራበት ጨዋታ ነበር፡፡ መብራት ኃይሎች በሁለት አጋጣሚ መምራት ቢችሉም በመጨረሻ እጃቸውን የሰጡት ለደደቢት ሳይሆን ለታደለ መንገሻ ነው፡፡1-0 ሲመራ የነበረው ደደቢት ታደለ ከረጅም ርቀት ባስቆጠራት ድንቅ ግብ አቻ ቢሆኑም ብዙም ሳይቆዩ ግብ ተቆጠረባቸው፡፡ እስከ 83ኛው ደቂቃም ግብ ማስቆጠር ተሳናቸው፡፡ በ83ኛው ደቂቃ ታደለ በግራ እግሩ ከ25 ሜትር አካባቢ በድጋሚ ድንቅ ግብ አስቆጥሮ የጨዋታውን መንፈስ ለወጠው፡፡ ከግቧ መቆጠር በኋላም ደደቢቶች በመብራት ኃይል ተከላካዮች ላይ ጫና ፈጥረው መንቀስ ጀመሩ፡፡ በ89ኛው ደቂቃ ላይ ሽመክት ጉግሳ ግብ አስቆጥሮ ደደቢትን ከተመሪነት ወደ መሪነት ለወጠ፡፡ በመጨረሻም በ91ኛው ደቂቃ የተገኘውን ፍፁም ቅጣት ምት ታደለ ወደ ግብ ቀይሮት ደደቢት 4-2 አሸነፈ፡፡ በጨዋታው ለተከሰቱት ድራማዎች በሙሉ የ16 ቁጥሩ ልጅ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡

## ምርጥ ጨዋታ

### ደደቢት 2-2 መከላከያ

ፕሪምየር ሊጉ ሁልጊዜ ማየት የሚፈልገው አይነት ጨዋታ ነበር፡፡ በሊጉ 8ኛ ሳምንት የተደረገው ይህ ጨዋታ በውድድር ዓመቱ እስካሁን ያየነው ምርጥ ጨዋታ ነው፡፡ መከላከያ ከዚህ ጨዋታ በፊት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ባደረገው የ7ተኛ ሳምንት ጨዋታ የፈጠራቸውን በርካታ የግብ እድሎች ወደ ግብ መቀየር ተስኖት 3-0 የተሸነፈ ሲሆን ደደቢት በበኩሉ በወቅቱ በደረጃ ሠንጠረዡ ግርጌ ላይ የነበረውን ኢትዮጵያ መድንን በዳዊት ፍቃዱ ጎል ሲመራ ቆይቶ በሁለተኛው ግማሽ በተቆጠሩበት 2 ግቦች ባልተጠበቀ ሁኔታ 2-1 ተሸንፎ ነበር ወደዚህ ጨዋታ ያመራው፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ጨዋታውን ባሸናፊነት ለመደምደም የማጥቃት አሠላለፍ ይዘው የገቡ ሲሆን ግብ በማስቆጠሩ ረገድ ደደቢቶች ቀዳሚ ነበሩ፤ በዳዊት ፍቃዱ አማካኝነት፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ ሲሳይ ደምሴ ያገኘውን ፍፁም ቅጣት ምት በአግባቡ በመጠቀም መከላከያን አቻ አደረገ፡፡ በማጥቃት አጨዋወታቸው የቀጠሉት ደደቢቶች በግብ ክልሉ አካባቢ ያገኙትን ቅጣት ምት የቀድሞው የቅዱስ ጊዮርጊስ አማካይ ሳምሶን ጥላሁን በቀጥታ ወደ ጎል በመምታት አስቆጠረ፡፡ በጨዋታው የደደቢት አሸናፊነት የተቃረበ

# ኢትዮ-ሊግ
# ልዩ ዘገባ



## የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ኮከብ ግብ አግቢዎች

| | |
|---|---|
| 1. ሑመድ ሑክሪ (ቅዱስ ጊዮርጊስ) | 10 |
| 2. ፊሊፕ ዳውዚ (ንግድ ባንክ) | 6 |
| ኤፍሬም አሻሞ (ኢትዮጵያ ቡና) | |
| 3. ተመስገን ተክሌ (ሐዋሳ ከነማ) | 5 |
| አዳነ ግርማ (ቅዱስ ጊዮርጊስ) | |
| መስፍን ኪዳኔ (ደደቢት) | |
| ዳዊት ፍቃዱ (ደደቢት) | |
| 4. ቢንያም አሠፋ (ኢትዮጵያ ቡና) | 4 |
| አኪም አኬንዳ (ሙገር ሲሚንቶ) | |
| ታደለ መንገሻ (ደደቢት) | |
| 5. አንዱአለም ንጉሴ (ሐዋሳ ከነማ) | 3 |
| ተመስገን ዱባ (አርባምንጭ) | |
| በረከት ይስሃቅ (መብራት ሐይል) | |
| ፍፁም ገብረማርያም (ቅዱስ ጊዮርጊስ) | |
| ኤሊያስ ማሞ (ንግድ ባንክ) | |
| አሸናፊ ሽብሩ (ወላይታ ዲቻ) | |
| ዳዊት እስጢፋኖስ (ኢትዮጵያ ቡና) | |
| ፍሬው ሰለሞን (መከላከያ) | |
| ሲሳይ ደምሴ (መከላከያ) | |
| ሄኖክ ኢሳያስ (ደደቢት) | |

ቢመስልም የመከላከያው ፍሬው ሰለሞን ያሻማውን የማዕዘን ምት የደደቢቱ ጋናዊ ተከላካይ አዳሙ መሐመድ በራሱ ጎል ላይ በማስቆጠሩ ጨዋታው 2-2 ተጠናቋል። በጨዋታው 90ኛ ደቂቃ ማናዬ ፋንቱ 1 ለ 1 ከደደቢቱ ግብ ጠባቂ ሲሳይ ባንጫ ጋር ተገኛኝቶ ለመከላከያ 3 ነጥብ የሚያስገኝ ግብ አስቆጠረ ተብሎ ሲጠበቅ ሲሳይ በግሩም ሁኔታ ሊያከሽፍበት ችሏል። አዝናኝ፣ ከሁለቱም ቡድኖች የተደረጉ በርካታ የግብ ሙከራዎች፣ ድንቅ አጨራረስ፣ ምርጥ ቅጣት ምት፣ ፍስት እና ውበት፣ 4 ግቦች እና እስከመጨረሻው ድረስ የዘለቀ የመሸናነፍ ፉክክር በጨዋታው ላይ ታይቷል። በሊጉ ሁለም ጨዋታዎች እንደዚህ ግጥሚያ ቢሆኑ ያስባለ ድንቅ ጨዋታ……።

## ተወዳጅ ቅፅበት (Favourite Moment)

### ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመብራት ሐይል
### የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋቾች የደስታ አገላለፅ

ቅዱስ ጊዮርጊስ መብራት ኃይልን 2-0 ባሸነፈበት የ4ኛ ሳምንት የፕሪምየር ሊግ ጨዋታ ኡመድ ኡክሪ ካስቆጠራት የመጀመሪያ ግብ በኋላ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋቾች ያሳዩት የደስታ አገላለፅ የ1994ቱ የቤቤቶ ማንሆ እና ሮማርዮን የደስታ አገላለፅ ያስታወሰ ነበር። በዚያች ዕለት የወንድ ልጅ አባት ወደሆነው ምክትል አሠልጣኝ ፋሲል ተካልኝ በመሄድ ህፃን ልጅን የማስተኛት (እሹሩሩ) የደስታ አገላለፅ በማሳየት ፋሲልን 'እንኳን ደስ ያለህ' ያሉበት ቅፅበት በኛ አስተያየት የግማሽ ውድድር ዓመቱ ተወዳጅ ቅፅበት ነው።

## በአስደናቂ ሁኔታ መመለስ (Best Comeback)

### የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስደናቂ መሻሻል

በፕሪምየር ሊጉ የረጅም ጊዜ ልምድ ባላቸው ተጫዋቾች የተነባው ንግድ ባንክ የመጀመሪያ ሳምንት ጨዋታ ከብሄራዊ ሊግ ባደገው ወላይታ ዲቻ በአስደንጋጭ ሁኔታ 4-0 መሸነፉ ብዙዎችን ያነጋገረ ጉዳይ ነበር። በዚህ ጨዋታ ምርጥ እንቅስቃሴ ላደረጉት ዲቻዎች በዕለቱ ባዬ ገዛኸኝ፣ ዮሴፍ ደንጊቶ፣ ተስፋዬ መላኩ እና ሳምሶን ኮሌቻ በደካማው የንግድ ባንክ የተከላካይ መስመር ብዙም ሳይቸገሩ ግቦቹን አስቆጥረዋል። ከጨዋታው በኋላም የስፖርት ቤተሰቡ በባንክ የዘንድሮ የሊግ ውጤት ላይ ያለውን ጥርጣሬ ሲገልፅ ቆይቷል። ይህን ጨዋታ እንደ ማንቂያ ደወል የተጠቀሙበት ንግድ ባንኮች ግን በቀጣይ ካደረጓቸው 6 ጨዋታዎች ውስጥ 4ቱን አሸንፈው በ2ቱ አቻ በመውጣት ለማገገም ችለዋል። ከዲቻ በኋላ ባደረጉት ጨዋታዎች አንዴ ብቻ ተሸንፈዋል፤ ባስመዘገቡት ውጤትም በደረጃ ሠንጠረዡ በሶስተኛነት ተቀምጠዋል። የፀጋዬ ኪዳነማርያም ቡድን በሁለተኛው የውድድር ዓመት አጋማሽ ይህን መልካም ውጤት ለማስቀጠል ጥረት እንሚያደርግ ይጠበቃል።



ፍፁም ገብረማርያም ከአዲስ አበባ ኮከብ ግብ አግቢ እና ተጫዋችነት ሽልማት በኋላ

## ሊጠቀሱ የሚገባቸው

### ፍፁም ገብረማርያም

ፍፁም ገብረማርያም ከጉዳተኛነት ወደ አስደናቂ ግብ አግቢነት የተለወጠበት ፍጥነት አስገራሚ ነው። ከወራት በፊት ለህክምና ባመራበት ዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት እድል አግኝቶ በዛው ሊቀር እንደሚችል ሲወራበት የነበረው የሙገር ሲሚንቶ ውጤት ከ26 ቀናት በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ቅዱስ ጊዮርጊስን ተቀላቅሏል። ከ2 ወራት ጉዳት ሲመለስ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ተቋርጦ የነበረ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ውድድር አጥቂው ወደ አቋሙ እንዲመለስ ዋነኛ አጋጣሚ ሆነለት። በመጀመርያው የምድብ ጨዋታ ተቀይሮ የገባው ፍፁም በቀድሞ ክለቡ ሙገር ሲሚንቶ ላይ ግብ አስቆጥሮ ቅዱስ ጊዮርጊስን ለአሸናፊነት አበቃ። ከዛ በኋላ በተደረጉ 4 ተከታታይ ጨዋታዎች (የፍፃሜውን ጨምሮ) ላይ ሁሉ ግብ በማስቆጠር በአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ታሪክ ብቸኛው ተጨዋች ለመሆን በቃ። ቅዱስ ጊዮርጊስን የዋንጫ ባለቤት እንዲሆን የረዳው ፍፁም የውድድሩ ኮከብ ግብ አግቢ እና ኮከብ ተጫዋች በመሆን አጠናቀቀ። የፍፁም ወቅታዊ አቋም ለተቃራኒ ቡድን ብቻ ሳይሆን ለቡድን አጋሩ ኡመድ ኡክሪም አስፈሪ ይመስላል። በ12ኛው ሳምንት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሐረር ቢራን 5-1 ባሸነፈበት ጨዋታ የጋምቤላውን ተወላጅ ተጠባባቂ ወንበር ላይ አስቀምጠው ግጥሚያውን የጀመሩት ማርት ኖይን በ2 ግቦች ክሷቸዋል። በሁለተኛው ዙር ለማየት ከሚያጓጉት ነገሮች አንዱ ቀጣዩ የጊዮርጊስ አሠልጣኝ እንደ ማርት ኖይ በአንድ አጥቂ የመጠቀም ልምድ ያላቸው ከሆነ በወቅታዊ ድንቅ አቋም ላይ ከሚገኘው ፍፁም እና የሊጉን ኮከብ ግብ አግቢነት ክብር ከሚመራው ኡመድ ለማን ቅድሚያ ሰጥተው እንደሚያሰልፉ መመልከት ነው።

### ኢትዮጵያ ቡና

የዘንድሮው ኢትዮጵያ ቡና በሽግግር ላይ ያለ ቡድን ነው። በክረምቱ 3 ወሳኝ ተከላካዮቹን ጨምሮ በርካታ ተጫዋቾችን አጥቶ እንብዛም በግዢ ላይ አልተሳተፈም። ከዝውውሮች በተጨማሪ በትልቅ ደረጃ የማሰልጠን ልምድ ብዙም የሌለው አሰልጣኝ ጳውሎስ ጌታቸውን የቡድኑ አሰልጣኝ አድርጎ በመሾሙ ከዘንድሮው ኢትዮጵያ ቡና በፍጥነት ውጤት መጠበቅ ያዳግት ነበር። በውድድር አመቱ መጀመርያ ላይ የታየውም ይኸው ነበር። ከወላይታ ድቻ ፣ ንግድ ባንክ ፣ሙገር እና አርባምንጭ ጋር አቻ ሲወጡ በቅዱስ ጊዮርጊስ ተሸንፈው ማሸነፍ የቻሉት ሁለቱን ብቻ ነበር። ብሄራዊ ቡድናችን በቻን ለሚያደርገው ተሳትፎ ፕሪሚየር ሊጉ ሲቋረጥም ኢትዮጵያ ቡና በደረጃ ሰንጠረዡ ወገብ ላይ ነበር። ነገሮች ለኢትዮጵያ ቡና መልካም መሆን የጀመሩት በ11ኛው ሳምንት በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ዳሽን ቢራን 2-1 ሲያሸንፉ ነው። ከዛ ወዲህ ከኢትዮጵያ መድን፣ መከላከያ፣ ደደቢት፣ ሀዋሳ ከነማ እና ሀረር ቢራ ጋር በመደበኛው መርሃ ግብር እና በተስተካካይ ያደረጓቸውን ጨዋታዎች በሙሉ አሸንፈው የ1ኛውን ዙር በ2ኛነት አጠናቀዋል። በሁለተኛው ዙር የመጀመርያዎቹ ጨዋታዎች ቅዱስ ጊዮርጊስ ነጥብ ከጣለ ታላቁ የኢትዮጵያ ደርቢ በውድድር ዘመኑ ለማየት የምንጓጓው ምርጥ ጨዋታ ይሆናል።
መልካም የሁለተኛ ዙር ውድድር እንመኛለን!

የኢትዮጵያ ቡና የተከላካይ መስመር የጀርባ አጥንት የሆነው ቶክ ጀምስ





የደደቢቶቹ ታደለ መንገሻ እና አዳሙ መሐመድ

## የሶከር ኢትዮጵያ የውድድር ዓመቱ ምርጥ ቡድን


**ግብ ጠባቂ**
መክብብ ደገፉ (ወላይታ ዲቻ)

**ተከላካዮች**
መሐሪ መና (ንግድ ባንክ)
ቶክ ጀምስ (ኢትዮጵያ ቡና)
አይዛክ ኢሲንዴ (ቅዱስ ጊዮርጊስ)
ሲሳይ ደምሴ (መከላከያ)

**የተከላካይ አማካዮች**
ኢሳድጃ ዊሊያምስ (ቅዱስ ጊዮርጊስ)
ሳምሶን ጥላሁን (ደደቢት)

**የአጥቂ አማካዮች**
ፍፁው ሰለሞን (መከላከያ)
ዳዊት እስጢፋኖስ (ኢትዮጵያ ቡና)
ታደለ መንገሻ (ደደቢት)

**አጥቂ**
ኡመድ ኡክሪ (ቅዱስ ጊዮርጊስ)



**ተጠባባቂዎች**
ዮሐንስ ሽኩር (ንግድ ባንክ)
ሳልሃዲን ባርጌቾ (ቅዱስ ጊዮርጊስ)
መስዑድ መሐመድ (ኢትዮጵያ ቡና)
ኤሊያስ ማሞ (ንግድ ባንክ)
በኃይሉ አሠፋ (ቅዱስ ጊዮርጊስ)
ኤፍሬም አሻሞ (ኢትዮጵያ ቡና)
ተመስገን ተክሌ (ሐዋሳ ከነማ)

## ኮከብ አሠልጣኝ

**ማርት ኖይ:** ሆላንዳዊው የቅዱስ ጊዮርጊስ አሠልጣኝ ምንም እንኳን የሚመሩት ቡድን በውስጡ በሃገራችን አሉ የተባሉ ምርጥ ተጫዋቾችን ያሰባሰበ ቢሆንም፣ አንዳንዴም ቡድናቸው አይን ሳቢ የሆነ የአጨዋወት ዘይቤ አይከተልም እየተባለ ቢታማም፤ በተመዘገበው ውጤት ላይ ተመርኩዘን ስናየው የሊጉ ምርጥ አሠልጣኝ መሆናቸው ጥያቄ ውስጥ አይገባም:: በሊጉ 11ኛ ጨዋታቸው በወላይታ ዲቻ 2-1 ተሸንፈው የአሸናፊነት ጉዟቸው ቢገታም 10 ተከታታይ የሊግ ጨዋታ ማሸነፍም ሆነ በመጀመሪያው ዙር 13 ጨዋታዎች 36 ነጥብ መሰብሰባቸው በሪከርድነት ተመዝግቧል::

## የውድድር ዓመቱ በምስሎች




አሉላ ግርማ




አስቻለው ግርማ፣ ኤፍሬም አሻሞ፣ ጋቶች ፓኖም

# የውድድር ዓመቱ በምስሎች







# አዲሱ የብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝ ሊመለከቷቸው የሚገቡ 10 አዳዲስ ተጫዋቾች

**የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አዳዲስ ፊቶችን ባለማሳየቱ ሁልጊዜም ይታማል። በአንድ አጋጣሚ የተመረጠ ተጫዋች አቋሙ እና የአካል ብቃቱ ወርዶ እንኳን ከምርጫ አይዘለሉም። ከአንፃራዊ ስኬት እና የቻን ውድቀት በኋላ አዲስ የሚቀጠሩት አሰልጣኝ አይን ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ አዳዲስ ፊቶችን ሶከር ኢትዮጵያ እንዲህ በአጭሩ ታስተዋውቃለች።**



1. ዘላለም ታደሰ
የወላይታ ድቻው አምበል የአስገራሚው ድቻ የተከላከይ ክፍል የጀርባ አጥንት እናመሪ ነው:: የተሟላ የአካል ብቃት ሲሆን የአየር ኳሶች ላይ ያለው የበላይነት ድንቅ ነው:: ፈጣን ባይሆንም የቦታ አጠባበቁ ጥሩ በመሆኑ አጥቂዎች ፈተና አይሆኑበትም:: በድቻ 3-5-2 አሰላለፍ ከሶስቱ የመሃል ተከላካዮች መሃሉን ይዞ የሚጫወተው ዘላለም ፍጥነት እና ወደ ፊት ተጠግቶ የመጫወት ልምዱን ካዳበረታላቅ ተከላካይ ይሆናል::

2. ፍሬው ሰለሞን
የመከላከያው አማካይ ዘንድሮ በሊጉ የማይዋዥቅ ምርጥ አቋም ካሳዩ ተጫዋቾች ውስጥ አንዱ ነው:: 10 ቁጥሩ የአጥቂ አማካይ ከግራ መስመር እየተነሳ ወደ መሀል በመሳብ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ለተቃራኒ ቡድን ተከላካዮች ትልቅ ፈተና ነው:: ፍሬው በ2005 የውድድር ዓመትም ቢሆን ለክለቡ ምናልባትም ከአንዳንድ የብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች የተሻለ ድንቅ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም በሰውነት ቢሻው እምነት ተጥሎበት ሊመረጥ አልቻለም:: ፍሬው በግራ አማካይነት እንዲሁም ከአጥቂ ጀርባ በ10 ቁጥርነት መጫወት የሚችል ሲሆን ቀጣዩ አሠልጣኝ የትኛውንም የአጨዋወት ዘይቤ ቢመርጡ ጠቃሚ ተጫዋች ሊሆንላቸው ይችላል::

3. መክብብ ደገፉ
ግብ ጠባቂው በድቻ ጠንካራ የተከላከይ መስመር ምክንያት ብዙ ባይፈተንም በርካታ ግብ የሚሆኑ ኳሶችን አድኗል:: በራሱ የሚተማመንና ተጣጣፊ ሲሆን ከቁመቱ አንፃር በአየር ኳስ ላይ ያለው ብቃት ጥሩ ነው:: መክብብ ከሌሎች የሃገራችን ግብ ጠባቂዎች በተለየ የትኩረት ችግር የለበትም:: በርካታ ከርቀት የሚሞከሩ ኳሶችን የሚያድነውም ለዚህ ነው:: በግብ ጠባቂዎች የትኩረት ችግር ዋጋ ለከፈለችው ኢትዮጵያ ለስህተት (በአንፃራዊነት) ሩቅ የሆነው መክብብ ጥሩ መፍትሄ ይሆናታል:: በቁጥራዊ መረጃዎችም ሆነ በሜዳ ላይ እንቅስቃሴ ገምግሞ መክብብን ከብሄራዊ ቡድን ምርጫዎች መዝለል የማይታሰብ ነው::

4. ዮሀንስ ሽኩር
በውድድር ዓመቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ዋና ግብ ጠባቂዎች የሆኑት ሲሳይ ባንጫ እና ጀማል ጣሰውን በብዛት ልናያቸው አልቻልንም:: ጀማል ባጋጠመው ጉዳት ምክኒያት አብዛኛዎቹ የቡና ጨዋታዎች ላይ ለመሰለፍ ባለመቻሉ በጌቱ ተስፋዬ ተተክቷል:: ሲሳይ ደግሞ በደደቢት በአቋም መዋዠቅ ወይም ከአሰልጣኙ ጋር በፈጠረው አለመግባባት ይሁን በማይታወቅ ምክኒያት የታሪኬ ጌትነት ተጠባባቂ ለመሆን ተገዷል:: በዚህ ምክኒያት በብሔራዊ ቡድኑ የተፈጠረውን ክፍተት የንግድ ባንኩ ግብ ጠባቂ በበቂ ሁኔታ የመሸፈን ብቃት አለው:: ንግድ ባንክ ዘንድሮ የሚመርጠው በማጥቃት ላይ ያተኮረ የአጨዋወት ዘይቤ ለተከላካይ ክፍሉን በቂ ሽፋን መስጠት ባልቻለባቸው አጋጣሚዎች ዮሀንስ በርካታ የማግባት ሙከራዎችን ለማዳን እና ክለቡን ከሽንፈት ለመታደግ ችሏል:: ንግድ ባንክ በሊጉ 3ኛ ደረጃ ላይ እንዲቀመጥ ትለቁን አስተዋፅኦ ካበረከቱ ተጫዋቾች አንዱ ሲሆን ያሳየው አቋምም ለብሔራዊ ቡድን ለመጠራት በቂ ነው::

5. ዮሴፍ ዴንጌቶ
ድንቅ 10 ቁጥር ነው:: የድቻ የማጥቃት እንቅስቃሴዎች በሙሉ የሚያልፉት በዮሴፍ በኩል ነው:: ምናልባትም በሚገባ ሽፋን ስለሚያገኝ ነፃነቱን በሚገባ ተጠቅሞበት ይሆናል:: ጥሩ አይን ያለው ሲሆን ውሳኔ ላይም ፈጣን ነው:: በጉልበት ላይ ካመዘኑት የድቻ ተጫዋቾች ይልቅ በቴክኒክ የበለፀገው ዮሴፍን ያገኙትን እድል በመጠቀም በኩል ከማይታሙት የብሄራዊ ቡድን አጥቂዎች ጀርባ ሲጫወት መመልከት ያጓጓል::

6. እሸቱ መና
በጣም ፈጣን፣ ጠንካራ እና በመስመር አማካይነትም ሆነ በመስመር ተከላከይነት መሰለፍ የሚችል ተጫዋች ነው:: ዘንድሮ በወላይታ ድቻ የቀኝ መስመር ላይ እይታ ውስጥ የገባው እሸቱ በተለይም በ3-5-2 የቀኝ አማካይ ሁኖ ሲሰለፍ ጎልቶ መውጣት ይችላል:: ለማጥቃት ወደ ፊት መሄድ ቢያዘወትርም በፍጥነት የተወውን ክፍት ቦታ በመሸፈኑ ረገድ ምናልባትም ከሊጉ የመስመር ተከላከዮች የተሻለ ነው:: ስዩም ተስፋዬ ወደ አቋሙ እየተመለሰ ቢሆንም፣ አሉላ ግርማ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቋሚ ተሰላፊነቱን ባለማስከበሩና ሞገስ ታደሰ ተደጋጋሚ ጉዳት በማስተናገዱ ለብሄራዊ ቡድን መመረጡ የማይቀር ነው:: የሚያሻግራቸውን ኳሶች ጥራት ካሻሻለ በብሄራዊ ቡድኑ የቀኝ እና የግራ ተከላካይ ክፍል ሁለቱን ወንድማማቾች እሸቱ መና እና መሃሪ መናን በቋሚ አሰላለፍ ውስጥ የምናይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም::

7. ተመስገን ዱባ
ተመስገን ዘንድሮ የአርባምንጭ ከነማ ኮከብ ተጫዋች ነው:: ከቀኝ መስመር እየተነሳ ለቡድን ጓደኞቹ የግብ ዕድል ከመፍጠሩ በተጨማሪ ወደ ፊት በመሄድ ግቦችን ለማስቆጠር ችሏል:: አምና በዚህ ቦታ ለአርባምንጭ ጥሩ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረው እንዳለ ከበደ ወደ ሲዳማ ቡና ቢያመራም ተመስገን የተፈጠረውን ክፍተት በሚገባ ሸፍኗል:: በሁለተኛው ዙር ጨዋታዎች እስካሁን ያሳየንን ብቃት መድገም ከቻለ በቅርቡ ብሔራዊ ቡድን ማሊያ ልናየው እንችላለን::

8. አሸናፊ ሽብሩ
አጨዋወቱ፣ የመጫወቻ ቦታው እና ቁመቱ ከአስራት መገርሳ ጋር ይመሳሰላል:: የተረጋጋ፣ ኳስን ማደራጀት የሚችል፣ ጉልበቱን

የሚጠቀምና ቡድን መምራት የሚችል አማካይ ነው፡፡ አሸናፊ በድቻ ዘንድሮ ድንቅ የውድድር ዘመን እያሳለፈ ሲሆን የቡድንን ፍጥነት የሚቆጣጠር ተጫዋች በፅኑ የሚፈልገው ብሄራዊ ቡድናችን የድቻውን 23 ቁጥር ሊመለከተው ይገባል፡፡

9. ሔኖክ ኢሳያስ

የደደቢቱ 23 ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ብቃቱን እያሳደገ የሚገኝ ተጫዋች ነው፡፡ በተለይ የውድድር ዘመኑ እየገፋ ሲመጣ ከጨዋታ ጨዋታ የተሻለ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ ክለቡ ባደረጋቸው የመጨረሻ 5 ጨዋታዎች 3 ግቦችን ማስቆጠር መቻሉ ለዚህ ማሳያ ነው፡፡ የደደቢት ወጣት ቡድን ውጤት የሆነው አማካይ በትልቅ ደረጃ የመጫወት ልምዱን እያካበተ ሲመጣ የቡድኑ መሀል ሜዳን በብቃት የመምራት አቅም ይኖረዋል፡፡ በዕድሜው ገና ወጣት እንደመሆኑ የብሔራዊ ቡድኑ የወደፊት ተስፋ ከሆኑ ተጫዋቾች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

10. ሳምሶን ጥላሁን

በ2005 ለቅዱስ ጊዮርጊስ ከወጣት ቡድኑ አድጎ ከፕሪምየር ሊግ እስከ ኮንፌዴሬሽንስ ካፕ ድረስ ጥሩ ግልጋሎት የሰጠው ወጣቱ አማካይ ዘንድሮ ለደደቢት አስገራሚ አቋም እያሳየ ይገኛል፡፡ በተከላካይ አማካይ ስፍራ ከጋናዊው ሻይቡ ገብርኤል ጋር ከፈጠረው የሰመረ ጥምረት በተጨማሪ ከረጅም ርቀት በመምታት እና ከቅጣት ምት ግቦችን ማስቆጠር ችሏል፡፡ ደደቢት ይህን ተጫዋች ከሌላው የጊዮርጊስ ወጣት ቡድን ውጤት መስፍን ኪዳኔ ጋር ያዘዋወረበት ሂደት ሊደነቅ የሚገባው ነው፡፡ ሳምሶን እያሳየ ከሚገኘው እንቅስቃሴ እና በዕድሜው ወጣት መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ያለጥርጥር አንድ ቀን ለብሔራዊ ቡድኑ ሲጫወት እናያዋለን፡፡



ታሚ ኩፔ

# ዝውውር እና የተጫዋቾች መጥፋት?

የኢትዮጵያ እግርኳስ ወደኋላ ከቀረባቸው ነገሮች አንዱ የዝውውር ሲስተሙ ነው፡፡ ክለቦች ተጫዋቾች እና አሰልጣኞችን የሚያዘዋውሩት በዘፈቀደ ሲሆን የፌዴሬሽኑ ስራ እና ሀላፊነትም የተዘዋወሩ ተጫዋቾችን መመዝገብ ብቻ ይመስላል፡፡ በኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ ተጫዋቾችን ለማዘዋወር ክለቦች ከወኪሎች ጋር መደራደር የማይታሰብ ነው፡፡ ኮንትራት ያለውን ተጫዋች ክለቦች ከክለቦች ጋር ተደራድረው የሚያስፈርሙባቸው አጋጣሚዎች ለ0 የቀረቡ ናቸው፡፡ ተጫዋቾች ኮንትራታቸውን ሲጨርሱ ከፈለጉት ክለብ ጋር በፊርማ ተስማምተው ከመፈረም በዘለለ ክለቦቹ የተጫዋቾችን ቆይታ የሚያረጋግጡበት ምንም ዋስትና አይኖራቸውም፡፡ ዘንድሮ በካሜሩናዊው ታሚ ኩፔ እና ታፈሰ ሰለሞን ላይ የተመለከትነውም የዝውውር ባህላችን ኋላ ቀርነትን የተመለከትነው ነው፡፡

በአመቱ መጀመርያ ከመብራት ኃይል 650ሺህ ብር ተቀብሎ ለእረፍት ወዳመራበት በዛው ቀልጦ የቀረው ታሜ ኩፔን ስንመለከት መብራት ኃይል በተጫዋቹ ላይ ቀድሞ መስራት የነበረበትን ባለመስራቱ ለኪሳራ ተዳርጓል፡፡ መብራት ኃይል መጀመርያውኑ በፊፋ የተመዘገበ ህጋዊ ወኪልን ተጠቅሞ ቢያስፈርም ኖሮ ይሄ ባልተከሰተ ነበር፡፡ ተጫዋቹ ቢጠፋ እንኳን አቅራቢው ወኪል ኃላፊነት ስለሚወስድ ወኪሉን መጠየቅ ይችላል፡፡

ይህ የተጫዋቾች የኮንትራት ጊዜያቸውን ሳያጠናቅቁ መጥፋት ችግር በተለይ አንዴ ከሃገሪቱ ከወጡ ተመልሰው በማይመጡ የውጪ አገር ዜጋ የሆኑ ተጫዋቾች ላይ ሊታይ ስለሚችል በጊዜ መፍትሄ መፈለግ ያስፈልጋል፡፡



# የወላይታ ድቻ መምጣት ለአዲስ አበባ ቡድኖች ጠቀሜል

ገቢዎቹ ይፋ ባይሆኑም፣ የተረጋገጠ የፋይናንስ ጥናት ባይኖርም በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አንደኛው ዙር የአዲስ አበባ ክለቦች ከስታዲየም የሚያገኙት ገቢ ከሌሎች አመታት የበለጠ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ እንደውም የወላይታ ድቻ ወደ ፕሪሚየር ሊጉ ማደግ የጠቀመው ለሶዶው ክለብ ሳይሆን በሜዳቸው ለሚጫወቱ ቡድኖች ነው፡፡ በአንደኛው ዙር ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ኢትዮጵያ ቡና እና ደደቢት ወላይታ ድቻን ባስተናገዱባቸው ጨዋታዎች የራሳቸውን ደጋፊ ጨምሮ ስታድየሙ ሙሉ ለሙሉ በተመልካች የተሞላ ሲሆን በርካታ ደጋፊ የሌላቸው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮጵያ መድን እና መከላከያ (በኢትዮጵያ ዋንጫ) ወላይታ ዲቻን ባስተናገዱባቸው ጨዋታዎች ላይም የስታዲየሙ አመዛኝ ክፍል በተመልካች ተሞልቷል፡፡ ከዚህ ቀደም እንደ ዲቻ ሁሉ የበርካታ ደጋፊዎች ባለቤት የሆነው አርባምንጭ ከነማ ፕሪምየር ሊጉን ሲቀላቀል በተመሳሳይ የክለቦች የስታዲየም ገቢ እንደጨመረ ይታወሳል፡፡ ከስታዲየም የሚገኘው ገቢ ለራሱ በመቶኛ አስቀርቶ በእለቱ ባለሜዳ ሆኖ ለተጫወተው ክለብ የሚያከፋፍለው ፌዴሬሽንም በድቻ መምጣት ከፍተኛ ገቢ ያገኛል፡፡ በጨዋታ ቀን ከስታዲየም መግቢያ ከሚያገኙት ገቢ እና ድርጅቶች ከሚመድቡላቸው በጀት በስተቀር በተጠና ሁኔታ እግርኳሱን ወደ አትራፊ ቢዝነስነት መቀየር ያልቻሉት ክለቦቻችን (የአዲስ አበባ ክለቦች) ገቢያቸው በመጠኑም ቢሆን ጭማሪ ማሳየቱ መልካም ዜና ነው፡፡




የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋቾች ክለቡ በቅርቡ በቱርክ ያሰራው ማሊያ በሚመረቅበት ጊዜ

# ማሊያ ፣ ብራንድ እና ክለቦቻችን

በኢትዮጵያ እግርኳስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ቢዝነስ፣ ገንዘብ፣ ብራንድ... የሚሉ ቃል ያሉ አይመስልም። በ2006 ግማሽ የውድድር ዘመንም ይህን አለማየታችን አያስገርምም። ሶከር ኢትዮጵያ በዚህኛው እትሟ በማልያ ብራንድ ላይ ትኩረት አድርጋ ክለቦቻችን ወዴት እያመሩ ነው ስትል ትጠይቃለች።

ብራንድ በእግር ኳስ ቢዝነስ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ካገኘ ሰንበትበት ብሏል:: በእግር ኳስ ኢንዱስትሪ ውስጥ በገንዘብ አቅም ለመፈርጠር እና አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት የብራንድ ጥቅም ከፍተኛ ነው:: ብራንድን በተለያዩ ዘዴዎች መፍጠር ይቻላል:: ክለቦች የደጋፊዎቻቸው ህብረ ዜማ፣ የአጨዋወት ፍልስፍናቸው፣ የሚለብሱት የማልያ ቀለም እና ዲዛይን፣ መጠርያ ስማቸው፣ አርማቸው፣ ውጤታማነታቸው እና ቅፅል ስማቸው ሳይቀር በጊዜያት የማይቀየር እና በህብረተሰቡ ጭንቅላት ውስጥ አንዴ ከገባ በኋላ ለረጅም አመታት በሚገባ ተቀርፆ ሲቀመጥ ለክለቡ ብራንድ ሆነ ማለት ነው::

ብራንድ በራሱ የሚያድግም የሚሞትም ነው:: አንድ ክለብ የማራኪ አጨዋወት ባለቤት ቢሆን ሰዎች የክለቡን አርማ ባዩ ቁጥር ውብ ጨዋታው ውልብ ይልባቸዋል:: በአሰልጣኞች ሹም-ሽር ወይም በሌሎች ምክንያቶች ያ ማራኪ አጨዋወታቸው መልኩን የቀየረ እለት ክለቡ ብራንዱን እንዳጣ ይቆጠራል:: ብራንድ በቢዝነስ አለም ውስጥ በሰው ገላ ላይ በሚያርፍ ንቅሳት ይመሰላል:: አንድ ሰው በሰውነቱ ላይ የተነቀሰው ንቅሳት ዘላለማዊ እንደሆነው ሁሉ አንድ ክለብ አንድ ጊዜ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ የፈጠረውን ምስል በቀላሉ መፋቅ የማይታሰብ ነው:: ቪ ምልክት ያለው አርማ ስታዩ ወደ አዕምሯችሁ የሚመላለሰው ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነው:: ቢጫ ማልያ እና ጥቁር ቁምጣ ስትመለከቱስ የቡና ደጋፊዎች ህብር ዜማ ትውስ አይላችሁም? በየትኛውም የአለም ክፍል ቢገኙ ቀይ እና አረንጓዴ ማልያ ካያችሁ መከላከያ እዚህ ምን ይሰራል የሚል ጥያቄ አዕምሯችሁ ውስጥ ይፈጠራል:: ቀይ በነጭ ሸንተረር ስትመለከቱ የመብራት ኃይል ወርቃማ ዘመን ትዝ አይላችሁም? የክለብ ማልያዎችን ከአጋጣሚዎች ጋር አስተሳስረን ወይም ለረጅም ዘመናት የተጠቀሙበት ማልያ በመሆኑ አንዴ አዕምሯችን ውስጥ ገብቶ ተደላድሏል:: ነገር ግን ክለቦች ብራንዳቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይጠቀሙበት ቀርተዋል::

## ብራንድ...? ምን ተይዞ

በብራንድ ለመጠቀም ቀድሞውኑ የማርኬቲንግ ፅንሰ-ሃሳብ በእግርኳሳችን ውስጥ ዘልቆ ሊገባ ይገባል:: እግርኳሳችን ገና ከአማተር አስተሳሰብ ያልተላቀቀ በመሆኑ የእግርኳስ ቢዝነስ ፀሃይ በኢትዮጵያ ገና አልወጣችም:: የመንግስት እና የግል ተቋማት ክለብን የሚያቋቁሙትና በየአመቱ እስከ 20 ሚልዮን ብር በጀት የሚመድቡት ማህበራዊ እና ሃገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት እንጂ ከክለቦቹ ትርፍ ለማግኘት ባለመሆኑ ክለቦቻችን ከእግርኳስ ገንዘብ ለማግኘት እንዲንቀሳቀሱ አይጠበቅም::

አንድ ተቋም ክለብን የሚያስተዳድረው አንድም ፖለቲካዊ ትርፍ አሊያም ማህበረሰባዊ ጥቅም ለማግኘት ነው:: በአመት በመቶ ሚልዮኖች ትርፍ የሚያጋብስ ድርጅት ከእግርኳስ በሚገኝ ጥቂት ሚልዮን ብር ላይ ትኩረት ሊያደርግ አይችልም:: በመሆኑም ዋናው ሚና ይጫወታሉ ተብለው የሚጠበቁት ፌዴሬሽኖች እና የክለብ አመራሮች ናቸው:: አንድ የክለብ አመራር ክለቡን ራሱን የቻለ እና በየአመቱ ትርፍ የሚያጋብስ ክለብ የመፍጠር ራእይ ከሌለው ምንግዜም በተቋማት አመራሮች መልካም ፍቃድ ላይ የተንጠለጠለ ክለብ ይሆናል::

በኢትዮጵያ አንዳንድ ክለቦች ብራንድ እንደሆኑ ብናስብ እንኳን ገንዘብ ሲያገኙ የሚችሉበት መንገድ ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ መከላከያን በዝነኛው ማልያ የምንለየው ቢሆንም የክለቡ የደጋፊዎች ቁጥር ዝቅተኛ በመሆኑ በብራንዱ ብቻ ምንም ሊፈይድ አይችልም። እንደ አርባምንጭ ከነማ እና ወላይታ ድቻ ያሉ ክለቦችን ብንመለከት ደግሞ ከፍተኛ የደጋፊ ቁጥር አላቸው። ነገር ግን የደጋፊ መኖር ብቻውን ካለ ጠንካራ አመራር ለ90 ደቂቃዎች ቡድን ከማበረታታት ሊዘል የሚችል ፋይዳ አይኖረውም። ሁሉንም ያሟሉትን ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ኢትዮጵያ ቡናን ተመልከቱ። ሁለቱም በርካታ ደጋፊ አላቸው፣ ሁለቱም በሃገሪቱ ደረጃ የጥሩ ብራንድ ባለቤቶች ናቸው። ነገር ግን ከጥቂት የማልያ ሽያጭ እና አባል ምዝገባ ውጪ ምንም መስራት ያልቻሉ ክለቦች ናቸው።

### ማልያ እና ብራንድ በኢትዮጵያ

ዘንድሮ ክቦቻችን ከሚለብሱት ማልያ ጋር አያይዘን ጉዳዩን ብንመለከተው ክለቦቻችን ከብራንድ አስተሳሰብ እንዴት ወደኋላ እንደቀሩ መገንዘብ እንችላለን።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በ1938 ይድነቃቸው ተሰማ በፈረንሳዩ ሊል ላይ የተመለከቱት የ 'ቪ' ምልክትን በማልያው ደረት ላይ እንዲጠቀም ካደረጉ በኋላ በጊዜው ነጮችን ሲታገሉ ለነበሩት ኢትዮጵያውያን የድል ምሳሌ መሆን ቻለ። ከዛ በኋላም ክለቡ ይህን ምልክት እስካሁን ሲጠቀምበት ኖሯል። በዋናነት የሚለብሰው ቢጫ ማልያ ላይ የ'ቪ'ው ምልክት በጉልህ ይታያል። ዘንድሮ ክለቡ ይህንን ምልክት ባያጠፋውም ከግማሽ ምዕተ-አመት በላይ ሲጠቀምበት የኖረውን ቢጫ ማልያ ወደ ብረቱካናማ ቀይሮ የ 'ቪ' ምልክቱም በጉልህ እንዳይታይ ሆኗል። አንድ የአዲስ አበባ ስታዲየም ተመልካች የተጫዋቾችን ፊት ተመልክቶ ካልሆነ በቀር አዲሱን ማልያ ተመልክቶ "ይህ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው" የማለት እድሉ እጅግ ዝቅተኛ ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስና ቢጫ ማልያ፣ ቢጫ ማልያ እና ቀይ 'ቪ' በደጋፊዎቹ እና በእግርኳስ ተከታታዩ አእምሮ በእጅጉ ዘልቆ በመግባቱ በሌላ የማልያ ቀለም መቅረብ ተመልካችን ግራ ያጋባል አቶ ይድነቃቸው እግርኳሱ በቅጡ ባልዳበረበት ጊዜ ያስቀመጡትን ትልቅ አሻራ አሁን በዘመናዊው አለም ውስጥ እየኖርን ለማስቀጠል አለመቻላችን ያሳፍራል።

በአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ መከላከያ የኬንያው ሊዮፓርድስን ኤ.ሲ. ላይ ሲያስተናግድ የለበሰው ማልያም የኢትዮጵያ ክለቦችን የብራንድ አስተሳሰብ ደረጃ ያመላክተ ነው። ከ1947 ጀምሮ በቀይ እና አረንጓዴ ማልያው የሚታወቀው መከላከያ በእለቱ ለብሶ ወደ ሜዳ የገባው ከክለቡ ማንነትም፣ ታሪክም፣ አርማም ጋር ፍፁም የማይገናኝ ማልያ ነው። በጨዋታው የመከላከያ ተጫዋቾች ቢጫ ማልያ በሰማያዊ ቁምጣ ለብሰው ከመልበሻ ክፍል ሲወጡ በስታዲየሙ የተገኘው ተመልካች በለመደው ማልያ ተጫዋቾቹ እስኪወጡ መጠበቁ እርግጥ ነው። ቀይ እና አረንጓዴ ቀለማት ክለቡን የሚያስዳድረው የመከላከያ ሰራዊት መለያ ባይወክል እንኳን ለ60 አመታት በብዙሃን አእምሮ የተለመደን ማልያ መቀየር እንዴት ትርፍ ሊያስገኝ ይችላል?

ሁኔታው ከክለቦች አልፎ በብሄራዊ ቡድኑ ላይ መታየቱ በራሱ በእግርኳሳችን ላይ ያለውን ችግር የሚያመላክት ነው። ፌዴሬሽኑ ባለፉት 2 አመታት በየጨዋታው ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ የተጫዋቾቹን ማልያ ቀለም እና ዲዛይን ሲቀያይር ተመልክተናል። አንዳንድ ማልያዎች (ኢትዮጵያ ከ ናይጀርያ ካላባር ላይ፣ ኢትዮጵያ ከ ሩዋንዳ ኤ.ሲ. ላይ ...) ብሄራዊ ቡድኑን የማይወክሉ ናቸው።

### ክለቡ ወዲህ ደጋፊው ወዲያ...

አርባምንጭ ከነማ ለደጋፊዎቹ ገበያ ያቀረበው ማልያ ለክለቡ ገቢ በማስገባቱ ጠቃሚነቱ ባይካድም በጣም በአስገራሚ ሁኔታ የተጫዋቾቹ ማልያ እና የደጋፊዎቹ ማልያ ምንም መመሳሰል አይታይበትም። ክለቡ ዘንድሮ የሚለብሰው ማልያ ሙሉ ቀይ ሲሆን በማልያው ግራ ደረት ላይ ዩኤስኤ የሚል በነጭ ቀለማት የተፃፈ ፅሁፍ ይታያል። ማልያው ላይ አርማ የሌለው ሲሆን በጀርባው ከቁጥሩ ከፍ ብሎ የክለቡ ስም በላቲን ፊደላት ተፅፏል። ወደ ደጋፊዎች ማልያ ስንመጣ ደግሞ ቀለማቱ እና ዲዛይኑ ሙሉ ለሙሉ የጋሞ ባህላዊ ልብስ የሆነው ደንገዛን ይመስላል። በፊት ለፊት ግራ ደረት ላይ የክለቡ አርማ የሚገኝ ሲሆን ከጀርባው ደግሞ የክለቡ ስም በግዕዝ ፊደላት ተፅፏል። ሁኔታውን ላልተረዳ ሰው አርባምንጭ ከነማ እየተጫወተ በሌላ ክለብ ደጋፊዎች የሚደገፍ ክለብ ይመስላል። የአርባምንጭ ደጋፊዎች ማልያ የአርባምንጭ ከተማን፣ ክለቡን፣ ባህሉን እና የህዝቡን የአኗኗር ዘይቤ የሚወክል በመሆኑ ጥቂት ማስተካከያ ተደርጎበት የተጫዋቾችም መለያ ቢሆን ለክለቡ ጠቃሚ እርምጃ ይሆን ነበር። ከአርባምንጭ ጋር የሚመሳሰሉ በርካታ ክስተቶችን መታዘብ አዲስ ነገር አይደለም። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በቻን፣ በአፍሪካ ዋንጫ እና በሴካፋ ጨዋታዎች ላይ ደጋፊዎች የሚለብሱትና ተጫዋቾቹ የሚለብሱት መለያ አለመጣጣምም ስንመለከት ችግሩ ያለው በብሄራዊው እግርኳስ ላይም እንደሆነ እንረዳለን።

### ብራንድ መቀየር

ከእግርኳሱ፣ ከቢዝነሱ እና ከሃገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት እንዳስፈላጊነቱ ብራንድን መቀየር በክለቦች ላይ ለውጥ ሊፈጥር ይችላል። ከተመሰረተበት 1975 ጀምሮ በተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ውህደት ሲተዳደር የቆየው ኢትዮጵያ ባንኮች በ2003 ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መጠቃለሉን ተከትሎ ስያሜው ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲቀየር የማልያ ቀለሙም አብሮ ተለውጧል። ከዚህ ቀደም በጥቁር እና ነጭ ሸንተረር ማልያ የሚታወቀው ክለብ አሁን ላይ የማልያው ቀለም ሀምራዊ መሆን ግርታ ሊፈጥርብን አይችልም። ምክንያቱም የክለቡ ባለቤት የሆነው ንግድ ባንክ መለያ ሀምራዊ በመሆኑና የክለቡም ስያሜ የባንኩን በመያዙ አእምሮአችን ንግድ ባንክ እና ሀምራዊ ቀለምን በአንድ ላይ አቆራኝቷቸዋል። በአጠቃላይ ብራንድን ለመፍጠር፣ ለመለወጥ ወይም ለማሳደግ እምቅ አቅምን ከግምት ውስጥ ማስገባት ግድ ይላል። ብራንድ ከገንዘብ ምንጭነትም አልፎ የህዝቦች ማንነት ማሳያ፣ የድል አድራጊነት ምልክት እና የማሸነፍ ወኔ ማነሳሻ ጭምር መሆን ይችላል። ለዕሁፋችን ማሳረጊያ የአንዳንድ የአለማችን ክለቦች የብራንድ ተፅእኖና አዳዲስ ሀሳቦች እንመልከት።

አጥባቂ ካቶሊክ እና ፕሮቴስታንቶች በሚበዙባት ብራዚል ተጫዋቾች ወደ ማንችስተር ዩናይትድ ተገዝተው መጫወትን ከሰይጣን ጋር ከመተባበር ጋር ያያይዙት ነበር። ማንችስተር ዩናይትድ በአርማው ላይ የሚገኘው የሰይጣን ምልክት እና ቅፅል ስማቸው በብራዚላውያን ዘንድ ጥላቻን አትርፎበት ቆይቷል። አሁን ማንችስተር ዩናይትድ በቢዝነሱ አለም ከሚጠቀሱ ታላላቅ ብራንዶች አንዱ በመሆኑ የድሮው አስተሳሰብ አሁን ላይ የመስራት እድሉ ዝቅተኛ ቢሆንም የብራንድ ተፅእኖ ይህን ያህል ስር እንደሚሰድ መገንዘብ እንችላለን። ዘንድሮ በማሌዥያ ባለሃብቶች የተያዘው ካርዲፍ ሲቲ ለአመታት የተጠቀመበትን ሰማያዊ መለያ ወደ ቀይ የቀየረበት ምክንያት በማሌዥያ ቀይ የእድል ምልክት ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው። ክለቡን በማሌዥያውያን ልብ ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ያለመ ነው። አንዳንድ ጊዜ ብራንድን መቀየር እንደሚያዋጣ ያስገነዝበናል።

የሀል ሲቲ ደጋፊዎች የክለቡ መጠሪያ ወደ ሀል ታይገርስ እንዲለወጥ በክለቡ መታቀዱን በሰሙ ጊዜ በተቃውሞ ጎዳና ወጥተዋል። የክለቡ ሀሳብ ግን በእንግሊዝ የመጨረሻ ስማቸው ሲቲ የሚል በርካታ ክለቦች በመኖራቸው ይህን መቀየር ለክለቡ ብራንድ ማደግ ይጠቅማል ከሚል መነሻ ነው።

በ2005 እና 2006 ጁቬንቱስን አሰልጥነው የሴሪአ ክብርን የተቀዳጁት ፋብዮ ካፔሎ በአንድ ወቅት የክለቡን የእንስሳት መጠበቂያ ማእከል ሲጎበኙ በማእከሉ ከክለቡ ማልያ ጋር የሚመሳሰለው የሜዳ አህያን ባለመመልከታቸው ተገርመው የሜዳ አህዮችን ገዝተው ለማእከሉ ሰጥተዋል። ሃብታሙ ክለብ ፓሪስ ሰን ዠርመ የሚገኝበትን ከተማ ስያሜ በማጉላትና በከተማዋ አለም አቀፍ ዝና ለመጠቀም በማሰብ አርማው ላይ ፓሪስ የሚለውን ፅሁፍ ጎላ ተደርጎ እንዲታይ በማድረግ እንደ አዲስ አሻሽለውታል።

ክለቦቻችን ብራንዳቸውን ተጠቅመው ደጋፊ የሚስቡበት፣ ገንዘብ የሚሰሩበት እና ራሳቸውን ወደ ሃብታም እግርኳስ ክለብነት የሚቀይሩበት ጊዜ አሁን ነው። በሆይ ሆይታ ሳይሆን በረጅም ጊዜ እቅድ የመስሪያ ጊዜያቸው ደርሷል። አዳዲስ የቢዝነስ ሃሳቦች ያስፈልጉናል፣ ለኛ ሊጠቅሙ የሚችሉ የትልልቅ ሃገራት የእግርኳስ ቢዝነስ አሰራሮችን ልምድ መውሰድም ተገቢ ነው።

# ጥቂት ታክቲካዊ ነጥቦች በፕሪሚየር ሊጉ ዙርያ

አዲስ ወርቁ ለማህበራዊ ድረገፅ ተከታታዮች አዲስ አይደለም፡፡ በፌስቡክ እና ትዊተር በሚያቀርባቸው ጥልቅ ታክቲካዊ ትንተናዎች በርካታ አድናቂዎች አፍርቷል፡፡ ሶከር ኢትዮጵያ የፕሪሚየር ሊጉን አንደኛ ዙር መጠናቀቅ ተከትሎ ከአዲስ ጋር በታክቲክ ጉዳዮች ላይ አጭር ቆይታ አድርጋለች፡፡

## Addis Football Tactics

ጥያቄ: ዘንድሮ 3-5-2 በሊጉ አንዳንድ አሰልጣኞች እየተተገበረ ነው፡፡ በ1990ዎቹ የ3-5-2 ፋሽን በ4-4-2 ከተሸፈነ በኋላ ኢትዮጵያውያን ለአመታት ከ3-5-2 አጨዋወት አልወጡም ነበር፡፡ ጊዜ አልፎ የ4-4-2 አስተሳሰብ ወደ 4-3-1-2፣ 4-3-3 እና 4-2-3-1 ሲቀየሩ ኢትዮጵያውያን አሰልጣኞች ገና ወደ 4-4-2 እየገቡ ነበር፡፡ ዘንድሮ አልፎ አልፎ እንደ ቡድኖች አጨዋወት የጨዋታ እቅዳቸውን የሚቀይሩ (Proactive) አሰልጣኞችን መመልከታችንን እንዴት ትመለከተዋለህ፡፡ በሂደት የአሰልጣኞቻችን አእምሮ መቀየር ጀምሯል?

**አዲስ:** የአሰልጣኞቻችን አዕምሮ ተቀይሯል ብሎ በእርግጠኝነት መናገር ከባድ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ጥሩ የሚባሉ ለውጦች አሉ፡፡ እንደቀደሙት አመታት ሳይሆን ቡድኖቻችን እንደ ቀኖና ከያዙት ‹ፍላት› 4-4-2 እየራቁ መጥተዋል፡፡ 4-2-3-1፣ 4-3-3፣ 3-5-2/5-3-2 (ወላይታ ዲቻ)፣ 4-5-1፣ 4-4-2 ዳይመንድ (መከላከያ በጥቂት ጨዋታዎች) ሲስተምን የሚተገብሩ ቡድኖች ማየት ችለናል፡፡ ዘመኑ የስልጣኔ እና የቴክኖሎጂ ነው፡፡ አሰልጣኞቻችን ለመማር ፍቃደኛ ከሆኑ በሩ ክፍት ነው፡፡ የታላላቅ ሊግ ውድድሮችንም በብዛት የማየት እድል አላቸው፡፡ ትምህርት ከወረቀት ጋር ብቻ የሚገናኝ ነገር ነው ብዬ አላምንም፡፡ በየትኛውም አጋጣሚ አዲስ ነገር የማወቅ እና የመማር ዕድሉ አላቸው፡፡

ጥያቄ: በፕሪሚየር ሊጉ ከቆሙ ኳሶች በርካታ ግቦች አይቆጠሩም፡፡ እንደውም የማእዘን ምቶች እና ቅጣት ምቶች ሲገኙ እንደ ግብ እድል አይቆጠሩም፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የሚቆጠሩት ግቦች ከተከላከዮቻች ደካማነት ጋርም ይያያዛል፡፡ የቡድኖቻችንን የቆመ ኳስ አጠቃቀም እንዴት ታዘብከው? ከ3ቱ የመከላከል ሲስተሞች አንፃር የተከላካዮች የቆመ ኳስ የመመከት ችሎታስ?

**አዲስ:** በመጀመሪያው ዙር ከቆሞ ኳሶች የገቡት ጎሎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ አለመታደል ሆኖ በቁጥሮች ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ በእኔ እምነት የቆሙ ኳሶችን የምንከላከልበትም ሆነ የምናጠቃበት መንገድ የተጠና አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ ቡድኖች በእርግጥ የትኛውን ዘዴ በወጥነት እንደሚጠቀሙ ማወቅ አልቻልኩም፡፡ የጠራ ነገር የለም፡፡ በቀጠና ይሁን ሰው ለሰው ይሁን ወይም ድብልቅ በእርግጠኝነት መናገር አልችልም፡፡ ቡድኖቻችን በልምምድ ሜዳዎች ላይም በደንብ የሚዘጋጁባቸው አይመስለኝም፡፡ ይህየቆየ ደካማ ጎናች በሊጉ ውድድሮች ዋጋ ሲያስከፍለን በብዛት ላንመለከት እንችላለን ነገር ግን በክለቦች ኢንተርናሽናል ውድድሮች ላይ ግን ይሄ ገመናችን ሊጋለጥ ይችላል፡፡

ጥያቄ: በፕሪሚየር ሊጉ አብዛኛዎቹ በተለይ ከወገብ በላይ ያሉ ክለቦች በአጥቂ አማካይ (10 ቁጥር) ይጫወታሉ፡፡ ነገር ግን በመስመሮች መሃከል ያለውን ሰፊ ክፍተት አይጠቀሙበትም፡፡ አሰልጣኞች ይህን ቦታ እንዴት ይጠቀሙበት?

ልክ ነህ አብዛኞቹ ቡድኖቻችን ሰፊ ክፍተት በመስመሮች መካከል ይተዋሉ፡፡ በዘመናዊ እግር ኳስ ይህ ቦታ እጅግ ወሳኝ ቀጠና ነው፡፡ ነገር ግን አሰልጣኞቻችንም ሆኑ 10 ቁጥሮቻችን ክፍተቱን ለመጠቀም ሲጥሩ እምብዛም አልመለከትም፡፡ በአብዛኛው ጊዜ የሚያስጨንቃቸው ከተከላካዮች ጀርባ የሚገኘው ቦታ ብቻ መሆኑ ያስገርመኛል፡፡ አሰልጣኞች ይህን ቦታ ለመጠቀም አማካዮቹን ትዕግስት እና ብልሃት ማስተማር አለባቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ትዕግስት ያልኩበት ምክንያት አብዛኞቹ








10 ቁጥሮች በመስመሮች መካከል ከመጠበቅ ይልቅ በጥልቀት ወደ ኃላ እየተመለሱ ኳስን ለመቀበል ይሞክራሉ። በእኔ እምነት እነዚህ ተጫዋቾች ወደ ኳሱ መምጣታቸው ትርጉም የለውም። ምክንያቱም ለምሳሌ በ4-2-3-1 የሚጫወት ቡድን ሁለት ሆልዲንግ አማካዮች አሉት እነዚህ ተጫዋቾች ኳሱን ከኃላ ለመመስረት በጣም በቂ ናቸው። 10ቁጥሩ በብልሃት ጥሩ ቦታ ይዞ በመስመሮች መካከል ቢጠብቅ ይሻላል። ሲያስፈልግም ወደ ክንፍ እየወጣ የተጋጣሚን ፉልባክ ማጨናነቅ(overload) ይችላል። የተቃራኒ ቡድን የተከላካይ አማካይ እርሱን ተከትሎት ወደ መስመር ከወጣ መሀል ለመሀል ትልቅ ቀዳዳ ስለሚተው ለቡድን ጓደኞቹ ክፍተትን መፍጠር ይችላል።

ጥያቄ፡ ባለፈው ወር ኢትዮ-ስፖርት ጋዜጣ ላይ የፃፍከውን ፅሁፍ ተመልክቸዋለሁ። የአሰልጣኝ አሪጎ ሳኪ ዝነኛው ሚላን በተከላካዩ እና በመጨረሻው አጥቂ መካከል ያለው ርቀት ከ25 ሜትር እንደማይበልጥ ጠቅሰህ ቡድኖቻችን በዚህ ረገድ ሚዛናቸውን እንደሳቱ ገልፀሃል። በእርግጥ ይሄ ችግር የመጣው ከአሰልጣኞቹ ነው ወይስ የተጫዋቾቻችን ወደ ኳስ የመሮጥ አባዜ እና ታክቲክ የመቀበል ድክመት ውጤት ነው?

አዲስ፡ ይሄን ጥያቄ በእርግጠኝነት መመለስ ከባድ ነው። በእኔ እምነት አሰልጣኞቹም ሆነ ተጫዋቾቹ የራሳቸውን ድርሻ ይወስዳሉ። የትኞቹ ቡድኖች ናቸው በልምምድ ሜዳዎች ላይ በቡድን ቅርፅ (form)፣ የመከላከል ውህደት ላይ እና ጥቅጥቅ (Compact) ብሎ መከላከል ላይ በቂ ጊዜ ሰጥተው የሚለማመዱት? ተጫዋች በልምምድ ሜዳ በተደጋጋሚ ካላሳየከው እና ካላሰራከው ከየት ያመጣዋል?

ጥያቄ፡ በአውሮፓ የምንመለከታቸው ለፍፁምነት የቀረቡ የጨዋታ አቀራረቦችን በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ላይ ተመልክተህ ታውቃለህ? አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለትንታኔ የሚመቹ ድንቅ አቀራረቦች ቢመለከቱ እንኳን በአጋጣሚ የሆኑ ያህል ይሰማቸዋል። የአሰልጣኞቻችን የጨዋታ አቀራረብ እንደው እንደነገሩ ነው ወይስ የተጠና ነው ብለህ ታምናለህ?

አዲስ፡ ምንም ጥርጥር የለውም በታክቲኩ ረገድ የእኛን ሊግ አውሮፓ ጋር ማወዳደር ፈፅሞ አይታሰብም። እንደ እኔ እምነት የአብዛኞቹ ቡድኖቻችን አጨዋወት የተጠና ነው ብዬ ለመናገር በጣም ይከብደኛል። ለAddis Football Tactics የፌስቡክ ገፅ ታክቲካዊ ትንታኔዎችን ለመፃፍ ስሞክር በእጅጉ የሚያስቸግረኝ የጨዋታ ንድፍ(Pattern of Play) ማውጣት ነው። በብዙዎቹ አጋጣሚዎች የቡድኖቻችን የጨዋታ እቅድ ምን እንደሆነ መረዳት አስቸጋሪ ሆኖብኛል። ምንም ልትጨብጠው አትችልም። ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ ተጋጣሚያቸውን በግራ መስመር ወይንም በቀኝ ወይንም መሀል ለመሀል ዘልቀው

# ታክቲክ ጥቂት ነጥቦች በሊጉ ዙርያ

መግባት እንደፈለጉ ማወቅ ያዳግትሃል፡፡ የትኛውን ቀጠና ትኩረት አድርገው እንደሚያጠቁትም እንደዚሁ፡፡ ነገር ግን ቡድኖቻቸውን በደንብ የሚያዘጋጁ እጅግ ጥቂት አሰልጣኞች መኖራቸውን ግን አልክድም፡፡

**ጥያቄ፡** ወደ በጎ ጎኖች ስንመለስ... በፕሪሚየር ሊጉ በርካታ ተስተካካይ ጨዋታዎች ተካሂደው ግብ ያልተቆረበት ጨዋታ አንድ ብቻ ነው፡፡ ቀድሞ በአንድ ሳምንት እንኳን የማናየውን በጨዋታ እስከ 6 ግቦች እየተቆጠሩ ተመልክተናል፡፡ በመጀመርያዎቹ ሳምንታት የታየው የግብ ድርቅ እንዴት ተቀረፈ?

**አዲስ፡** እውነት ለመናገር የዚህን ጥያቄ መልስ አላውቀውም! ሊጋችን እንዲህ ነው ብለክ የምትተነብየው አይደለም፡፡ የአጋጣሚ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡

**ጥያቄ፡** ኢትዮጵያ ቡና ቀስ በቀስ ወደ ውጤታማነት ተመልሷል፡፡ ለውጤታማነታቸው አብይ ምክንያት ደግሞ የአማካይ ክፍላቸው ጥንካሬ ነው፡፡ ነገር ግን የዳዊት መጎዳት ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ማድረጋቸው አይቀርም፡፡ አሰልጣኝ ጳውሎስ ሊተገብሯቸው የሚገባቸው ፕላን ቢ የጨዋታ እቅዶች ምን አይነት ሊሆኑ ይገባል?

**አዲስ፡** በመጀመሪያ በዘንድሮው ውድድርጥሩ አቋም እያሳየ የሚገኘው ዳዊት እስጢፋኖስ በፍጥነት እንዲያገግም ምኞቴ ነው፡፡ በእኔ እምነት የቡድኑ ቅርፅ ምንም ሳይነካ ጋቶች ፓኖምን በተከላካይ አማካይነት ሚና ማሰለፍ እና ፋሲካ አስፋውን ከመስኡድ ጎን ወደፊት አስጠግቶ ማጫወት ጥሩ አማራጭ ይመስለኛል፡፡ ጋቶች ለቡድኑ ጥሩ ሚዛን የመስጠት አቅም አለው ባይ ነኝ፡፡ ወይም በ4-2-3-1 ፋሲካ እና ጋቶት በሆንዲንግ ሚና መስኡድን ደግሞ ከአጥቂ ጀርባ ማሰለፍም ይቻላል፡፡



**ጥያቄ፡** በሊጉ በአብዛኛው የተደራጀ መከላከልን አንመለከትም፡፡ ሰው በሰው የመከላከል ዘዴ በሊጉ እንደ ብቸኛ አማራጭ በመታየቱ ደረጃውን የጠበቀ ተከላካይ ያልያዘ ቡድን በቀላሉ ግብ ሲቆጠርበት ተመልክተናል፡፡ በተቃራኒው በመሳይ ተፈሪ ቡድን ላይ የምናየው የመከላከል አደረጃጀት አድናቆት የሚቸረው ነው፡፡ ቡድኑ በአንደኛው ዙር የተቆጠረበት 7 ግብ ሲሆን በመጀመሪያዎቹ 12 ጨዋታዎች 3 ግብ ብቻ ተቆጥሮበታል፡፡ ሁኔታው በአጋጣሚ የመጣ እንዳልሆነ እርግጥ ነው፡፡ ቡድኖች ከወላይታ ድቻ ምን ይማራሉ?

**አዲስ፡** አንተ እንዳልከውም የወላይታ ዲቻ የመከላከል አደረጃጀት አድናቆት የሚገባው ነው፡፡ በእርግጥ 3-5-2/5-3-2 መጫወታቸው በመከላከሉ ረገድ ጠንካራ እንዳደረጋቸው ጥርጥር የለውም፡፡ ቡድኑ ከማንኛውም የተቃራኒ የአጥቂ ክፍል ጋር ቢገናኝ ‹ትርፍ ሰው› አለው፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት ከ4-2-3-1 ጋር ሲጫወቱ ሶስቱ የመሀል ተከላካዮች ከአንድ አጥቂ ጋር ብቻ ነው የሚፋለሙት፡፡ ከ4-4-2 ጋር ደግሞ አሁንም የመሀል ተከላካዮቹ አንድ ትርፍ ሰው ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ከ4-3-3 ጋርም እንዲሁ የክንፍ ተከላካዮቹ በአብዛኛው ወደ ኋላ በመመለስ ባለ አምስት ሰው የኋላ መስመር ስለሚሰሩ 5ለ3 ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ የዲቻ ተከላካዮች ሁሌም የቁጥር ብላጫ ስለሚኖራቸው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእጅጉ የሚደንቀኝ የቡድኑ እንደ አንድ መንቀሳቀስ ነው፡፡ በመከላከል ወቅት ሁሉም ተጫዋች ለቡድኑ ይለፋል ከፊት መስመር እስከ የተከላካይ ክፍሉ፡፡ የተከላካይ ክፍሉ ትኩረትም አስገራሚ ነው፡፡ በአካል ብቃቱም ሆነ ተክለ ሰውነቱም በኩል አይታሙም፡፡ የመሳይ ተፈሪ ቡድን ከመከላከል ጥንካሬው ባሻገር በተጫዋቾቹ ላይ የሚታየው ከፍተኛ አንድነት ተነሳሽነት እና ፍላጎትም ወሳኝነት አለው፡፡ ሌሎች ቡድኖች መውረስ አለባቸው ብዬ የማምነው ይሄን ነው፡፡

**ጥያቄ፡** ቅዱስ ጊዮርጊስ ሳይቸገር 1ኛውን ዙር በመሪነት አጠናቋል፡፡ ከቡድኑ ትልቅነት እና ጥልቅ ስብስብ በተጨማሪ በታክቲኩ ረገድ የቅዱስ ጊዮርጊስ ጠንካራ ጎን ምንድን ነው?

**አዲስ፡** የተጫዋቾቹ ጥራት እና ጥልቀት እንዳለ ሆኖ አዲሱ አሰልጣኝ አዳዲስ ነገሮችን ለማካተት ሞክረዋል፡፡ ለምሳሌ ተጋጣሚን በላይኛው የሜዳ ክልል ፕሬስ ማድረግ፣ የተከላካይ ክፍሉ ወደ ፊት በማስጠጋት በመስመሮች መካከል ያለውን ክፍተት እንዲያጠብ ማድረግ፣ የክንፍ አጥቂዎቹ በቻሉት መጠን ጨዋታውን ወደ ጎን እንዲለጥጡ እና ሌሎችም ትንንሽ የማይባሉ ለውጦችን አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም የጊዮርጊስ የተከላካይ ክፍሉም ሆነ በረኛው እጅግ ጠንካራ ናቸው፡፡ በግለሰብ ደረጃም ጥራታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ኡመድ ኡኩሪም ወሳኝ ወሳኝ ጎሎችን አስቆጥሯል፡፡

**ጥያቄ፡** ወላይታ ድቻ ቅዱስ ጊዮርጊስን ካሸነፈ በኋላ አሰልጣኝ ፀጋዬ ኪዳነማርያም ቅዱስ ጊዮርጊስን ለማሸነፍ የድቻን ፕላን ለመጠቀም ሞክሯል፡፡ በጨዋታው በግልፅ እንደታየውም ቅዱስ ጊዮርጊሶች የግብ እድል እንዳይፈጥሩ አድርጓቸዋል፡፡ በእርግጥ ወላይታ ድቻ ቅዱስ ጊዮርጊስን የረታበት ሲስተም እና 3-5-2 እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ኢትዮጵያ ቡና አይነት በ3 አማካይ የሚጫወቱ ቡድኖችን ለማሸነፍ ዋነኛ አማራጭ መሆን ይችላል?

**አዲስ፡** በእኔ እምነት ከአማካይ ክፍሉ ጋር በቁጥር ለመፋለም አይመስለኝም፡፡ አብዛኞቹ ቡድኖች ሲስት አማካዮችን ይጠቀማሉ፡፡ 4-2-3-1 ሆነ 4-3-3 መሀል ለመሀል ሶስት አማካዮች አሏቸው፡፡ ቅድም እንደገለፅኩት በመከላከል ወቅትም ሆነ ከማጥቃት ወደ መከላከል በሚኖር ሽግግር ወቅትም ብዙ ተጫዋቾች ከኃላ ማስቀረታቸው ነው፡፡ 3-5-2 እንበለው እንጂ በመከላከል ወቅት 5-3-2 ማለት፡፡ አስበው የቁጥር ብልጫውን በፍፁም ቅጣት ምት ሳጥን ውስጥ ወይም አካባቢ አንዱን ስታልፈው አንዱ ወዲያው ይደርስብሀል፡፡ ኳሶችን ወደ ፍፁም ቅጣት ምት ሳጥን ክልል ስታሻማም የማግኘት ዕድልክ ጠባብ ነው፡፡ ያ ይመስለኛል ከባድ ያደረገው፡፡ ከወገብ በታች ያሉ ቡድኖች በተደራጀ መልኩ ቢጠቀሙት ከትልልቆቹ ቡድኖች ቢያንስ አንድ ነጥብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

**ጥያቄ፡** ከ14ቱ ክለቦች ገሚሶቹ በብቸኛ አጥቂ አንዳንዶች ደግሞ በ2 አጥቂ ይጫወታሉ፡፡ አብዛኛውን የሚያመሳስላቸው ነገር ክለቦች ለፊት አጥቂው ግብ የማስቆጠር ሚና ብቻ መስጠታቸው ነው፡፡ እንደ ፊሊፕ ዳውዚ ፣ አኪም አካንዴ ፣ ሚካኤል ጆርጅ ፣ ገብረሚካኤል ያዕቆብ ፣ ግሩም ተስፋዬ ፣ ታፈሰ ተስፋዬ ፣ ኡመድ ኡኩሪ እና ተመስገን ተክሌ ግብ ከማስቆጠር ውጪ በቡድን ስራ ላይ አይሳተፉም፡፡ ለባህላዊ አጥቂዎች መበራከት ምክንያቱ ምንድነው አሰልጣኞች ሆን ብለው ይህን ሚና ስለሚሰጧቸው ነው ወይስ አጥቂን በቡድን ስራ ውስጥ የማሳተፍ ግንዛቤው ስለሌላቸው?

**አዲስ፡** ከአጨዋወት ባህል ይመስለኛል፡፡ የአጥቂ ተጫዋች ማለት በቡድኑ የማጥቃት እንቅስቃሴ ላይ ብቻ መሳተፍ የሚመስላቸው ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ለዚህ ተጠያቂ የማደርገው አሰልጣኞቹን ነው፡፡ አንድ አሰልጣኝ የራሱን አጥቂ ‹የተጋጣሚ ተከላካይ ኳስ ሲይዝ ተጫነው›፣ ‹ጊዜ አትስጠው›፣ ‹ቡድናችን ከኳስ ውጪ ሲሆን በጥልቀት ወደ ኃላ በመመለስ ለአማካይ ክፍሉ እርዳታ ስጥ› እና የመሳሰሉትን ካላለው ተጫዋቹ በደስታ የሚቆም ይመስለኛል፡፡ ብዙ አጥቂዎች በተፈጥሮ እና ከልምድ መከላከል አይወዱም፡፡ በእርግጥ አንዳንድ አሰልጣኞች አጥቂዎቻቸው በማባረር ብቻ እንዳይደክሙ የሚሰጉ አሉ፡፡ ነገር ግን በዘመናዊ እግር ኳስ ሁሉም ተጫዋች በተለያዩ የእንቅስቃሴ ሂደቶች ውስጥ መሳተፍ አለበት፡፡ መከላከል ሲባል የተቃራኒን ተከላካይ የገባበት ገብቶ ማሳደድ ብቻ አይደለም፡፡ ብልጠት የታከለበት የቦታ አያያዝ ይዞ የተጋጣሚ ተከላካይ ለአማካዮ በቀላሉ ኳሶችን ማቀበል እንዳይችል የማቀበል አማራጮችን መስጋት በራሱ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

**ጥያቄ፡** በመጨረሻ... አንዳንድ ጊዜ ተጫዋቾች በግል ብቃታቸው ታግዘው ወይም በአርቢትሮች የተሳሳተ ውሳኔ ምክንያት ጨዋታዎች ሲቀየሩ ወይ አንድ ተጫዋች አሸነፈ ወይም ዳኛው አሸነፈ እንላለን፡፡ ዘንድሮ ጆሴ ሞውሪንሆ ማንቼስተር ሲቲን ሲረቱ እንደታየው አይነት በሊጋችን ዘንድሮ አሰልጣኝ ብቻውን (በታክቲኩ ውጤታማነት) ጨዋታ አሸነፈ ብለህ የደመደምክበት ጨዋታ ተመልክተሃል?

**አዲስ፡** ይህም ከባድ ጥያቄ ነው፡፡ ትንሽ እድል ቢታከልበትም ወላይታ ዲቻ ጊዮርጊስን ያሸነፈበት ጨዋታ ለዛ የሚቀርብ ይመስለኛል፡፡ ምንም እንኳን አሰልጣኝ መሳይ ተፈሪ በፈጣሪ ኃይል ነው ያሸነፍነው ቢልም፡፡ ቡድኑ በጨዋታው በእጅጉ የተገራጀ ነበር፡፡ በተጨማሪም አሰልጣኝ ፀጋዬ ኪዳነ ማርያም በሳሙኤል ሳኑሚ ብቸኛ ጎል ቡድናቸው ባንክ በጊዮርጊስ ሽንፈት ቢደርስበትም ሳይጠበቅ ይዘውት የቀረቡት የ3-5-2 የአጨዋወት ዘይቤ በእጅጉ ተመችቶኛል ነበር፡፡


www.soccerethiopia.net

አለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ፊፋ እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም በጀርመኗ ሙኒክ ከተማ በጠራዉ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በየሀገራቱ ዉስጥ የሚደረገዉ የእግር ኳስ እንቅስቃሴ የተሻለ ፕሮፌሽናል መልክ እንዲኖረዉ ያግዛል በሚል ያዘጋጀዉን የክለቦች ምዝገባ አሠራር (Club Licensing) ለመጀመርያ ጊዜ ያስተዋዉቃል። በስብሰባዉ የተገኙ የ209ኙ አባል ፌደሬሽን ተወካዮችም በጉዳዩ ዙሪያ ከተወያዩ በኋላ የፊፋን ሐሳብ በመቀበል በየአህጉራቱ የሚገኙ ኮንፌዴሬሽኖች ይህን አሰራር ተቀብለዉ እንዲተገብሩ ዉሳኔ በማሳለፍ ጉባኤዉን አጠናቀቁ። የአዉሮፓ እግር ኳስ ማህበር (UEFA) አዲሱን አሰራር በመተግበር የመጀመሪያዉ ሲሆን በሌሎች ኮንፌዴሬሽኖችም ይህ የክለቦች ምዝገባ አገልግሎት ላይ ዉሏል።

# አዲሱ የክለቦች ምዝገባ አሠራር በኢትዮጵያ

ሐገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ እግርኳስ ማህበር (CAF) አሠራሩን ለመተግበር ከ2011 ጀምሮ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ይህንን ሂደት ለማቀላጠፍም የዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ዜግነት ባላቸዉ Constant Omari Selemani የተባሉ ሰዉ የሚመራ እና ኢትዮጵያዊዉን አቶ ብርሀኑ ከበደን በአባልነት ያቀፈ ኮሚቴ ሰይሟል። ካፍ የክለቦች ምዝገባ እስከ ታህሳስ 31 2013 ድረስ በአባል ፌዴሬሽኖች እንዲተገበር ቀነ ገደብ አስቀምጦ የነበረ ቢሆንም የተለያዩ የአፍሪካ ክለቦች ቅሬታ በማሰማታቸዉ ጊዜዉ እስከ ህዳር 2014 እንዲራዘም ተደርጓል። እስከ ቀነ ገደቡ ጊዜ ድረስ በተዘጋጀዉ የክለቦች ምዝገባ ህግ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች በማሟላት ከሀገሩ ፌዴሬሽን ፈቃድ (License) ለማግኘት ያልቻለ ክለብ ከ2015 ጀምሮ በሚደረጉ የአፍሪካ ክለብ ዉድድሮች ላይ ተሳታፊ እንደማይሆንም ካፍ አስታዉቋል። በዚህ ፅሁፍ የዚህ አዲስ አሰራር ምንነት፣ እንዲሁም በክለቦቻችንና በአጠቃላይ በሐገራችን እግር ኳስ እድገት ላይ የሚኖረውን አስተዋፅኦ እንመለከታለን።

### የክለቦች ምዝገባ መመሪያ (Club Licensing Regulation) ምንድን ነው?

የክለቦች ምዝገባ መመሪያ በዙሪኩ 57ተኛው የፊፋ ጠቅላላ ጉባዔ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን የፊፋ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እ.ኤ.አ. ጥቅምት 29, 2007 ዓ.ም. የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አካል በማድረግ አፅድቆታል፤ ከ2008 ጀምሮም እየተሰራበት ይገኛል።

አለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ለአባል ፌዴሬሽኖቹ ባሰራጨው ፅሁፍ ላይ ይህንን መመሪያ "የተለያዩ የእግር ኳሱ አካላት ስፖርታዊ እሴቶችን፣ የፋይናንስ ግልፅኝነት፣ የክለቦች ንብረትነት እና አስተዳደር፣ የክለብ ውድድሮች ጥንካሬ እና ተቀባይነትን የመሳሰሉ የጋራ መርሆችን የሚያጎለብተው የክለቦች ምዝገባ አሠራርን የሚያስተዳድር ዋና መመሪያ ነው፤" ሲል ይገልፀዋል።

ይህ ጥራዝ (Document) ክለቦች በሀገርአቀፍ እና ዓለምአቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸውን ዝቅተኛ መስፈርቶች ያስቀምጣል። ዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር የፊፋ የክለቦች ምዝገባ መመሪያ (FIFA Club Licensing Regulations) ተብሎ የሚጠራውን ዋንኛ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጀ ሲሆን የየአህጉራቱ ኮንፌዴሬሽኖች ደግሞ በዚህ ዓለምአቀፍ ዶክመንት ተመርኩዘው የራሳቸውን መመሪያ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ጨምሮ የየሃገራቱ ማህበራት ደግሞ ይህን መመሪያ በሀገርአቀፍ ደረጃ እንዲሰራበት ለማድረግ በሚያመች መልኩ በማሻሻል ተግባራዊ ያደርጉታል።

### ዝቅተኛ መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

ከላይ እንደተገለፀው ክለቦች በሃገርአቀፍ ወይም በኢንተርናሽናል ውድድሮች ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። እነዚህ መስፈርቶች አምስት የተለያዩ ክፍሎች አሏቸው።

1. ስፖርታዊ መስፈርቶች

ይህ ክፍል ክለቦች ደረጃቸውን የጠበቁ የወጣቶች አካዳሚ እና የወጣት ተጫዋቾች ማብቂያ ፕሮግራሞች ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገልፃል። ይህ ማለት ክለቦች ከ15-21 ዓመት እና ከ10-14 ዓመት ባሉ የእድሜ ክልሎች ውስጥ ቢያንስ አንድ የተሟላ የወጣት ቡድን ይኖራቸዋል ማለት ነው። ክለቦች የወጣት ተጫዋቾቻቸውን እግርኳሳዊ የሆኑ እና ያልሆኑ ትምህርቶች እና የህክምና ወጪዎችን የመሸፈን ግዴታ አለባቸው። ይህ አሠራር ለዋና ቡድኑ የሚመጥኑ ተጫዋቾችን ማፍራት ከማስቻሉ በተጨማሪ ክለቦቹ ያሠለጠኗቸው ከ23 ዓመት በታች ያሉ ተጫዋቾች ባህር ማዶ ወዳሉ ክለቦች የሚዘዋወሩ ከሆነ ከዝውውር ሂሳቡ ድርሻ እንደሚኖራቸው በዚህ መመሪያ ተቀምጧል።

2. የመሠረተ ልማት መስፈርቶች

ክለቦች ለደጋፊዎቻቸው በቂ አገልግሎት የሚሰጥ እና ለሚድያ ሰዎች አመቺ ቦታ ያለው ስታዲየም እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የስልጠና ማዕከል ሊኖራቸው ይገባል። ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹ እና በበቂ ሁኔታ የተደራጀ ስታዲየም ደጋፊዎች የተሟላ እና አዝናኝ የጨዋታ ቀን እንዲያሳልፉ ይረዳል።

3. የሰው ሐይል እና አስተዳደራዊ መስፈርቶች

በመሠረታዊነት የአንድ በትክክል ፕሮፌሽናል የሆነ ክለብ ፋይናንስ፣ ማርኬቲንግ፣ መዝናኛ፣ ሚድያ፣ ህግ፣ ሰው ሐይል አስተዳደርን የመሳሰሉ ክፍሎቹ ፕሮፌሽናል በሆኑ እና ሰፊ እውቀት ባላቸው ሰዎች መመራት አለበት። ይህ መስፈርትም ክለቦች በቂ እውቀት ያላቸው ሰራተኞችን ቀጥተኛ በሆነ ቅጥር ወይንም በአማካሪነት ማሰራት እንዳለባቸው ይገልፃል።

4. ህጋዊ መስፈርቶች

የህጋዊ መስፈርቶች አላማ በአንድ ውድድር የሚሳተፉ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ክለቦች በአንድ አካል ንብረትነት፣ አስተዳደር ወይንም ተፅእኖ ስር እንዳይሆኑ በማድረግ ውድድሩ ከአሠራር ችግሮች የነፃ እንሆን ማስቻል ነው። በዚህ መመሪያ መሰረትም አንድ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይንም የመንግስት አካል ከአንድ በላይ ክለቦችን በባለቤትነት አልያም በአስተዳዳሪነት ሊያንቀሳቅስ አይችልም። ወደ ሐገራችን ስንመጣ




ደግሞ ለምሳሌ የክልል መንግስታት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ክለቦችን በቀጥተኛ ባለንብረትነት ወይንም አስተዳዳሪነት መምራት እንደማይችሉ ህጉ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክለቦች ግልፅ የሆነ የንብረትነት እና አስተዳደር አደረጃጀት ሊኖራቸው እንደሚገባ እንዲሁም እግርኳስ ነክ የሆኑ ክሶች በመደበኛ ፍርድ ቤት እንዳይታዩ የሚከለክለውን ጨምሮ የሚሳተፉበት ውድድር ህጎችን የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

5. የፋይናንስ መስፈርቶች

ይህ ክፍል ክለቦች ግልፅ እና ተቀባይነት ያለው የፋይናንስ አሠራር መዘርጋት ይገባቸዋል ሲል ቅድመ ሁኔታዎችን ያስቀምጣል፡፡ የፋይናንስ አስተዳደርን ዘመናዊ በማድረግና ወጪና ገቢን በአግባቡ መዝግቦ በመያዝ ክለቦች የፋይናንስ መረጋጋትን (Financial Stability) ማምጣት ከመቻላቸውም በላይ ገንዘብ ለጋሾቻቸውን እና የክለቡ ባለቤቶችን ከትችት ማዳን ይችላሉ፡፡

**የመስፈርቶቹ አስፈላጊነት**

ከላይ የተገለፁት አምስት ክፍሎች እያንዳንዳቸው የተለያዩ መስፈርቶችን የያዙ ሲሆን እያንዳንዱ መስፈርትም እንዳስፈላጊነቱ ቅደም ተከተል A፣ B ወይንም C ተብሎ ይመደባል፡፡ A እና B የተባሉት ምድቦች በውስጣቸው ክለቦች እንዲተገብሯቸው ግዴታ ያለባቸውን (Mandatory) መስፈርቶች የሚይዙ ሲሆን በሶስተኛው (C) ምድብ ደግሞ ክለቦች ለመተግበር ግዴታ የሌለባቸው ነገር ግን የሚበረታቱ፣ ወደፊትም ግዴታ ሊሆኑ የሚችሉ "ጥሩ ልምዶች" ይካተታሉ፡፡

"A" መስፈርቶች (ግዴታ)፡- ክለቦች እነኚህን መስፈርቶች ማሟላት ካልቻሉ በውድድሮች ለመሳተፍ ፈቃድ አያገኙም፡፡ ለምሳሌ በስፖርታዊ መስፈርቶች ስር ክለቦች ከ15-21 ዓመት እንዲሁም ከ10-14 ዓመት ባሉት የእድሜ ክልሎች በእያንዳንዳቸው ቢያንስ አንድ የወጣት ቡድን ማቋቋም እንዳለባቸው የሚገልፀውን ድንጋጌ የማያከብሩ ከሆነ ካፍ በሚያዘጋጃቸው የቻምፒየንስ ሊግ እና ኮንፌዴሬሽንስ ካፕ ተሳታፊ መሆን አይችሉም፡፡

"B" መስፈርቶች (ግዴታ)፡- ምንም እንኳን እኚህ መስፈርቶችም እንዲፈፀሙ ግድ የሚሉ ቢሆኑም ክለቦች መስፈርቶቹን ማሟላት ባይችሉ እንኳን ቅጣት ተጥሎባቸው በውድድሮቹ እንዲሳተፉ እድል ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ በመሠረተ ልማት መስፈርቶች ስር የተቀመጠውን የተሟላ ስታዲየም መኖር እንዳለበት የሚገልፀው ደንብ ስር "ስታዲየሞች በቂ እና ንፁህ የሆኑ የመፀዳጃ ቤቶች ሊኖሯቸው ይገባል፣" የሚለው አንቀፅ በ'B' ምድብ የሚካተት ሲሆን ክለቦች በዚህ ደረጃ የማይገኝ ስታዲየም ካላቸው በካፍ ውድድሮች መሳተፍ የሚችሉ ቢሆንም በሃገራቸው የሚያደርጓቸውን ጨዋታዎች በሌሎች ስታዲሞች እንዲያከናውኑ ይገደዳሉ፡፡

"C" መስፈርቶች፡- ክለቦች እነዚህን መስፈርቶች ማሳካት ባለመቻላቸው የቅጣት ወይንም ከውድድር የመታገድ ዕጣ ባይደርሳቸውም ወደፊት ግዴታ መሆናቸው ስለማይቀር መስፈርቶቹን ለማሟላት ጥረት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡፡ በመሠረተ ልማት መስፈርቶች ስር ስታዲየሞች ቁጥር ያላቸው ወንበሮች እና ዘመናዊ የትኬት አቆራረጥ ዘዴ ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚገልፀው መመሪያ በዚህ ምድብ ውስጥ ይካተታል፡፡

በክለቦች ምዝገባ አሠራር ስር በአንድ ውድድር ለመሳተፍ የሚፈልግ ቡድን ወደ ፌዴሬሽን ቀርቦ ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለክታል፡፡ ፌዴሬሽንም ክለቡ የተቀመጡትን መስፈርቶች እንደሚያሟላ ካረጋገጠ በኋላ የፈቃድ ሰርተፊኬት የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ክለቦች ያቀረቡት የፈቃድ ጥያቄ ያላግባብ ውድቅ ተደርጎብኛል ብለው ካመኑ ይግባኝ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

**የክለቦች ምዝገባ አሠራር ጥቅም**

ይህ አዲስ አሠራር ለክለቦች፣ ተጫዋቾች እንዲሁም ደጋፊዎች በርካታ ጥቅሞችን የሚሰጥ ሲሆን በመመሪያው ላይ የተገለፁት ፋይዳዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

**ለክለቦች**

- የእግርኳስ ክለቦች እና ውድድሮች አስተዳደር ፕሮፌሽናል እንዲሆን ያደርጋል፡፡
- የፋይናንስ ምንጭ እና መረጋጋትን ይፈጥራል፡፡
- የክለቦች ፋይናንስ፣ ንብረትነት እና አስተዳደር ግልፅ (Transparent) እንዲሆን ያደርጋል፡፡
- የክለብ ውድድሮች ከብልሹ አሠራር የፀዱ እንዲሆኑ በማድረግ ተአማኒነትን ይፈጥራል፡፡
- ስፖርታዊ እሴቶችን ያጎለብታል፡፡

**ለተጫዋቾች**

- የወጣቶች ስፖርታዊ እና ስፖርታዊ ያልሆኑ ስልጠናዎች እንዲጠናከሩ ይረዳል፡፡
- ከክለቦች ጋር ያላቸውን የኮንትራት እና ህጋዊ ግንኙነቶች ግልፅ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
- የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን ያረጋግጣል፡፡

**ለደጋፊዎች**

- ደህንነታቸው የተጠበቀ ስታዲየሞች ውስጥ በምቾት ጨዋታዎችን እንዲከታተሉ ያስችላል፡፡
- ማራኪ የሆኑ የእግርኳስ ውድድሮች እንዲፈጠሩ ይረዳል፡፡

በአስገራሚ ሁኔታ በአፍሪካ ክለቦች ውድድር ለመሳተፍ አስፈላጊ ቅድመ




ሁኔታ የሆኑትን መስፈርቶች የኢትዮጵያ ክለቦች በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ አያሟሉም፡፡ ከላይ በምሳሌነት እንደተገለፀው አብዛኛዎቹ ክለቦች በአሁኑ የውድድር ዓመት በተጀመረው ከ17 ዓመት በታች ፕሪምየር ሊግ ምክኒያት አንድ የወጣት ቡድን ቢኖራቸውም ከ10-14 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ በክለቦች ስር የሚገኝ ቡድን የለም፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የታዳጊ ወጣቶች አካዳሚ ለማቋቋም በሂደት ላይ ቢሆንም ግንባታው በመዘግየቱ እስካሁን ስራ ሊጀምር አልቻለም፡፡ ከ17 አመታት በፊት ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎችን በመያዝ የተመሠረተው ደደቢትም ቢሆን ወደ ፕሪምየር ሊጉ ካደገ በኋላ ወጣቶችን ከታች ከማሳደግ ይልቅ ብዙ ገንዘብ በማውጣት ታዋቂ ተጫዋቾችን በማዘዋወሩ ተጠምዷል፡፡ በዚህ አዲስ አሠራር ግን ክለቦች በአፍሪካ ውድድሮች ለመሳተፍ የግድ በታዳጊ ተጫዋቾች ላይ መስራት ስላለባቸው በኢትዮጵያ እግርኳስ ላይ በተደጋጋሚ የሚነሳውን የተተኪዎች እጥረት በመጠኑ ሊያቃልል ይችላል፡፡

ዘንድሮ በፕሪምየር ሊጉ የሚገኙት 7 የአዲስ አበባ ክለቦች በመሠረተ ልማት መስፍቶች ላይ የተቀመጡትን ዝቅተኛ ቅድመ ሁኔታዎች በመጠኑም ቢሆን በሚያሟሉት የአዲስ አበባ እና አበበ በቂላ ስታዲየሞች እየተጫወቱ ቢገኙም በክልሎች ግን ደረጃቸውን የጠበቁ ስታዲየሞች ለማግኘት ይቸግራል፡፡ ለምሳሌ ከላይ በምስሉ ላይ የሚታየው የአርባምንጭ ስታዲየም የመልበሻ ክፍል እና የመፀዳጃ ቤት እንኳን የሌለው ሲሆን ይህ ችግር በብዙዎቹ የክልል ሜዳዎች የሚታይ ነው፡፡ የዚህ መመሪያ መተግበር በዚህ ዘርፍም መሻሻል ሊያመጣ እንደሚችል የታመነ ነው፡፡

በመጨረሻም መመሪያው በሰው ሐይል እና አስተዳደራዊ ክፍል ላይ እንዳስቀመጠው ክለቦች ፋይናንስ፣ ማርኬቲንግ፣ መዝናኛ፣ ህዝብ ግንኙነት...... በመሳሰሉት ዘርፎች ሰፊ ዕውቀት ባላቸው ፕሮፌሽናል ሰዎች መመራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የስፖርት አመራር ዕውቀት የሌላቸው የድርጅት እና የመንግስት አካል ሃላፊዎች በትርፍ ጊዜያቸው የሚመሯቸው ክለቦች ለበዙበት የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ መልካም ዜና የሚባል ነው፡፡

የክለቦች ምዝገባ አሠራር በቅድሚያ በአፍሪካ እግርኳስ ኮንፌዴሬሽን በሚዘጋጁ ውድድሮች በተደጋጋሚ ተሳታፊ በሚሆኑ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ደደቢት፣ ኢትዮጵያ ቡና ባሉ ትልልቅ ክለቦችን የሚተገበር ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ነገርግን ካፍ ባስቀመጠው የረጅም ጊዜ እቅድ ወደፊት መመሪያውን ማሟላት የማይችሉ ክለቦች በሀገር ውስጥ ውድድሮችም መሳተፍ እንደማይችሉ ይፋ አድርጓል፡፡ ስለዚህ አሠራሩ ለእግርኳሳችን ሊያመጣ ከሚችለው ጠቀሜታ አንፃር ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክለቦች ይተገበር ዘንድ ቀነ ገደብ አስቀምጦ ወደ ተግባር መግባቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ለሚደረገው ጉዞ ወሳኝ ነው፡፡



# የአሸዋ ሜዳ እንቁዎች

## አሸናፊ ግርማ እና ዮርዳኖስ አባይ

አንደኛው በግብ ማስቆጠር ብቃቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለትና "ኢትዮጵያ እንደሱ አይነት አጥቂ አፍርታ አታውቅም" የተባለለት ታላቅ አጥቂ ነበር። ሌላኛው ደግሞ ጣልያኖች ‹‹ mystero ›› የሚሉት አይነት የበቃ አማካይ ነበር። የሁለቱ የቀድሞ የኢትዮጵያ ወጣት ቡድን አውራዎች ከድሬዳዋ ተነስተው እስከ ፕሪምየር ሊግ ንግስና ድረስ ወርቃማ የእግርኳስ ህይወት አሳልፈዋል። የሶከር ኢትዮጵያው አብርሃም ገብረማርያም ዘንድሮ ከእግርኳስ አለም ራሳቸውን ያገለሉትን የሁለቱን ድንቅ ተጫዋቾች ታሪክ እንዲህ አጠናቅሮታል፡፡



ዮርዳኖስ አባይ እና አሸናፊ ግርማ በኢትዮጵያ ቡና ማልያ - 1995

### አሸናፊ ግርማ

#### አወዛጋቢው የመሃል ሜዳ ንጉስ

በወርቃማ ዘመናቱ ስሙ ቀድሞ የሚጠራ ኮከብ ነበር፡፡ ‹‹ሳቪዮላ›› በተመጠኑ ረጅም እና አጭር ኳሶቹ፤ በመሃል ሜዳ ሞተርነቱ እንዲሁም ከአማካይ እየተነሳ በሚያስቆጥራቸው ግቦች ይታወቃል፡፡ የጋዜጣ ርእስ አድማቂ ከሆኑ ጥቂት "celebrity" ተጫዋቾችም ግንባር ቀደሙ ነበር፡፡

አሸናፊ ግርማ የተገኘው ባለክህሎት ተጫዋቾች እንደ አሸን ከሚፈሉባት ድሬዳዋ ነው፡፡ ለወላጆቹ የመጀመርያ ልጅ የሆነው አሸናፊ ታሪክ የሚጀምረው እንደ አመዛኙ ኢትዮጵያዊ በድህነት ውስጥ በማደግ ነው፡፡ ‹‹ተወልጄ ያደግኩት ድሬዳዋ ነው፡፡ በቤታችን እኔን ጨምሮ 6 ልጆች እንኖር ነበር፡፡ እናቴ የቤት እመቤት ስትሆን አባቴ በፋብሪካ ውስጥ ሙያተኛ ነው፡፡ አባቴ በስራው ታታሪ፣ ጠንካራ እና ብርቱ ነው፤ አሁንም ድረስ ይሰራል፡፡›› ይላል አሸናፊ ስለ ቤተሰቡ ሲናገር፡፡

በድሬዳዋ ተወልዶ ያደገ ልጅ እግር ኳስን በአሸዋ ሜዳ ሳይጫወት የልጅነት ጊዜውን ያሳልፋል ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ አሸናፊም በርካቶች ያጨበጨቡለትን የኳስ ክህሎት ያገኘው በአሸዋ ሜዳ ነው፡፡ ነገር ግን ቀጫጫው አማካይ የኋላ ኋላ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ላይ ስሙን በደማቅ ቀለም ያፅፍ እንጂ በልጅነቱ በተክለ ሰውነቱ ምክንያት ብዙ ተፈትኗል፡፡ ከቡድን ጓደኞቹ እስከ ክለብ አሰልጣኞች ድረስ እሱ ላይ ያላቸው እምነት በተክለ ሰውነቱ ምክንያት ስህተት ውስጥ መግባታቸው ሁሌጊዜም ያንገበግበው ነበር፡፡ አሸናፊ ስለ ልጅነት

> እኔ አሸናፊ ግርማ ነኝ፤ ታውቁኛላችሁ። ተፈልጌ እና ተለምኜ ነው እዚህ የመጣሁት... በችሎታ ደግሞ ሁላችሁንም እበልጣችኋለሁ። ስለ እኔ እየተንሾካሾካችሁ ማውራታችሁን አቁሙ። እዚህ ክለብ ውስጥ ተጫዋች በአፉ እንጂ በችሎታው አይደለም የሚሰለፈው። ደግሞም በዛሬው ጨዋታ መቀየር አልነበረብኝም።

ጊዜው ሲያስታውስ እንዲህ ይላል፡፡ "መጀመርያ ወደ ክለብ ለሙከራ የሄዴኩት ወደ ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ (ኮተን) ነው፡፡ ምርጫ አለ ተብሎ ስለተነገረ ከጓደኞቼ ጋር ተያይዘን ወደ ኮተን አመራን፡፡ ነገር ግን በዚያ መልካም ነገር አላጋጠመኝም፡፡ አሰልጣኙ የእግሬን ቅጥነት ተመልክቶ አንድም የሙከራ ጨዋታ ሳላደርግ አባረረኝ፡፡ በዛን ወቅት ከኮተን ሜዳ እስከ ቤቴ ዴረስ በእግሬ እያለቀስኩ ተመለስኩ፡፡ ከዛ አጋጣሚ በኋላ በርካታ ክለቦች ጋር ለሙከራ ብሄድም በቅጥነቴ የተነሳ ተቀባይነት አለማግኘቴ ተስፋ አስቆርጦኝ ነበር፡፡"

በትልልቅ ክለቦች ተስፋ የቆረጠው አሸናፊ በችሎታው ለማሳመን በዝቅተኛ ዲቪዝዮን ወደሚወዳደረው ሶጂክ ክለብ አመራ፡፡ በወቅቱ ለድሬዳዋ ምርጥ ተጫዋቾችን ለመምረጥ በተካሄደው የአጎራባች ክልሎች ሻምፒዮናም ድንቅ አቋሙን አሳየ፡፡ ክህሎቱን ሳያዩ በቅጥነቱ ምክንያት ያባረሩትን በሙሉ በግርምት አፍ አስያዘ፡፡ በሙከራ ወቅት አሸማቆ ያባረረው የድሬዳዋው ታሪካዊ ክለብ ጨርቃ ጨርቅ ወድያውኑ አሸናፊን ለማስፈረም ጥያቄ አቀረበ፡፡ "ያኔ ያባረረኝ አሰልጣኝ አሁን እንደሚፈልገኝ ነገረኝ፡፡ እኔን በቶሎ መርሳቱ አስገርሞኛል፡፡ በበርካታ ክለቦች በመፈለጌ ኮተኖች 150 ብር እና ምግብ እንዲሁም የህክምና ወጪ እንደሚሸፍኑልኝ ቃል ገቡልኝ፡፡ ገንዘቡ እጅግ ብዙ ቢሆንም ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ካለው የገዘፈ ስም አንፃር በ50 ብርም ቢሆን ብጫወት ቅር አይለኝም ነበር፡፡"

> "ከ3 ቀን በፊት በቅዱስ ጊዮርጊስ ማልያ የተመለከቱኝ ደጋፊዎች ወደ ሜዳ ስገባ እቀፍ አበባ ይዘው 'እንኳን ደህና መጣህ፤ በቡና ማልያ ግርማ ሞገስ አለህ፤ እንወድሃለን' እያሉ አቀባበል አደረጉልኝ፡፡ እንባ እየተናነቀኝ ሰላም አልኳቸው፡፡"

በ1990 የውድድር ዘመን በድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ያሳየው ድንቅ አቋም ወደ መድን እንዲዘዋወር እና ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን እንዲጠራ በር ከፍቶለታል፡፡ በሰማያዊዎቹ ለ1 የውድድር ዘመን ብቻ ከቆየ በኋላ በ1992 የእግር ኳስ ህይወቱን ከፍ ወዳለ ምዕራፍ ወዳሸጋገረበት ኢትዮጵያ ቡና አመራ፡፡

አሸናፊ የኢትዮጵያ ቡናን ማልያ መልበስ የምኞቶቹ ሁሉ ጫፍ ነበር፡፡ በአጨዋወታቸው የተማረከው ትንሹ ልጅ በመድን ቆይታው እንኳን የኢትዮጵያ ቡናን መዝሙር እየዘመረ በአመራሮቹ እና በቡድን አባላቱ ለትዝብት ተዳርጓል፡፡ አሸናፊ በጊዜው የነበረውን ሂደት እንዲህ ያስታውሰዋል፡፡ "ቡና ብገባ የእግርኳስ ጥማቴን እንደማረካ አውቀዋለሁ፡፡ ለክለቡ የነበረኝ ፍቅር ከልብ የመነጨ ነበር፡፡ መድን እያለሁ ምሳ

አማካዩ ባለፈው ዓመት ለንባብ በበቃው የግል ህይወቱን የሚዳስስ መፅሃፍ የአወዛጋቢው ተጫዋች ህይወት ተዳሷል፡፡ በዚህ ፅሁፍ የተካተቱት የተጫዋቹ ንግግሮች በሙሉ የተወሰዱትም ከዚሁ መፅሃፍ ሲሆን ለሶከር ኢትዮጵያ በሚመች መልኩ ቀርቧል፡፡

በምንመገብበት ሰዐት ሹካ እና ማንኪያውን እያጋጨሁ 'ቡና ገበያ አደገኛ' እያልኩ እዘምር ነበር፡፡ ቡና እኔን ለማስፈረም ጥያቄ ሲያቀርብ ሁለቱ አላሰብኩም፡፡ በጊዜው መድን 25ሺህ ብር የኮንትራት ማራዘምያ ቢያቀርብልኝም የአደገኞቹ 8ሺህ ብር በልጦብኝ ለኢትዮጵያ ቡና ፈረምኩ፡፡ በወቅቱ የተስማማሁት በ8ሺህ ብር ቢሆንም ቡና ቤት ውስጥ ምንም ገንዘብ አልነበረም፡፡ ኋላ ላይ ስራ አስኪያጁ አቶ ፀጋዬ ሽዋረጋ 3ሺህ ብር ከኪሳቸው ሰጥተውኝ መጫወት ጀመርኩ፡፡"

1993 የአሸናፊ ዓመት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከኢትዮጵያ ቡና ጋር የቡድን ስኬት ባያስመዘግብም በግሉ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የአመቱ ኮከብ ተጫዋች ተብሎ ተመረጠ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከኢትዮጵያ ወጣት ቡድን ጋር የማይረሳ ዓመትን አሳለፈ፡፡ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በተካሄደው የ2001 የአፍሪካ ወጣቶች ዋንጫ ኢትዮጵያ ግማሽ ፍፃሜ ድረስ እንድትደርስ ዋናውን ሚና ተወጣ፡፡ ኢትዮጵያም በታሪኳ ለመጀመርያ ጊዜ ለአለም ከ20 አመት በታች ዋንጫ አለፈች፡፡ አሸናፊ በሁሉም ኢትዮጵያውያን አፍ የሚጠራ ስም መሆን የጀመረውም ያኔ ነበር፡፡

### ጉዞ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ

የአሸናፊ የእግር ኳስ ህይወት አወዛጋቢ ገፅታም አለው፡፡ ሜዳ ላይ ተነጫናጭ እና ግልፍተኛ ባህርይ ያለው አማካዩ 1993 የህይወቱ ወሳኝ ወቅት ነበር፡፡ ግብፅ ላይ ፍፁም ቅጣት ምት በመሳቱ የኢትዮጵያን ወደ ግማሽ ፍፃሜ የማለፍ ተስፋ የደበዘዘ ቢመስልም በመጨረሻው የምድብ ጨዋታ ኢትዮጵያ ደቡብ አፍሪካን 4-1 ስትረታ ድንቅ አቋሙን ሲያሳይ ከህዝብ ወቀሳ ተረፈ፡፡ ክረምት ደርሶ የተጫዋቾች የዝውውር መስኮት ሲከፈት ደግሞ አሸናፊ ተመልሶ የእግር ኳስ አፍቃሪያን መነጋገርያ ሆነ፡፡ ባለ አስደናቂ ክህሎቱ አሸናፊ የሁሉም ክለቦች አይን ማረፍያ ቢሆንም በመጨረሻ የቅዱስ ጊዮርጊስ ንብረት መሆኑ አወዛጋቢም አነጋጋሪም ነበር፡፡

"ከአርጀንቲናው የአለም ከ20 አመት በታች ሻምፒዮና እንደተመለስኩ ብዙ ክለቦች እኔን ለመውሰድ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ኢትዮጵያ ቡና እውቅና ያገኘሁበት ክለብ በመሆኑ መልቀቅ አልፈለግኩም ነበር፡፡ ለእረፍት ወደ ድሬዳዋ በሄድኩበት ወቅት የቤተሰቤን የአኗኗር ሁኔታ፣ የአባቴ እርጅና መጫጫን እና የተጎሳቆለውን መኖርያ ቤታችን ሁኔታ ስገነዘብ ኢትዮጵያ ቡናን ለመልቀቅ ወሰንኩ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለፊርማ ያስቀመጠልኝ 30ሺህ ብር እጅግ በጣም ብዙ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቡናን መልቀቅ ከባድ ቢሆንብኝም አደረግኩት፡፡"

አሸናፊ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቋሚ ቦታን ለማግኘት ባይቸገርም በፈረሰኞቹ ደጋፊዎች



እጅግ የሚወደደው እና ከወጣት ቡድኑ ያደገው ሙሉአለም ረጋሳ ተጠባባቂ እንዲሆን መደረጉ ቆይታውን ውስብስብ አደረገው፡፡ አሸናፊ በወቅቱ የሃገሪቱ ቁጥር አንድ አማካይ ቢሆንም ሙሉአለም ወደ ተጠባባቂ ወንበር እንዲወርድ ምክኒያት መሆኑ ሁኔታዎችን አስቸጋሪ እንዳደረገበት ይናገራል፡፡ "ክለቡን በተቀላቀልኩኝ በኋላ በአጭር ጊዜ አንዳንድ ተጫዋቾች በኔ ዝና እና ችሎታ መዋጣቸውን አልወደዱትም፡፡ አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅን ለመግጠም ሄደን ነጥብ ስንጥል ተቀይሬ ወጣሁ፡፡ በጨዋታው ጥሩ ከመሆኔ የተነሳ የአርባምንጭ ደጋፊዎች ስሜን እየጠሩ ሲያሞካሹኝ ነበር፡፡ ተቀይሬ መውጣቴ እጅግ አበሳጭቶኝ ስለነበር በሰርቪስ ውስጥ ድምፄን ከፍ አድርጌ መናገር ጀመርኩ፣ 'እኔ አሸናፊ ግርማ ነኝ፣ ታውቁኛላችሁ፡፡ ተፈልጌ እና ተለምኜ ነው እዚህ የመጣሁት... በችሎታ ደግሞ ሁላችሁንም እበልጣችኋለሁ፡፡ ስለ እኔ እየተንሾካሾካችሁ ማውራታችሁን አቁሙ፡፡ እዚህ ክለብ ውስጥ ተጫዋች በአፉ እንጂ በችሎታው አይደለም የሚሰለፈው፡፡ ደግሞም በዛሬው ጨዋታ መቀየር አልነበረብኝም' ብዬ አሰልጣኝ ስዩም ከበደ ፊት አምባረቅሁ፡፡ 'እኔ የድሬ ልጅ ነኝ፣ ነገሮችን በግልፅ መናገር የምፈልግ ሰው ነኝ፡፡ ተደብቆ በማውራት የእግርኳስ ችሎታ ሊገኝ አይችልም' ብዬ ስም ጭምር እየጠቀስኩ ተናገርኩ፡፡ከአርባምንጭ መልስ ከወንጂ ጋር አዲስ አበባ ስታዲየም ስንጫወት የኢትዮጵያ ቡና ደጋፊዎች በእኔ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለፅ ስታዲየም መጡ፡፡ 'በጊዮርጊስ ማሊያ አታምርም፣ ተመለስ' ሲሉ ይሰማኛል፡፡ በጨዋታው ቋሚ አሰላለፍ ውስጥ አልገባሁም ነበር፡፡ እጅግ ተበሳጭቼ ክለቡን መልቀቅ እንዳለብኝ ወሰንኩ፡፡ የመጀመርያው አጋማሽ ሳይጠናቀቅ ከተጠባባቂ ወንበር ተነስቼ በፍጥነት ወደ ፌዴሬሽኑ ፅህፈት ቤት በማምራት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ያለኝን ኮንትራት ማፍረስ እንደምፈልግ በማመልከቻ መልክ አስታወቅሁ፡፡"

### ወደ ቤት መመለስ

ከብዙ ውዝግቦች በኃላ በ3 ጨዋታዎች ብቻ የተገደበው የቅዱስ ጊዮርጊስ እና አሸናፊ ግርማ ፍቺ እውን ሆነ፡፡ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ተለያይቶ ወደ ኢትዮጵያ ቡና የተመለሰበትን ሂደት አሸናፊ እንዲህ ያስታውሰዋል፡፡

"ከወንጂው ጨዋታ በኋላ ሻንጣዬን ይዤ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ካምፕ ስወጣ አሸናፊ ሲሳይ አስቁሞ ክለቡን እንዳልለቅ ተማፀነኝ፡፡ ነገር ግን ከዚህ በላይ በዚህ ክለብ መቆየት እንደማልችል እና ውሌን እንዲፈርስኩ ነግሬው ሃሳቡን ውድቅ አደረግኩት፡፡ በነጋታው ውል ማፍረሴን የሰሙ የቡና ደጋፊዎች ለጊዮርጊስ የምመልሰውን ብር ማዋጣት ጀመሩ፡፡ ሁሉም ነገር በዛው ምሽት ተጠናቀቀ፡፡ እሁድ ከመብራት ኃይል ጋር ለምናደርገው ጨዋታ መልቀቂያዬን አገኘሁ፡፡ ብዙዎቹ መመለሴን ቢሰሙም ስጫወት እስኪያዩኝ ድረስ ጭራሽ አላመኑም ነበር፡፡ ከ3 ቀን በፊት በቅዱስ ጊዮርጊስ ማልያ የተመለከቱኝ ደጋፊዎች ወደ ሜዳ ስገባ እቅፍ አበባ ይዘው 'እንኳን ደህና መጣህ፣ በቡና ማልያ ግርማ ሞገስ አለህ፣ እንወድሃለን' እያሉ አቀባበል አደረጉልኝ፡፡ እንባ እየተናነቀኝ ሰላም አልኳቸው፡፡"

አሸናፊ ወደ አደገኞቹ ቤት ከተመለሰ በኋላ ለ5 የውድድር ዘመናት ቆይቶ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግን ዋንጫ ለማንሳት ባይታደልም 2 የኢትዮጵያ ዋንጫን (ጥሎ ማለፍ) አሸንፏል፣ ከብሄራዊ ቡድኑ ጋር 3 የሴካፋ ዋንጫ ያገኘውም በኢትዮጵያ ቡና ተጫዋችነቱ ነው፡፡ በግሉ በ1993 እና 1995 የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ኮከብ ተጫዋች ተብሎ የተመረጠውም በኢትዮጵያ ቡና ማልያ ባሳየው ድንቅ አቋሙ ነው፡፡ በ1998 ከክለቡ አመራሮች እና አሰልጣኞች ጋር በገባው ቅራኔ ምክንያት ከቡና ጋር ተለያየ፡፡ አሸናፊ በወቅቱ ኢትዮጵያ ቡናን የለቀቀበት መንገድ ያበሳጨዋል፡፡

"በቡና ከተደላደልኩ እና አምበል ከሆንኩ በኋላ አሰልጣኝ ክፍሌ ቦልተና እና አብርሃም ተ/ኃይማኖት እኔን ለማስወጣት የነበራቸው እቅድ ተሳክቶ ለ6 ወር እንድቀጣ አደረጉ፡፡ ከካምፕ እንድወጣ ከመታዘዜ በተጨማሪ የደሞዜ 2/3ኛ ተቀነሰ፡፡ የታገድኩት ለረጅም ጊዜያት በመሆኑ በእረፍት መልክ ገዳማትን መዞር ጀመርኩ፡፡ አንድ ቀን ባህርዳር ሆኜ የየመኑ አል ሻህብ ሙክላ ሊያዘዋውረኝ እንደሚፈልግ በስልክ አሳወቁኝ፡፡ ከኢትዮጵያ ቡና ጋር ተስማምተው ቅጣቴ ተነስቶ አስፈረሙኝ፡፡ ነገር ግን በየመኑ ክለብ የቆየሁት ለ6 ወራት ብቻ ነው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ መቶ አለቃ ፈቀደ ማሞ ክለቡ እንደሚፈልገኝና ኮንትራቱም ስላለቀ መጫወት እንዳለብኝ ነገሩኝ፡፡ ለ3ኛ ጊዜ በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ቡና ተመለስኩ፡፡ ለ1998 የኢትዮጵያ ዋንጫ ፃሜ ከመከላከያ ጋር ለመጫወት ተዘጋጀን፡፡

ዋንጫውን እንደምናገኝ እርግጠኛ ከመሆኔ የተነሳ 5 ሻምፓኝ በቦርሳዬ ይዤ ወደ ስታዲየም ገባሁ። በጨዋታው መከላከያ 1-0 ሲመራ የጊዮርጊስ ደጋፊዎች እኔን ማብሸቅ ጀመሩ። ጨዋታው በመከላከያ አሸናፊነት ከተጠናቀቀ በኋላ እጅግ ተበሳጭቼ ቁምጣዬን በማውለቅ ደጋፊዎችን ተሳደብኩ። ድርጊቴ እንደሚያስቀጣኝ ባውቅም በእለቱ ከመጠን በላይ ስሜታዊ ሆኜ ነበር። በእለቱ ድርጊት ክለቤ እና ፌዴሬሽኑ ቀጡኝ። በኋላ ላይ ፌዴሬሽኑ ቅጣቴን ቢያነሳልኝም ኢትዮጵያ ቡና ቅጣቴን አንስተው ወደ ቡድኑ እንድቀላቀል አልፈለጉም። ወዲያው መብራት ኃይል የ1 ዓመት ኮንትራት አቅርቦልኝ ወደዛ አመራሁ። 1999 በፌዴሬሽኑ እና በክለቦች ውዝግብ ምክንያት ውድድር ብዙም ያልተደረገበት በመሆኑ በመብራት ኃይል ብዙም ሳልጫወት ኮንትራቱ አበቃ።"

አሸናፊ ከኢትዮጵያ ቡና ከወጣ በኋላ መረጋጋት አልቻለም። ጫማውን እስከሰቀለበት ጊዜ ድረስ የመብራት ኃይል፣ ሜታ ቢራ፣ አየር ኃይል እና ድሬዳዋ ከነማን ማልያ ለብሷል። በ2002 በኤፊ ኦኑራ እምነት አግኝቶ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንን ቢያገለግልም በክለብ ደረጃ የሚጠቀስ ተፅእኖ ማሳረፍ አልቻለም። ሊታወስ የሚችል ነገር ቢኖር 2001 ለድሬዳዋ ከነማ ሲጫወት ኢትዮጵያ ቡና ላይ ግብ አስቆጥሮ ቢጫውን የቡና ማልያ የሳመበት ክስተት ነው።


## ዮርዳኖስ አባይ

### ግብ ማግባትን ከዘር የወረሰው

የድሬዳዋ ከተማ ደቻቱ መንደር ላይ የተንጣለለው አሸዋ ሜዳ ከኢትዮጵያ እግርኳስ ጋር በሰፊው የተቆራኘ ስፍራ ነው። ከ1950ዎቹ የጥጥ ማህበር ንግስና ጀምሮ በኢትዮጵያ ሻምፒዮናና ፕሪሚየር ሊግ በችሎታቸው ተመልካችን ቁጭ ብድግ ያደረጉ ድንቅ የድሬዳዋ ተጫዋቾች መነሻ ይኸው የአሸዋ ሜዳ ነው። አሸዋ ሜዳ በርካታ ከዋክብትን ቢያፈራም የዚህ ቤተሰብ ዳግሞ የተለየ ነው። የአባይ ቤተሰብ...ይህ ቤተሰብ ከአንዱ ወደ ሌላው የቤተሰብ አባል በተሸጋገረ ዝና እና ችሎታቸው እያደገ በመሄድ ፒራሚድ ይመስላል። አባይ - ስምኦን - ዮርዳኖስ አባትየው አባይ ጌታሁን በ1960ዎቹ በድሬዳዋ ጥጥ ማህበር ስማቸው ጎልቶ የሚጠራ ድንቅ አጥቂ ነበሩ። የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ኮከብ ግብ አግቢ ከመሆናቸው በተጨማሪ ከክለባቸው ጋርም የኢትዮጵያ ሻምፒዮናን አሸንፈዋል። የመጀመርያ ልጃቸው ስምኦን አባይ ለመብራት ኃይል እና ኢትዮጵያ ቡና የተጫወተ ሲሆን ከመብራት ኃይል ጋር የሊጉን ዋንጫ አንስቷል። በምስራቅ እና መካከለኛው አፍሪካ ወጣቶች ውድድርም ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ ያጠናቀቀ ግብ አዳኝ ነው። የስምኦን ታናሽ የሆነው ዮርዳኖስ አባይ ደግሞ ኢትዮጵያ በዘመናዊ የእግርኳስ ታሪኳ ካየቻቸው አስደናቂ አጥቂዎች አንዱ ነው። ለዮርዳኖስ ግቦች ማስቆጠር ቀላል ስራ ነበር፤ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ እንኳን ግብ ለማስቆጠር አይቸገርም። ከቅጣት ምት፣ ከፍፁም ቅጣት ምት ሳጥን ውጪ፣ በአንድ ለአንድ ግንኙነት... በየትኛውም እንቅስቃሴ ከየትኛውም ቦታ ግብ የማስቆጠር ችሎታ ከታደሉ ጥቂት ምርጦች አንዱ ነበር።

ወደ የመን ከተዛወረ 10 አመታትን ቢያስቆጥርም፣ በኢትዮጵያውያን ፊት ከተጫወተ ረጅም አመታት ቢያልፍም አሁንም ድረስ ከኢትዮጵያ እግርኳስ አፍቃሪያን አእምሮ አልጠፋም። እግርኳስ ብዙም በማይከታተሉ ሰዎች ሳይቀር የሚታወቀው መልከ-መልካሙ ዮርዳኖስ በእርግጥም ሊታወስ የሚገባ ታላቅ ተጫዋች ነበር። የ "ቡሎ" እግርኳስ ህይወት የሚጀምረው አብዛኛዎቹ የድሬ ኮከቦች ከጀመሩበት ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ነው። በ1989 ወደ ዋናው የድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ቡድን ያደገው ዮርዳኖስ በዋናው ቡድን ጎልቶ ለመውጣት ጊዜ አልፈጀበትም። ከአንድ አመት በኋላ ለኢትዮጵያ ታዳጊ ቡድን ሲመረጥ በአዲስ አበባ ታላላቅ ክለቦች አይን ውስጥም መግባት ቻለ። ወጣቶችን በማደግ ስም የተከለው መብራት ኃይል በ1991 ክረምት ወጣቱ ዮርዳኖስን እጁ አስገባ። የማይዘሙት ምሰሶዎች እና የቡሎ ወርቃማ ታሪክ መፃፍ የጀመረውም ከዚህ በኋላ ነው። በ1993 የውድድር ዘመን የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ እና የኢትዮጵያ ዋንጫን በጥምር በማሸነፍ ከረጅም ጊዜያት በኋላ የመጀመርያ የሆነ ገድል ሲፈፅሙ ዮርዳኖስ አባይ ከታላቅ ወንድሙ ስምኦን አባይ ጋር በጥምረት 31 ግቦች አስቆጥረው የሊጉ ክለቦች የቀን ቅዠት ሆኑ። በዚህ አመት ዮርዳኖስ በሊጉ ያስቆጠረው 24 ግብ ከ12 አመታት በኋላም ያልተደፈረ የግብ ቁጥር መሆኑ የቡሎን የግብ አነፍናፊነት ታሪክ ይመሰክራል። ከሊግ ሻምፒዮንነት እና ኮከብ ግብ አግቢነት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ወጣት ቡድን ከበርካታ አወዛጋቢ ክስተቶች በኋላ ወደ ዓለም ወጣቶች ዋንጫ እንዲያልፍ ቁልፍ ሚና ከተወጡት ተጫዋቾች አንዱ ሆነ። ደቡብ አፍሪካን 4-1 ባሸነፉበት ልዩ ቀን ግብ ሲያስቆጥር በግማሽ ፍፃሜው በአንጎላ ሲረቱ ከቅጣት ምት ያስቆጠራት ግብ በብዙዎች አእምሮ የምትታወስ ግብ ነበረች። የዮርዳኖስ የግብ ማግባት ጉዞ በአርጀንቲናም አልተገታም። ኢትዮጵያ ሶስቱንም ግጥሚያዎች በሽንፈት ብታጠናቅቅም በግሉ ጥሩ የውድድር ጊዜን አሳልፏል።

1994 የውድድር ዘመን ለመብራት ኃይል



እንደቀደመው ዘመን መልካም ባይሆንም ዮርዳኖስ አስደናቂ አጥቂነቱን በተግባር ያሳየበት የውድድር ዘመን ሆኖ አልፏል። እስከመጨረሻው ጨዋታ ድረስ በምድር ባቡሩ አህመድ ጁንዲ በግብ ቁጥር ተበልጦ የቆየው ዮርዳኖስ ቀደም ብሎ ሻምፒዮንነቱን ባረጋገጠው ቅዱስ ጊዮርጊስ 8-5 ሲሸነፉ 4 ግቦችን አስቆጥሮ በመጨረሻም የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ኮከብ ግብ አግቢነትን ክብር በ20 ግቦች በመውሰድ አጠናቀቀ። በአንድ ጨዋታ 4 ግብ ያስቆጠረበት አስደናቂ ታሪክ በ2002 በታፈሰ ተስፋዬ እስኪሰበር ድረስ በሪከርድነት ቆይቷል። በዚሁ አመት ከሴካፋ ድል ጋር ከሩዋንዳ የተመለሰው ብሄራዊ ቡድን አባል የነበረ ሲሆን ከባዩ ሙሉ ጋር የፈጠሩት የአጥቂ ጥምረት ለድሉ ከፍተኛውን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በ1995 በትዝታ ከተሞሉ ድንቅ የመብራት ኃይል ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያ ቡናን ተቀላቀለ። በአደገኞቹ ቤት አንድ የውድድር ዘመን ብቻ ያሳለፈው ዮርዳኖስ በቆይታው ግብ ለማምረት አልሰነፈም። በ14 ግቦች ከአህመድ ጁንዲ ጋር በጥምረት የሊጉ ኮከብ ግብ አግቢ በመሆን ሲያጠናቅቅ በ3 ተከታታይ አመታት የሊጉ ኮከብ ግብ አግቢ በመሆንም እስካሁን ያልተደፈረ ታሪክ ፃፈ።

ከቡና ቆይታው በኋላ የተጓዘው ወደ የመኑ አል ሳቅር ነው። እዛም በሄደበት የመጀመርያ አመት የሊጉ ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ አጠናቋል። በአል ሳቅር በቆየባቸው 10 አመታትም 112 ግቦች በማስቆጠር የአል ሳቅር የምንግዜም ከፍተኛ ግብ አስቆጣሪነትን ተቆናጥጧል። በየመኑ ክለብ እጅግ የሚከበረውና እንደምንግዜም ጀግና የሚቆጠረው ዮርዳኖስ አባይ በቢጫ እና ጥቁሩ ማልያ እየተጫወተ ዘንድሮ ከእግርኳስ የመለየቱን ውሳኔ ማሳወቁን ተከትሎ በክለቡ ይፋዊ አሸኛኘት ተደርጎለታል።

# የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ

## 1ኛ ሳምንት

ቅዳሜ፣ ጥቅምት 16
ኢትዮጵያ መድን 0-0 አርባምንጭ ከነማ
መከላከያ 3(ማናዬ ፋንቱ፣ ፍሬው ሰለሞን፣ ሐብታሙ መንገሻ) -
ሲዳማ ቡና 1(ቢንያም አድማሱ)

እሁድ፣ ጥቅምት 17
ዳሽን ቢራ 0-0 ሐረር ቢራ
ሐዋሳ ከነማ 1 (ወንድሜነህ ዘሪሁን) -
መብራት ሐይል 2 (በረከት ይስሐቅ፣ ተሾመ ኦሼ)
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 0 ወላይታ ዲቻ 4
(ባዬ ገዛኸኝ፣ ዮሴፍ ደንጊቶ፣ ተስፋዬ መላኩ፣ ሳምሶን ኮሌቻ)

ወደሌላ ጊዜ የተላለፉ ጨዋታዎች
ሙገር ሲሚንቶ ከ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ደደቢት ከ ኢትዮጵያ ቡና

## 2ኛ ሳምንት

እሁድ፣ ጥቅምት 24
መብራት ሐይል 1 (በረከት ይስሐቅ) -
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 3 (ፊሊፕ ዳውዚ×3)
አርባምንጭ ከነማ 0-0 መከላከያ
ሐረር ቢራ 1 (አምሐ በለጠ) -
ኢትዮጵያ መድን 0
ሙገር ሲሚንቶ 1 (አዲሱ አላሮ) -
ዳሽን ቢራ 0

ወደሌላ ጊዜ የተላለፉ ጨዋታዎች
ኢትዮጵያ ቡና ከ ሐዋሳ ከነማ
ሲዳማ ቡና ከ ደደቢት
ቅዱስ ጊዮርጊስ ከ ወላይታ ዲቻ

## 3ኛ ሳምንት

ሐሙስ፣ ህዳር 12
ኢትዮጵያ መድን 0-
ሙገር ሲሚንቶ 1 (አኪም አካንዴ)
ቅዳሜ፣ ህዳር 14
መከላከያ 2 (ፍሬው ሰለሞን፣ በዳሶ ሆራ) -
ሐረር ቢራ 1 (ልይህ ገብረመስቀል)
ዳሽን ቢራ 0-
ቅዱስ ጊዮርጊስ 1 (ኤሳድጆ ዊሊያምስ)
ወላይታ ዲቻ 0-0 መብራት ሐይል
ኢትዮጵያ ቡና 1 (ዳዊት እስጢፋኖስ) -
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1 (ኤሊያስ ማሞ)
እሁድ፣ ህዳር 15
ሐዋሳ ከነማ 1 (አንዱለም ንጉሤ) -
ሲዳማ ቡና 0
ደደቢት 1 (ዳዊት ፍቃዱ) -
አርባምንጭ ከነማ 0

## 4ኛ ሳምንት

ሐሙስ፣ ህዳር 19
ዳሽን ቢራ 0-0 ኢትዮጵያ መድን
ሙገር ሲሚንቶ 0-
መከላከያ 1 (ሲሳይ ደምሴ -ፍ.ቅ.ም)
ኢትዮጵያ ቡና 0-0 ወላይታ ዲቻ
ቅዱስ ጊዮርጊስ 2 (ኡመድ ኡክሪ፣ አዳነ ግርማ)
መብራት ሐይል 0

አርብ፣ ህዳር 20
ሐረር ቢራ 0 -
ደደቢት 3 (መስፍን ኪዳኔ፣ ዳዊት ፍቃዱ፣ ሻኢቡ ጂብሪል)
አርባምንጭ 2 (ተመስገን ዱባ፣ ፍሬው አለማየሁ) - ሐዋሳ ከነማ 1 (አንዱለም ንጉሤ)
ሲዳማ ቡና 1 (አሳምነው አንጀሎ) -
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1 (ታዲዎስ ወልዴ)

## 5ኛ ሳምንት

ማክሰኞ፣ ህዳር 24
ኢትዮጵያ መድን 1 (ወሰኑ ዓሊ - ፍ.ቅ.ም) -
ቅዱስ ጊዮርጊስ 2 (ኡመድ ኡክሪ፣ አዳነ ግርማ)
መብራት ሐይል 1 (ፍሬው ወልደጊዮርጊስ) -
ኢትዮጵያ ቡና 2 (ቢንያም አሰፋ፣ አስቻለው ግርማ)
መከላከያ 0-0 ዳሽን ቢራ
ረቡዕ፣ ህዳር 25
ሐዋሳ ከነማ 2 (ታፈሰ ተስፋዬ አንዱለም ንጉሤ) -
ሐረር ቢራ 1 (አትክልት)
ወላይታ ዲቻ 0-0 ሲዳማ ቡና
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1 (ጫላ ድሪባ) -
አርባምንጭ ከነማ 0
ደደቢት 1 (ሳምሶን ጥላሁን) -
ሙገር ሲሚንቶ 0

## 6ኛ ሳምንት

እሁድ፣ ህዳር 29
ሲዳማ ቡና 1 (ሳሙኤል ተረፈ) -
መብራት ሐይል 0
አርባምንጭ ከነማ 0-0 ወላይታ ዲቻ
ሙገር ሲሚንቶ 0 -
ሐዋሳ ከነማ 1 (አንዱለም ንጉሤ)
ኢትዮጵያ መድን 0 -
መከላከያ 2 (መድሃኔ ታደሰ፣ ሳሙኤል ታዬ)
ቅዱስ ጊዮርጊስ 2 (አይዛክ ኢሴንዴ፣ ኡመድ ኡክሪ) - ኢትዮጵያ ቡና 0
ሰኞ፣ ህዳር 30
ሐረር ቢራ 0 -
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1 (ታዬ አስማረ)
ዳሽን ቢራ 0-0 ደደቢት

## 7ኛ ሳምንት

ቅዳሜ፣ ታህሳስ 5
መብራት ሐይል 0 -
አርባምንጭ ከነማ 1 (ተመስገን ዱባ)
ደደቢት 1 (ዳዊት ፍቃዱ) -
ኢትዮጵያ መድን 2 (ወሰኑ ዓሊ - ፍ.ቅ.ም፣ ኢብራሂም ሁሴን)
እሁድ፣ ታህሳስ 6
ወላይታ ዲቻ 0-0 ሐረር ቢራ
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1 (ፊሊፕ ዳውዚ) -
ሙገር ሲሚንቶ 0
ሐዋሳ ከነማ 2 (ተመስገን ተክሌ፣ አስጨናቂ ሉቃስ) - ዳሽን ቢራ 0
መከላከያ 0 -
ቅዱስ ጊዮርጊስ 3 (ኡመድ ኡክሪ ×2፣ አዳነ ግርማ)
ኢትዮጵያ ቡና 1 (ኤፍሬም አሻሞ) ሲዳማ ቡና 0

## 8ኛ ሳምንት

ቅዳሜ፣ ታህሳስ 12
ቅዱስ ጊዮርጊስ 4 (ቢያድግልኝ ኤሊያስ፣ አዳነ ግርማ፣ ኡመድ ኡክሪ፣ ሳሙኤል ሳኑሚ) -
ሲዳማ ቡና 0
እሁድ፣ ታህሳስ 13
ዳሽን ቢራ 0-0 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ኢትዮጵያ መድን 1 (ሳሙኤል ብርሀኑ) -
ሐዋሳ ከነማ 1 (ተመስገን ተክሌ)
መከላከያ 2 (ሲሳይ ደምሴ - ፍ.ቅ.ም፣ አዳሙ መሐመድ - በራሱ ጎል) -
ደደቢት 2 (ሳምሶን ጥላሁን፣ ዳዊት ፍቃዱ)
አርባምንጭ ከነማ 1 (ተመስገን ዱባ) -
ኢትዮጵያ ቡና 1 (ቢንያም አሠፋ)
ሙገር ሲሚንቶ 1 (ጌዲዮን አካፖ) -
ወላይታ ዲቻ 1 (አሸናፊ ሽብሩ)
ሐረር ቢራ 0-0 መብራት ሐይል

## 9ኛ ሳምንት

ቅዳሜ፣ ታህሳስ 19
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1 (ኤልያስ ማሞ) -
ኢትዮጵያ መድን 0
እሁድ፣ ታህሳስ 20
መብራት ሐይል 0 -
ሙገር ሲሚንቶ (አኪም አካንዴ፣ ጌዲዮን አካፖ)
ሲዳማ ቡና 0-0 አርባምንጭ ከነማ
ሐዋሳ ከነማ 0-0 መከላከያ
ወደሌላ ጊዜ የተላለፉ ጨዋታዎች
ኢትዮጵያ ቡና ከ ሐረር ቢራ
ወላይታ ዲቻ ከ ዳሽን ቢራ
ደደቢት ከ ቅዱስ ጊዮርጊስ

## 10ኛ ሳምንት

ሐሙስ፣ ጥር 1
ሙገር ሲሚንቶ 0-0 ኢትዮጵያ ቡና
አርባምንጭ ከነማ 0 -
ቅዱስ ጊዮርጊስ 1 (ኡመድ ኡክሪ)
ዳሽን ቢራ 1 (አስራት መገርሳ) -
መብራት ሐይል 0
ሐረር ቢራ 1 (በረከት ገብረፃዲቅ) -
ሲዳማ ቡና 0
አርብ፣ ጥር 2
ኢትዮጵያ መድን 0-0 ወላይታ ዲቻ
ወደሌላ ጊዜ የተላለፉ ጨዋታዎች
መከላከያ ከ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ደደቢት ከ ሐዋሳ ከነማ

## 11ኛ ሳምንት

ቅዳሜ፣ የካቲት 8
መብራት ሐይል 3 (አዲስ ነጋሽ፣ አብዱልከሪም ሐሰን፣ በረከት ይስሐቅ) -
ኢትዮጵያ መድን 2 (ተዘራ መንገሻ፣ ሰይፈዲን ሁልደር)
ኢትዮጵያ ቡና 2 (ቢንያም አሠፋ - ፍ.ቅ.ም.፣ ኤፍሬም አሻሞ) -
ዳሽን ቢራ 1 (ዮናታን ከበደ - ፍ.ቅ.ም)
ሰኞ፣ የካቲት 10
አርባምንጭ ከነማ 2 (መልካሙ ፋንድሬ፣ በረከት ደሙ) -
ሐረር ቢራ 1 (በረከት ገብረፃዲቅ)
ማክሰኞ፣ የካቲት 11
ሐዋሳ ከነማ 0 -
ቅዱስ ጊዮርጊስ 1 (በኃይሉ አሠፋ)
ሲዳማ ቡና 2 (አግላን ቃሲም×2) -
ሙገር ሲሚንቶ 1 (አኪም አካንዴ)

ሐሙስ፣ የካቲት 13
ወላይታ ዲቻ 1 (አሸናፊ ሽብሩ) - መከላከያ 0
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 0-0 ደደቢት

## 12ኛ ሳምንት

ቅዳሜ፣ የካቲት 15
ኢትዮጵያ መድን 1 (ጀማል አህመድ) -
ኢትዮጵያ ቡና 2 (ዳዊት እስጢፋኖስ፣ ቢንያም አሠፋ)
መከላከያ 1 (አማኑኤል ግደይ) -
መብራት ሐይል 1 (ራምኬል ሎክ)
እሁድ፣ የካቲት 16
ቅዱስ ጊዮርጊስ 5 (አይዛክ ኢሴንዴ፣ ያሬድ ዝናቡ 2፣ ፍፁም ገብረማርያም 2) -
ሐረር ቢራ 1 (ልይህ ገብረመስቀል)
ሙገር ሲሚንቶ 1-1 አርባምንጭ ከነማ
ዳሽን ቢራ 0-0 ሲዳማ ቡና
ሐዋሳ ከነማ 1 (ተመስገን ተክሌ) -
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 2 (ኤልያስ ማሞ፣ መሐሪ መና)
ወደሌላ ጊዜ የተላለፉ ጨዋታዎች
ደደቢት ከ ወላይታ ዲቻ

## 13ኛ ሳምንት

እሁድ፣ የካቲት 27
ወላይታ ዲቻ 1 (ባዬ ገዛኸኝ) - ሐዋሳ ከነማ 1 (ተመስገን ተክሌ)
ሲዳማ ቡና 2 (ብሩክ አየለ፣ ምትኩ ጎአ) -
ኢትዮጵያ መድን 1 (ሳሙኤል ብርሃኑ)
አርባምንጭ ከነማ 0 - ዳሽን ቢራ 1 (ቢንያም ታዬ)
ሐረር ቢራ 0 - ሙገር ሲሚንቶ 2 (አኪም አካንዴ፣ በኃይሉ ግርማ)
ወደሌላ ጊዜ የተላለፉ ጨዋታዎች
መብራት ሐይል ከ ደደቢት
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ኢትዮጵያ ቡና ከ መከላከያ

## ተስተካካይ ጨዋታዎች

ሐሙስ፣ የካቲት 6
ሙገር ሲሚንቶ 1 (ቴዎድሮስ መሳይ) -
ቅዱስ ጊዮርጊስ 4 (ኡመድ ኡክሪ ×2፣ በኃይሉ አሰፋ፣ ፍፁም ገብረማሪያም)
ሐሙስ፣ የካቲት 27
ቅዱስ ጊዮርጊስ 1 (አበባው ቡጣቆ) - ወላይታ ዲቻ 2(አሸናፊ ሽብሩ - ፍ.ቅ.ም.፣ እሸቱ መና)
ማክሰኞ፣ መጋቢት 2
ወላይታ ዲቻ 0-0 ዳሽን ቢራ
ማክሰኞ፣ መጋቢት 9
መከላከያ 3 (ሲሳይ ደምሴ - ፍ.ቅ.ም.፣ ሳሙኤል ታዬ፣ ፍሬው ሰለሞን) - ንግድ ባንክ 3 (መሃሪ መና፣ ፊሊፕ ዳውዚ ×2)
ደደቢት 1 (ሄኖክ ኢሳያስ) - ኢትዮጵያ ቡና 2 (ኤፍሬም አሻሞ፣ ዘነበ ከበደ - በራሱ ግብ ላይ)
ቅዳሜ፣ መጋቢት 13
ኢትዮጵያ ቡና 3 (ኤፍሬም አሻሞ፣ ፋሲካ አስፋው፣ ዴቪድ በሻህ) - ሐዋሳ ከነማ 2 (ጋዲሳ መብራቱ፣ ግሩም አሠፋ)
ሲዳማ ቡና 1 (ብሩክ አየለ) - ደደቢት 0
እሁድ፣ መጋቢት 21
ደደቢት 1 (መስፍን ኪዳኔ) - ቅዱስ ጊዮርጊስ 2 (አዳነ ግርማ፣ ኡመድ ኡክሪ)
ረቡዕ፣ መጋቢት 24
ኢትዮጵያ ቡና 2 (ኤፍሬም አሻሞ፣ ሰለሞን ገብረመድህን) - ሐረር ቢራ 0
ሐሙስ፣ መጋቢት 25
ደደቢት 3 (ሄኖክ ኢሳያስ ×2፣ መስፍን ኪዳኔ) -
ሐዋሳ ከነማ 1 (ታፈሰ ተስፋዬ)
ሰኞ፣ መጋቢት 29
ደደቢት 4 (መስፍን ኪዳኔ x2፣ ዳዊት ፍቃዱ፣ ታደለ መንገሻ) - ወላይታ ዲቻ 0

## የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የደረጃ ሠንጠረዥ 1ኛው ዙር ከተጠናቀቀ በኋላ

| ደረጃ | ክለብ | ተጫወተ | አሸነፈ | አቻ | ተሸነፈ | አገባ | ገባበት | ልዩነት | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅዱስ ጊዮርጊስ | 13 | 12 | 0 | 1 | 29 | 6 | +23 | 36 |
| 2 | ኢትዮጵያ ቡና | 13 | 8 | 4 | 1 | 19 | 11 | +8 | 28 |
| 3 | ንግድ ባንክ | 13 | 6 | 5 | 2 | 14 | 12 | +2 | 23 |
| 4 | ደደቢት | 13 | 6 | 3 | 4 | 21 | 12 | +9 | 21 |
| 5 | ወላይታ ዲቻ | 13 | 3 | 9 | 1 | 9 | 7 | +2 | 18 |
| 6 | መከላከያ | 13 | 4 | 6 | 3 | 15 | 15 | 0 | 18 |
| 7 | ሲዳማ ቡና | 13 | 4 | 4 | 5 | 7 | 12 | -5 | 16 |
| 8 | ሐዋሳ ከነማ | 13 | 4 | 3 | 6 | 14 | 16 | -2 | 15 |
| 9 | አርባምንጭ ከነማ | 13 | 3 | 6 | 4 | 7 | 8 | -1 | 15 |
| 10 | ሙገር ሲሚንቶ | 13 | 4 | 3 | 6 | 9 | 11 | -2 | 15 |
| 11 | ዳሽን ቢራ | 13 | 2 | 7 | 4 | 3 | 6 | -3 | 13 |
| 12 | መብራት ኃይል | 13 | 2 | 3 | 8 | 10 | 20 | -10 | 9 |
| 13 | ሐረር ቢራ | 13 | 2 | 3 | 8 | 6 | 19 | -13 | 9 |
| 14 | መድን | 13 | 1 | 4 | 8 | 8 | 16 | -8 | 7 |